አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና
የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ

በ
ገዛኸኝ ጐሹ ገብረሥላሴ

ጥቅምት 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና
የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

ለኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር የኤምኤ ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት

*በ*

*ገዛኸኝ ጉሹ ገብረሥላሴ*

አማካሪ

ጌታቸው ኃህለማርያም (ዶ/ር)

*ጥቅምት 2005 ዓ.ም.*

# ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ

*በ*

*ገዛኸኝ ጎሹ ገብረሥላሴ*

*ጥቅምት 2005 ዓ.ም.*

**የፈተና ቦርድ አባላት**

<u>አማካሪ ስም</u> ፊርማ

ጌታቸው ሣህለማርያም (ዶ/ር) ____________

ፈታኝ ስም ፊርማ

[illegible] ____________

[illegible] ____________

# ማውጫ

ገፅ

ማውጫ ........................................................................ i
አበርክቶ ........................................................................ v
ምስጋና ........................................................................ v
ሙዳዬ ቃላት ........................................................................ vi
ስዕል ማውጫ ........................................................................ viii
የአርሲ ዞን ካርታ ........................................................................ x
የሽርካ ወረዳ ካርታ ........................................................................ xi
አጠቃሎ ........................................................................ xii
1. መግቢያ ........................................................................ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................................................ 4
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................................ 5
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........................................................................ 5
1.4. የምርምሩ መሠረታዊ ጥያቄዎች ........................................................................ 6
1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................................................ 6
1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................ 6
1.7. መረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴ ........................................................................ 7
1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ........................................................................ 7
1.7.2. የአጠናን ዘዴ ........................................................................ 8
1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........................................................................ 9
1.8.1. ያጋጠሙ ችግሮች ........................................................................ 9
1.8.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........................................................................ 9
1.9 የጥናቱ አደረጃጀት ........................................................................ 10
1.10. የመስክ ቆይታ ........................................................................ 10
2. ክለሳ ድርሳን ........................................................................ 13
2.1. የንድፈ ሃሳብ መነሻዎች ........................................................................ 13

2.1.1. ቁሳዊ ባህል ምንድ ነው? ........ 13
2.1.2. የቁሳዊ ባህል ዘርፎች ........ 14
2.1.3. የቁሳዊ ባህል ቁሶች ........ 16
2.1.4. ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሂደቶች ........ 19
2.1.5. ቁሳዊ ባህልን የመመደቢያ እና የመተንተኛ ሞዴሎች ........ 20
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 22
2.2.1. ያልታተሙ ጥናቶች ........ 22
2.2.2. የታተሙ ጥናቶች ........ 24
3. የሸርካ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ ........ 26
3.1. መልክአምድራዊ ገጽታ ........ 26
3.2. የመሰረተ ልማት አውታሮች ........ 26
3.3. የወረዳው ሕዝብና ሃይማኖት ........ 27
3.4 የሕዝቡ መተዳደሪያ ........ 28
4. የመረጃ ትንተና በሸርካ ወረዳ የቆዳ ቁሶች ስራ ........ 29
4.1. የቆዳ ቁሶች አይነትና አገልግሎት ........ 29
4.1.1. ለመኝታነት የሚያገለግሉ ቁሶች ........ 29
4.1.1.1. ነት ........ 29
4.1.1.2. ጀባ ........ 32
4.1.1.3. የጠፍር አልጋ /ድንክ/ ........ 33
4.1.2. የግብርና መገልገያ ቁሶች ........ 34
4.1.2.1. ምራን ........ 35
4.1.2.2. መርገጥ ........ 35
4.1.2.3. ማርገቢያ ........ 36
4.1.2.4. መጫኛ ........ 36
4.1.2.5. እጅ ቤዛ ........ 38
4.1.2.6. ገምባሌ ........ 38
4.1.2.7. ዛብ ........ 39
4.1.3. ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውሉ ቁሶች ........ 39
4.1.3.1. አገልግል ........ 39

4.1.3.2. መሶብ ..... 42
4.1.3.3. ቁና/እንቅብ/ ..... 44
4.1.3.4. ወንፊት ..... 45
4.1.3.5 ቀረቦ ..... 46
4.1.4. ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች ..... 46
4.1.4.1. አለንጋ ..... 46
4.1.4.2. ጉመድ ..... 47
4.1.4.3. ማሲኖዳ ..... 48
4.1.4.4. ጋዲ ..... 49
4.1.4.5. ሻንጣ ..... 50
4.1.4.6. ጉፍላ፡- ..... 50
4.1.4.7 ደላጉ ..... 51
4.1.4.8. ጠፍር ..... 51
4.1.4.9 ድቤ ..... 52
4.2. በሸርካ ወረዳ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች መስሪያ መሳሪያዎችና ጥሬ እቃዎች ..... 53
4.3. ለማለስለስ እና ፀጉር ለማስለቀቅ የሚያገለግሉ ጥሬ እቃዎች ..... 55
4.4 ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ለመዳ በሸርካ ወረዳ ..... 56
4.5. የባህላዊ ቆዳ ስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ..... 58
4.5.1. የባህላዊ ቆዳ ስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት ..... 58
4.5.2. የባህላዊ ቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ..... 62
5. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳቦች ..... 64
5.1. ማጠቃለያ ..... 64
5.2. የይሁንታ ሃሳቦች ..... 65
ዋቢ ፅሁፎች ..... 69
አባሪዎች

## *መታሰቢያነቱ*

*እራስህን ጉድተህ እኔን ለዚህ ያበቃኸኝ*
*ለውድ አባቴ ለአቶ ጉሹ ገብረሥላሴ እና*
*ለዛሬው ማንነቴ መሰረት ለሆንሺኝ ለውዷ*
*እናቴ ወ/ሮ ብርቄ ድርባ፣ ያለመታደል*
*ሆኖ ዛሬ ይህን ፍሬ ባታዩትም በዚህ ስራ*
*ስማችሁ ዘላለም ሲታወስ ይኖራል።*

# ምስጋና

በቅድሚያ አማካሪዬን ዶ/ር ጌታቸው ሣህለ ማርያምን አመሰግናለሁ። ከዚያም ይህን ጥናት ለማካሄድ ይረዳኝ ዘንድ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲን ምስጋናዬ ይድረስ። በመቀጠል ከጅምሩ ጀምሮ ድጋፏና ምክሯ ላልተለየኝ ለታላቋ እህቴ ወ/ሮ ጽጌ ጕሹን ምስጋናዬ የላቀ ነው። ሌላው የሸርካ ወረዳ ት/ቤቶች ጽ/ቤት ስፓንሰር ስላደረገኝ ምስጋና ይገባዋል። በዚህ ጥናት ላይ በማቴሪያል፣ በገንዘብ እና መረጃ በመስጠት ለተባበረኝ አቶ ታደሰ መልካሙ ምስጋናዬ ወደር የለውም። ጥናቱን ሳካሂድ መረጃ በመስጠት፣ በመተየብ ለተባበራችሁኝ አቶ መኑር ሐሰን፣ አቶ ታደሰ ሀብቴ፣ ወ/ት ገነት ሲሳይ፣ እንደ አባት ሲመክረኝ ለነበረው የቀድሞ አስተማሪዬ አቶ ግርማ ለማ እና በአባሪው ላይ ስማችሁ የተዘረዘረው በሙሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። በመጨረሻ ከሁሉ ከሁሉ ሥራዬን ሥራዬን ስል ፍላጐታችሁን ተጭኜ የባልና የአባትነት ወጉን ለነፍግኳችሁ ውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ሀረገወይን ሀብታሙ እና ልጆቼ ፅዮን ገዛኸኝ፣ ኤርሚያስ ገዛኸኝ እና ዳግማዊት ገዛኸኝ እጅግ በጣም አድርጌ አመሰግናለሁ።

ሙዳዬ ቃላት

1. ለጉመ- ዕቃን ስፌትን በሲር በማያልቅ ነገር ዳርዳሩን ወደመሆኑ የሚውለውን መቀመጫውን ለጉመ ከፈፍ፣ ለበደ አጠና፣ አጠናከረ
2. መርገጥ- የሞፈርና የድግር መርገጫ ማሰሪያ ጠፍር ድግሩንና እርፉን በወገሉ ቀለበት አግብቶ በሞፈሩ እየጠለፉ አጥብቆ ማሰሪያ።
3. ምራን - ሞፈርን ከቀንበር ጋር ማቆራኛ ወይም ማሰሪያ ጠፍር።
4. ሲር - ከተለፋ ቆዳ በቀጭኑ ተቀዶ የሚወጣ የኮርቻ፣ የስልቻ ወይም የሌላ የቆዳ ዕቃ መስፊያ ወይም ከበሬ ማጅራት ላይ የሚወጣ ጅማት
5. ቀረቦ - ከበሬ ግንባር ወይም ርጥብ ቁርበት በርጥብነት በአንድ ንርት ነገር ላይ ተስፍቶ ሲደርቅ የሚወጣና እንደ እርኮት ያለ ሆኖ የዕቃ ማስቀመጫ፣ ወይም እንደ ቅርጫት ሆኖ የማሰፉ ቀረቦ ወይም ቀርበቦ።
6. ቁና - ከስንደዶና ከአክርማ የሚሰፋ ከስድስት ጣሳ የሚይዝ
7. ቢላዋ - ስለቱ በአንድ ወገን የሆነ ደንደስ ያለው ጉራዴ፣ ቢላዋ መቁረጭ ስለት።
8. ችካል- ድንኳን ሲተከል በድንኳኑ ቋሊማ እየተጠለፉ ድንኳኑን ገትሮ የሚይዝ ካስማ።
9. ነት - ከከብት ቆዳ በቁርበት ፋቂ እጅ የሚፋቅ፣ ተፍቆ ከተለፋ በኂላ በጉፋ፣ በቀረጥ ተነክሮ የሚቀላ ነት የአልጋ ምንጣፍ።
10. እጅ ቤዛ - መንጠርን መንጣሪ፣ እህልን ዐጫጅ እሸህ፣ ብሩ እንዳይወጋው ከተለፉ ቁርበት ሰፍቶ በክንዱ ላይ እጅ ቤዛን ማጥለቅ
11. ወስፌ - እንደምሳር ያለ ጠፍርን፣ ስልቻን፣ የበቅሎን ይህን የመሳሰሉ ሁሉ መስፊያ።
12. ደላጉ - ድብዳብ የበግ ቆዳ፣ የቁርበት፣ የነት እላቂ።
13. ደበል አንሳ - ለቆዳ ሰራተኞች በማህበረሰቡ የተሰጣቸው የሚያገል ስም
14. ደደብ- ቆዳ ሲገፈፍ ከቆዳው ላይ ተለጥፎ የቀረ ስጋ
15. ጀባ - የበሬው ቁርበት ጠጉሩ ሳይመለጥ፣ ሳይፋቅ የሚለፋ ጀባ፣ ቁርበት።
16. ገምባሌ - በእግር ባት ላይ የሚጠመጠም የጨርቅ፣ ወይንም የወፍለቅ ዓይነት፣ ገምባሌ
17. ጉሎ - ጉሎ ቅጠል፣ ሰፋፊ ግንዱ ውስጥ ክፍት ፍሬው ጉሎ ዘይት የሚሆን

18. ጉማሬ አለንጋ- ከጉማሬ ቆርበት የሚወጣና ጉማሬ አለንጋ የሚሆን

19. ጉመድ - የበግ ወይም የፍየል ቅልጥም ቁርበቱ ሳይሰነጠቅ ርጥቡን እንዳለ ሽልቅቆ አውጥቶ ዱላው እንዳይሰነጠቅና ማፈኛ እንዲሆን ያጠልቁትና ከዱላው ላይ ደርቆ ተጠርቆ የሚኖር ጉመድ ያለው ባለ ጉመድ ዱላ።

20. ጉፍላ - በሞተ ጥጃ ቆዳ ውስጥ ገለባ በመጠቅጠቅ የሚሰራ የጥጃ ምስል።


21. ፋቂ - ከእነጠጉሩ የነበረውን ብራናን ፋቂ ወይም ያልተለፋውን ርጥብ ቁርበት ፍቆ አልፍቶ ነትን፣ ማስን፣ ጀንዲን ዳባን የሚያደርግ።

# ስዕል ማውጫ

**ገጽ**


ስዕል 1. አቶ ከበደ ነት ይዘው ........................................ 29
ስዕል 2. ጆባ ........................................ 32
ስዕል 3. ድንክ ........................................ 33
ስዕል 4. የጠፍር አልጋ ........................................ 33
ስዕል 5. የግብርና መገልገያ ቁሶች ........................................ 34
ስዕል 6. ምራን ........................................ 35
ስዕል 7. መጫኛ ........................................ 36
ስዕል 8. መረጃ አቀባዩ መጫኛ ይዘው ........................................ 36
ስዕል 9 እጅ ቤዛ ........................................ 38
ስዕል 10. የተለጐሙ አገልግሎች ........................................ 40
ስዕል 11. አገልግል ........................................ 40
ስዕል 12. ባለሙያው መሶብ በመለጐም ላይ ........................................ 42
ስዕል 13. የተለጐመ መሶብ ........................................ 42
ስዕል 14. ቁና/እንቅብ/ ........................................ 44
ስዕል 15. ወንፊቶች ........................................ 45
ስዕል 16. ቀረቦ ........................................ 46
ስዕል 17. አለንጋዎች ........................................ 46
ስዕል 18. አቶ አሰፋ ጫላ ስለጐመድ ማብራሪያ ሲሰጡ ........................................ 47
ስዕል 19. ማሲኖዳ ........................................ 48
ስዕል 20. ጋዲ ........................................ 49
ስዕል 21. ሻንጣ ........................................ 50
ስዕል 22. ጐፍላ ........................................ 50
ስዕል 23. ድቤ ........................................ 52
ስዕል 24. መጥረቢያ ........................................ 53
ስዕል 25. ወስፌዎች ........................................ 54
ስዕል 26. ቢላዎች (ካራዎች) ........................................ 54
ስዕል 27. የእንጨት ችካሎች ........................................ 55
ስዕል 28. የጉሎ ፍሬ ........................................ 55
ስዕል 29. የጉሎ ተክል ........................................ 55

Arsi zone




Source - Ethio - GIS (2012)

## Location of Shirka Wereda




Source - Ethio - GIS (2012)

# አጠቃሎ


የዚህ ጥናት ርዕስ "ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ" የሚል ነው፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዋና አላማ፣ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በወረዳው ምን እንደሚመስል ማሳየት እና መሰነድ ሲሆን ቁሶቹ ሲዘጋጁ የሚያልፉበትን የአሰራር ሂደት፣ ከቆዳ የሚሰሩት ቁሶች የሚሰሩባቸውን ጥሬ እቃዎች እና ቁሶቹን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ማስተዋወቅ ነው፡፡ በዚህ ስር የባለሙያዎችን ባህላዊ ዳራ፣ በወረዳው የባህላዊ ቆዳ ቁሶች ስራ ታሪካዊ አመጣጥ እና ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ፣ ባለሙያዎቹ ለማህበረሰቡ ያላቸውን አመለካከት እንዲሁም ባህላዊ የቆዳ ቁሶች አይነትና አገልግሎታቸው ምን እንደሚመስል በጥናቱ ተቃኝቷል፡፡ በዚህ አላማ ስር ጥናቱ የሚመልሳቸው አምስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

የጥናቱ አላማን ለማሳካት በጥናቱ ውስጥ ትኩረት ተደርጐባቸው መልስ እንዲሰጥባቸው ለተዘጋጁ የምርምር ጥያቄዎች ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀዳማይና ካልአይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ካልአይ መረጃዎቹ፣ ከቤተመፅሐፍት፣ ከታተሙና ካልታተሙ ጥናታዊ መረጃዎች፣ ከጥናቱ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ዲማዎች፣ ኢንሳይክሎፒዲያዎች፣ መጽሔቶች እና መፅሐፍትን ተጠቅሟል፡፡ በተጨማሪ ከመረጃ መረብ የተገኙ መረጃዎችን እንደግብአት ተጠቅሟል፡፡ ቀዳማይ መረጃዎች ከመስክ የተሰበሰቡ ሲሆን የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ብረት ሰራተኞች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የወረዳው ነዋሪዎች፣ ከቁሶቹ ተጠቃሚዎች እና ከስፌት ባለሙያዎች ጋር በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ አማካይነት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረት በወረዳው ከጥንት ጀምሮ የቆዳ ቁሶች ስራ እንደሚሰራ ጥናቱ ያሳያል፡፡ የጥንቱ የቆዳ ስራ ባለሙያዎች በአዲሶቹ ባለሙያዎች በመዋጣቸው ባህላዊ የቆዳ ስራውን በመተው ወደ ሌላ ስራ እየተሰማሩ እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል፡፡

ምደባውን በተመለከተ የባህላዊ የቆዳ ቁሶቹ በአገልግሎታቸው የተመደቡ ሲሆን ከንድፈ ሃሳባዊ ብያኔዎች ጋር በማገናዘብ አስፈላጊው ትንተና ተደርጐባቸዋል፡፡ ጥናቱ እንደሚያመለክተው የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ከዕለት ወደ ዕለት እየተዳከመ እና ባለሙያዎቹም ሙያውን እየተው ወደ ሌላ ስራ መስማራታቸው በባህላዊ የቆዳ ስራው ላይ ተፅዕኖ ያመጣ ቢሆንም የአካባቢውን የቆዳ ስራ መዳከም በመመልከት ከጐንደር አካባቢ እስቴ ወረዳ የመጡ የባህላዊ የቆዳ ስራ ባለሙያዎች አማካይነት ተዳክሞ የነበረው የቆዳ ስራ እያንሰራራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በጥናቱ የተተነተኑት የቆዳ ቁሶች ከጠቀሜታቸው ባሻገር የማህበረሰቡን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን በማሳየት እና የማህበረሰቡ የእምነት መገለጫ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

ከጥናቱ ግኝቶች መረዳት እንደሚቻለው፣ የባህላዊ ቆዳ ስራ የሚሰራው የባለሙያውን እውቀትና ችሎታ በመጠቀም ጥበብ የተሞላበት በመሆኑ ለተጠቃሚውና ለባለሙያው ጠቀሜታ ይሰጣል፡፡ ይሁንና በወረዳው ለዚህ ሙያ የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው፡፡ ስለሆነም የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ትኩረት ሰጥቶ ባለሙያዎቹ ቁሶቹን የሚያመርቱበትን ቦታ በማመቻቸት እና በማህበረሰቡ ዘንድ ስለባለሙያዎቹ ያለውን አሉታዊ አመለካከት የሚቀይርበት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪ የባህላዊ ቆዳ ስራ ቁሶችን በማሰባሰብ በሙዚየም መልክ ማህበረሰቡ እንዲጐበኛቸው ቢደረግ ለሙያውም ሆነ ለቁሶቹ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

# 1. መግቢያ

በአለማችን ከፍተኛ ደረጃ ደርሰዋል የሚባሉት ሀገሮች የዕድገት ሚስጥር ሲፈተሽ ያላቸውን ሀብት በአግባቡ ሊጠቀም የሚችል የሰው ኃይል ማፍራታቸውና ይህንኑ ሀብታቸውን ለሀገራዊ ጥቅም በማዋላቸው እንደሆነ በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህንን አንስተን የሀገራችንን ሁኔታ መለስ ብለን ለመቃኘት ስንሞክርም የሰው ኃይላችንን ሀብቶቻችንን ሊያለማና ሊጠቅም በሚችል መልኩ አሰልጥነን ልንጠቀምበት ባለመቻላችን መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ አገራችን ካላት ከፍተኛ ሀብት አንፃር ቤቀላሉ ልትጠቀምበትና ኢኮኖሚዋን ልትገነባበት ስትችል ካልተጠቀመችበት ሀብትም የቆዳውን ኢንዱስትሪ በዋናነት ማንሳት ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የ2001 ዓ.ም መረጃ መሰረት አገራችን ኢትዮጵያ 49.3 ሚሊዮን የቀንድ ከብቶች 25.02፣ ሚሊዮን በጐችና 21.88 ሚሊዮን ፍየሎች አሏት፡፡ ዓመታዊ የእርድ መጠኑም (off take rate) የቀንድ ከብት 7%፣ የበግ 33% እና የፍየል ደግሞ 34.3% ነው፡፡ በዚህ ስልት መሰረት በዓመት 3.5 ሚሊዮን የከብት ቆዳ፣ 8.3 ሚሊዮን የበግ ሌጦና 7.5 ሚሊዮን የፍየል ሌጦ ሊሰበሰብ እንደሚችል ይገመታል፡፡ በዚህም ውጤት መሰረት አገራችን ኢትዮጵያ በእንስሳት ብዛት ከአለም 10ኛ እንዲሁም ከአፍሪካ በ1ኛነት ተቀምጣለች፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 181/2002 መሰረት በአዲስ መልክ ተደራጅቶ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን የቀጣይ አምስት ዓመታት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን መሰረት በማድረግም ዘርፉን በምርት፣ በኢንቨስትመንት እና በግብዓት ላይ በመደገፍ ላይ ይገኛል፡፡[1]

የቆዳው ኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለበትን የቴክኖሎጂና የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር በመቅረፍ ደረጃቸውን የጠበቀ የቆዳ፣ የጫማ፣ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ተመርተው ለአገር ውስጥ እና ለውጭ አገር ገበያ በማቅረብ አገሪቷ ካላት የቆዳ ሀብት ተጠቃሚ እንድትሆን

[1] Lidi's journal vol. 2 No.1 Febr 2010 ገጽ 15-17

የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ሐምሌ 1 ቀን 1991 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 41/1991 የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢኒስቲቲዩት በሚል ስያሜ ተቋቁሞዋል።[2]

የቆዳው ኢንዱስትሪ ዘርፍ በአገራችን የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች (manufacturing industries) 6.54% ድርሻ ያለው ሲሆን ከውጭ ምርቶች ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 6.84% ድርሻ እንደሚይዝ ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ እና ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ኢኒስቲቲዩቱ "የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪን በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ማድረግ" የሚለውን ራዕዩን በማሳካት ሀገሪቷ ያላትን የእንስሳት ሀብት ያገናዘበ የውጭ ምንዛሪ ገቢ እንድታገኝ ለማድረግ በሚደረገው ርብርብ ውስጥ መንግስት በተለያዩ መንገዶች እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከዚህም ውስጥ በዘርፉ የተሰማሩ ፋብሪካዎች የተጠናቀቀ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ለውጭ ገበያ በማቅረብ አለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን በማስቻሉ ከታህሳስ 1/2004 ዓ.ም ጀምሮ በከፊል የተጠናቀቀ ቆዳን (rust) ወደ ውጭ መላክ በማስቀረት የተጠናቀቀ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ወደ ውጭ እንዲላኩ አድርጓል።[3]

ኤክስፖርትን በተመለከተ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት /2004/ ከቆዳና ከቆዳ ውጤቶች ምርት 206 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 112.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል።[4]

በአሁኑ ጊዜ ዘርፉን በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርግ ምርት የሚያመርትና ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ የሚጠቀም የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራት አንፃር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በቆዳ ቴክኖሎጂ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች እንዲሰለጥኑ እየተደረገም ነው።

ለተቋሞቹ ቅድሚያ የሚሰጠው ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ቁልፍ የምርት እድገት የተቋሞች ስለሆነና መሆን ስለሚገባቸው ነው። በኢንዱስትሪና ማኑፋክቸሪንግ ልማት

---

[2] በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያው ሪፐብሊክ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ማስተዋወቂያ መድበል አ/አ ሚያዚያ 2004 ዓ.ም ገጽ ገባ

[3] ኢንዱስትሪ፣ ቅፅ 01 ቁጥር 01 መጋቢት 2004 ዓ.ም ገጽ16

[4] ዜና ኢንዱስትሪ ቅፅ 2 ቁጥር 1 መስከረም 2005 ዓ.ም ገጽ 2

የላቀ ደረጃ ላይ የደረሰችውና እንደነ ቶዮታና ሶኒ ያሉ አለማቀፋዊ ግዙፍ ኩባንያዎችን ያፈለቀችው ጃፓን ሳትቀር ከ50% በላይ የሚሆነው የማኑፋክቸሪንግ ምርቷ የሚመረተው በአነስተኛ እና ጥቃቅን የማኑፋክቸሪንግ ተቋም ነው፡፡

በቀጣይነትም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ዘመን መጨረሻ /2007 ዓ.ም/ ቢያንስ ከጫማ ኤክስፖርት 315 ሚሊዩን የአሜሪካን ዶላር፣ ከአለቀለት ቆዳ 136 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እና ከቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ደግሞ 44 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶዋል፡፡[5]

ይህም ጥናት እነዚህን አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እንዲጠናከሩና በዘርፉ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ የጐላ እንዲሆን ለማስቻል ይረዳ ዘንድ ያለመ ነው፡፡

በኢትዮጵያ በባህላዊ መንገድ ከሚሰሩት የእጅ ስራዎች መካከል (ለምሳሌ፣ የጌጣጌጥ ስራ፣ የእንጨት ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ የሽመና ስራ ወ.ዘ.ተ) መካከል ባህላዊ የቆዳ ስራ አንዱ ነው፡፡ ይህ ስራ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲሰራበት እንደነበረ በብራና ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፡፡ "በኢትዮጵያ የብራና ስራ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ በመሆኑ ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በየዘመናቱ አያሌ የብራና መፅሐፍት ተጽፈዋል (ፈቃደ ስላሴ ተፈራ፣ 1979፣125)

"ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ" በሚል ርዕስ የሚጠናው ጥናት ዋና ትኩረት፣ በወረዳው ውስጥ በባህላዊ መንገድ ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶችን አሰራር ምን እንደሚመስል ፎክሎራዊ ትወራን መነሻ በማድረግ መተንተን ይሆናል፡፡

ጥናቱ በፎክሎር ተመራማሪዎች ከተሰጡት ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሂደቶች መካከል Prown (1982፣2) ቁሶችን ለመተንተን የተጠቀመባቸውን ሶስት ነገሮች እነሱም፡-

1. ቁሶቹ የተሰሩበት ጥሬ እቃን በመመልከት 2. ቁሶቹ የተሰሩበትን ዘዴ በመመልከት 3 የቁሶቹን አገልግሎት ምክንያት በማድረግ በሚል ከተዘረዘሩት ነጥቦች መካከል አገልግሎትን መሰረት ያደረገ ምደባን በመውሰድ ባህላዊ ቁሶችን በይመድባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Schlereth J. Thomas, (1980, http://www.btneporg.) ቁሶችን

---

[5] ዜና ኢንዱስትሪ ቅፅ 2 ቁጥር 1 መስከረም 2005 ዓ.ም ገጽ 2

ለመተንተን ያመቻሉ ብሎ ያስቀመጣቸውን ዘጠኝ ሞዴሎች በመውሰድ ከነሱም ውስጥ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን ሞዴሎች ነቅሶ በማውጣት ቁሶችን ለመተንተን ይሞክራል፡፡ ይህ ጥናት በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ላይ ባህላዊ የቆዳ ስራ እየተዳከመ መጥቶዋል፡ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መስፋፋት ምክንያት እየተለወጡ መጥተዋል፡፡ የቆዳ ቁሶች ባለሙያዎች ችግር ገጥሞዋቸዋል፡፡ ወ.ዘ.ተ. ለሚሉ መላምቶች ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በኢትዮጵያ ከሚገኙት የእጅ ስራ ልምዶች መካከል የቆዳ ስራ አንዱ ነው፡፡ ጥንት እንደዛሬው በዘመናዊ ዘዴ የቆዳ ስራ ከመሰራቱ በፊት በተፋቁና በለፉ ቆዳዎች የተለያዩ ቁሶች ይሰሩ ነበር፡፡ ከነዚህም መካከል ነት እና ቦርሳ ይገኙበታል፡፡

በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ ቆዳዎች በሁለት ዓይነት መንገድ ሊፋቁ ይችላሉ፡፡ አንደኛው "ክሮም" ከተባለ ማዕድን በተቀመመ መድሐኒት ሲሆን ሁለተኛው ከዛፍ ቅርፊትና ከአትክልት ጭማቂ በተገኙ ነገሮች ረዳትነት የሚፋቀው ቆዳ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቆዳን ለመፋቅ ከሚረዱ ነገሮች መካከል ኖራና አመድ ይገኙበታል፡፡ /አስራት ወልዴ፣ 1952፣ገጽ የለውም/

የዚህ ጥናት ዓይነተኛ መነሻ ሀሳብም በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ የቆዳ ቁሶች በምን ዓይነት መንገድ እንደሚሰሩ እና ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ላይ የሚሰሩ ቁሶችን መመርመር ነው፡፡ በዚህ ጥናት የቆዳ ቁሶቹ ስራ ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰ ማሳየት ሲሆን ለባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና ጥሬ እቃዎች አቅርቦት ምን እንደሚመስል መፈተሽ፣ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ባለሙያዎች ሙያውን የሚለምዱት እንዴት እንደሆነ፣ የባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት ምን አይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ እና በፎክሎር Folk ነው ወይስ lore ነው የሚንቀሳቀሰው የሚለውን ምሁራዊ አስተሳሰብ ከደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ በመጡ ባለሙያዎች አማካይነት ጥንት ሽርካ ወረዳ ላይ ካለው የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ጋር በማነፃፀር እውነታነቱን ማረጋገጥ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ከ1981 ዓ.ም. እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ በማስተማር ስራ ላይ ተሰማርቼ ቆይቻለሁ። በዚህ ቆይታዬ በወረዳው ዋና ከተማ በጐቤሳና አካባቢው የሚኖሩ ሰዎችን ማንነት፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘዬ ወ.ዘ.ተ. በመጠኑም ቢሆን ለመረዳት ችያለሁ። በቆይታዬም ጊዜ ከዚህ ቀደም ባህላዊ የቆዳ ስራ በጥቂት የአካባቢው ነዋሪዎች ሲሰራ እንደነበር ተመልክቻለሁ። ይሁንና ባሁኑ ጊዜ ባህላዊ የቆዳ ስራውን ተረክቦ የሚያስቀጥል ትውልድ እየተመናመነ መጥቶዋል። የጥናቱ አንዱ አነሳሽ ይህ የሆነበትን ምክንያት ምን እንደሆነ ለማሳየት እና የመፍትሄ አቅጣጫ ለመጠቆም ማሰቤ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ ባህላዊ የቆዳ ስራ ባለሙያዎች ወደ ሽርካ መጥተው ስራውን ያከናውናሉ። በፎክሎር ትምህርት ባገኘሁት እውቀት መሰረት ሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ከቦታ ወደ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ። በዚህ እንቅስቃሴያቸው ከሚሄዱበት አካባቢ ጋር በባህል በወግ በመሳሳሉት ነገሮች ይዋሃዳሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የሚንቀሳቀሰው Folk ነው የሚል ሃሳብ አለ። ከነዚህ በተጨማሪ እንደ Stein (1993, 35) አገላለፅ "Folk can refer to any group of people what's ever who share at least one common actor" ይህ ቡድን Dundes (1980,7) "A group could be as large as a nation or small as a family" ይላሉ። ይህ ቡድን ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳል። ጥበቡ ወይም Lore የሚሉት ግን አይንቀሳቀስም። ቡድኑ ጥበቡን ይዞ ይጓዛል። ሁለተኛው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የዚህን ሀሳብ እውነታነት ለማረጋገጥ ያለኝ ፍላጐት ነው። ሌላው የባለሙያዎች የስራ ውጤት የሆኑትን ባህላዊ የቆዳ ቁሶች አሰራር እና ለመስራት የሚገለገሉባቸውን መሳሪያዎች ሰንዶ ለማቆየት ለፎክሎር ጥናት የበኩሌን አስተዋፅኦ ለማበርከት በማሰብ ነው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት "ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ" በሚል ርዕስ በቁሳዊ ባህል ስር ሀገረሰባዊ እጅ ስራን ይዞ ለመስራት ሲወጠን በዋናነት አላማው ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በወረዳው ምን እንደሚመስል ማሳየት፣ መሰነድና ቁሶቹ ሲዘጋጁ ያለውን የአሰራር ሂደት፣ ቁሶች የሚሰሩባቸውን ጥሬ እቃዎች እና የመገልገያ መሳሪያዎችን መግለፅ ነው። ይህንን ዐቢይ ዓላማም ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች አሉት።

- በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ታሪካዊ አመጣጥን መግለፅ፣
- የባለሙያዎቹን የአሰራር ጥበብ መመርመር፣
- ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ፣ ባለሙያዎቹ ለማህበረሰቡ ያላቸውን አመለካከት ማሳየት

## 1.4. የምርምሩ መሠረታዊ ጥያቄዎች

ከፍ ሲል በ1.3 ስር የቀረቡትን ዋናና ንዑሳን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ፣ ጥናቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል።

- የቆዳ ቁሶች ስራ ጥንተ አመጣጥ እንዴት ነው?
- ለባህላዊ ቆዳ ስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና ጥሬ እቃዎች አቅርቦት ምን ይመስላል?
- የባህላዊ ቆዳ አሰራርን የሚለምዱት ከየት ነው?
- የባህላዊ ቆዳ ስራ ባለሙያዎች ሕይወት እንዴት ይታያል?
- በፎክሎር ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሰው Folk ወይስ Lore ነው?

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ይገኛል። ሁሉንም አካባቢ ማዳረስ ደግሞ ገንዘብ፣ ጊዜ እና አቅም ይጠይቃል። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚያተኩረው በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ላይ ሲሆን በቁሳዊ ባህል ስር ከሚጠኑት ዘርፎች መካከል በሀገረሰባዊ እጅ ስራ ላይ በተለይም በባህላዊ የቆዳ ቁሶች አሰራር ሂደት ላይ ይሆናል።

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል ተብሎ ይታመናል።

- ተጠኚ ማህበረሰቡ ከባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ጋር ተያይዞ ምን ባህላዊ ገጽታ እንዳለው ለአንባቢያን ሊያስተዋውቅ ይችላል።
- በሽርካ ወረዳ የሚገኙ የባህላዊ ቆዳ ቁሶች ባለሙያዎችን የህይወት ልምድ ያስተዋውቃል።
- በአካባቢው ወደፊት በቁሳዊ ባህል ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ሰዎች የተወሰነ መረጃ ይሰጣል።
- የባህላዊ የቆዳ ቁሶችን ቀርሶ እና ሰንዶ ለማቆየት ይረዳል።

## 1.7. የመረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴ

### 1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ

በዚህ ጥናት ተግባራዊ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታ እና የቃለመጠይቅ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የሁለቱ ዝርዝር ይገለፃል፡፡

**ምልከታ**

የትምህርታዊ ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች (እነ ዳንኤል 1994, 84) ከዘረዘሩዋቸው አራት የምልከታ አይነቶች ለዚህ ጥናት ነፃ /ግልፅ/ ምልከታ /ተሳትፎአዊ ምልከታ/ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ይህ የምልከታ ዓይነትም የተመረጠው አጥኚው መረጃ ከሚሰበስብባቸው ሰዎች መካከል በመገኘት ያለምንም ተፅእኖ የሚፈለገውን ባህሪ ወይም ሁኔታ በማነሳሳት በግልፅ መረጃውን ማሰባሰብ ስለሚያስችል ነው፡፡ ይህ ጥናት ከታህሳስ 20 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 10 2005 ዓ.ም ድረስ የተከናወነ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ምልከታ የተደረገው ከታህሳስ 20 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ነው፡፡ ይህ ወቅት የተመረጠበት ምክንያት የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ዐቢይ ፆም ስለሚገባ እና ከደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ የመጡት የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ቆዳ አንደልብ ስለማያገኙ ወደ እስቴ የሚሄዱበት ወቅት በመሆኑ የታህሳስ ወር ለምልከታው አመቺ ጊዜ በመሆኑ ነው፡፡

**ቃለመጠይቅ**

ቃለመጠይቁ በምልከታው ለተገኙ መረጃዎች ድጋፍ እንዲሰጥ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ በምልከታው ላይ የተካተቱ ጥያቄዎች በተቻለ መጠን እንዲካተቱ የተደረገ ሲሆን ጥያቄዎቹም በሙሉ ክፍት ናቸው፡፡ በቃለ መጠይቁም የተሳተፉትም መምህራን፣ አርሶአደሮች፣ ነጋዴዎች፣ ባለ ሆቴሎች፣ ባለ ጠላ ቤቶች፣ የብረታብረት ስራተኞች፣ የስፌት ባለሙያዎች፣ የቆዳ ስራ ባለሙያዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች ከጥናቱ ጋር አግባብነት ያላቸው የቢሮ ኃላፊዎች ናቸው፡፡ መረጃ አቀባዮቹ ወንዶችና ሴቶች ሲሆኑ እድሜያቸውም ከ18 ዓመት እስከ 90 ዓመት የሚደርሱ 30 ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ ለቃለመጠይቁ የተመረጡ ሰዎች በአካባቢው ሕብረተሰብ ስለ ጉዳዩ ያውቃሉ የተባሉ

ናቸው፡፡ በዚህ የቃለ መጠይቅ ወቅት ቴፕ፣ አሥራ አራት የቴፕ ካሴቶች እና የማስታወሻ ደብተር አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

### 1.7.2. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ከአይነታዊ የምርምር ዘዴ አንዱ በሆነው በገላጭ የምርምር ስልት የተደረገ ነው፡፡ ስልቱ የተመረጠው ጥናቱ መረጃዎችን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ለአንባቢያን የሚያቀርበው ትረካዊ በሆነ ወይም ገለጣዊ መንገድን ተከትሎ በመሆኑ ነው፡ ይህ ስልት አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጐ በትረካዊ መንገድ የሚያቀርብበት ስለሆነ ነው፡፡

የመጀመሪያ ምልከታ ከታህሳስ 20 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ ተካሄዷል፡፡ በዚህ ወቅት ለጥናቱ አስፈላጊ ናቸው የተባሉ ሰዎች በአመቺ ወይም ግኝት ናሙና ዘዴ በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ ይህ ዘዴም የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱን ለማጥናት ከጊዜ፣ ከጉልበት እና ከገንዘብ አቅም አጥረት አኳያ አመቺ በመሆኑ ነው፡፡

ምልከታው ያተኮረው ከደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ መጥተው በወንዝ ዳር አካባቢ ቤት ተከራይተው በሚኖሩ የቆዳ ስራ ባለሙያዎች ላይ ነው፡፡

ሁለተኛው ምልከታ ከ ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ የተካሄደ ሲሆን በዚህ ወቅት የቪዲዮ ካሜራ፣ የፎቶ ግራፍ ማንሻ ካሜራ፣ ዲጂታል የፎቶ እና የቪዲዮ ካሜራ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ባለሙያዎቹ ቁሶቹን እንዴት እንደሚሰሩ እና ለቁሶቹ መስሪያ የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ሲያስተዋውቁ በቪዲዮ ካሜራ ተቀርፀዋል፡፡ በቃል የሚመልሷቸውን ጥያቄዎች በቴፕ በመቅረፅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በቴፕ እና በቪዲዮ የተሰበሰቡት መረጃዎች ወደ ፅሁፍ ተለውጠዋል፡፡

ሶስተኛው ምልከታ ከየካቲት 12 ቀን እስከ የካቲት 22 ቀን 2004 ዓ.ም የተደረገ ሲሆን በዚህም በቀጠሮ ያልተገኙ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ተችሏል፡፡

## 1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

### 1.8.1. ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት እንደመሆኑ መጠን በመስክ ስራ የተደገፈ መሆን ስላለበት፣ ለመስክ ስራ የሚሆኑ ግብአቶች ለምሳሌ፡- ቴፕ ሪከርደር፣ የቴፕ ካሴት፣ ቪዲዮ ካሜራ፣ ዲጂታል የፎቶና የቪዲዮ ካሜራ የመሳሰሉትን ለማሰባሰብ ከፍተኛ ውጣ ውረድ አጋጥሞኛል። የመጀመሪያው ችግር የቴፕ ካሴት ነው። ሁለተኛው የቴፕ ሪከርደር ሲሆን ሶስተኛው የዲጂታል ካሜራ ባትሪ ቶሎ ቶሎ ቻርጅ ካልተደረገ ለረጅም ጊዜ ማገልገል አለመቻሉ ነው። አራተኛው የቪዲዮ ካሜራ ሲሆን መሳሪያውን በኪራይ፣ ባለሙያውን በቅጥር ለማግኘት አለመቻሉ ሌላው ችግር ነበር።

መረጃ አቀባዮቹ ገሚሱ በንግድ ስራ የተሰማሩ ገሚሱ ደግሞ በመንግስት ስራ ላይ ያሉ ወ.ዘ.ተ በመሆናቸው በቀጠሮ ሰዓት ለማግኘት አስቸጋሪ ነበር። የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎቹም ጥሬ ዕቃውንና የሚሰሩ ቁሶችን ለማሰባሰብ ከቦታ ወደ ቦታ ስለሚንቀሳቀሱ እነሱን ለማግኘት ፣ሲገኙም ሂደቱን ለመንገር አለመፈለግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቆዳ ቁሶች ስራ አሁን ተጀምሮ አሁን የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ የአሰራር ሂደቱን አንድ በአንድ ለማሳየት አለመቻል፣ የመረጃ አቀባዮቹ ምላሽ አንዳንድ ጊዜ የማይጣጣም ሆኖ መቅረቡ በመስክ ቆይታ የታዩ ችግሮች ናቸው። በቃለ መጠይቅ ወቅት ደግሞ እውነተኛ የሆነውን ነገር ለመናገር በመፍራት ዳርዳር ያሉ ሰዎችም አጋጥመዋል። በባለሙያዎቹ በኩልም ሆነ በመረጃ አቀባዮቹ መረጃ ለመስጠት የተለያየ ምክንያት በማቅረብ ገንዘብ እንዲሰጣቸው መጠየቃቸው ሌላው ችግር ነበር።

### 1.8.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

የቴፕ ካሴቱን በተመለከተ በዚህ ስራ ላይ የተሰማሩትን ነጋዴዎች በሰዎች አማካይነት ተዋውቄ ለመግዛት ችያለሁ። የቴፕ ሪከርደሩን በተመለከተ ከመደበኛው ሱቅ ውጭ ያገለገሉ ኤሌክትሮኒክስ መሸጫዎች የሚገኙበትን ቦታ በማሰስ ለስራው የሚሆን የተፈተሸ ቴፕ ሪከርደር በመግዛት ችግሩን አቃልያለሁ። የዲጂታል ካሜራውን ባትሪ ደግሞ ወዲያው ቻርጅ የሚያደርግበትን ሁኔታ በማመቻቸት ችግሩን ተወጥቼአለሁ። የቪዲዮ ካሜራውን በተመለከተ በጥናቱ አካባቢ በዚህ ስራ ላይ ከተሰማራው ሰው ጋር

መሳሪያውን በኪራይ ባለሙያውን ደግሞ በቀን አበል በመስማማት ችግሩን ለመቅረፍ ችያለሁ፡፡

መረጃ አቀባዮችን በተመለከተ በተደጋጋሚ ቦታው ላይ በመሄድ ቀጠሮ በማስያዝ ክፍተቱን ለመሙላት ችያለሁ፡፡ ባለሙያዎቹ በመስክ ስራ ሲሰማሩ የሚያገኙትን ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት ወጪያቸውን በመሸፈን ለጥናቱ ተባባሪ እንዲሆኑ አድርጌያለሁ፡፡ በስራው ወቅት የአሰራር ሂደቱን ለመቅረፅ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ በተለያየ መልኩ እያንዳንዱን ሂደት እንዲሰሩ በማድረግ ችግሩን ለመቅረፍ ተችሏል፡፡

## 1.9 የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ አላማ፣ የምርምሩ መሠረታዊ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ በጥናቱ ያጋጠሙት ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፣ የመስክ ቆይታ ተካተዋል፡፡ ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ነው፡፡ በዚህ ስር የንድፈ ሀሳብ መነሻዎችና መሠረታዊ ሀሳቦች ብያኔ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ በምዕራፍ ሦስት ውስጥ የምናገኘው የወረዳው አጠቃላይ ገፅታ የሚያስተዋውቀውን ክፍል ነው፡፡ በዚህ ስር የወረዳው መልካምድራዊ ገፅታ፣ የመሰረተ ልማት አውታሮች፣ የወረዳውን ህዝብና ሀይማኖት ተገልጿል፡፡ ምዕራፍ አራት ደግሞ የመረጃ ትንተና የቀረበበት ክፍል ሲሆን በዚህ ስራ የቆዳ ቁሶች አይነትና አገልግሎት፣ ቁሶቹ የሚሰሩበት ጥሬ እቃና መሣሪያዎች፣ በወረዳው የቆዳ ቁሶች ስራ እንዴት እንደተለመደ እና የባለሙያዎቹ ማህበራዊ ህይወትና ኢኮኖሚያዊ ገፅታ የተዋወቀበት ክፍል ነው፡፡ ምዕራፍ አምስት ደግሞ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡

## 1.10. የመስክ ቆይታ

የመስክ ቆይታዬ ከታህሳስ 20 ቀን 2004 ዓ.ም እስከ የካቲት 22 ቀን 2004 ዓ.ም ነበር፡፡

ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት በጥናቱ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን ከቤተ መፅሐፍት እና ከቤተ-መዘክር ወዘተ አንብቢያለሁ፡፡ በመስክ ስራ ወቅት ከተለያዩ ቢሮዎች ጋር በጥናቱ ዙሪያ ስለምገናኝ ከክፍለ ትምህርቱ የድጋፍ ደብዳቤ አስፅፌያለሁ፡፡ ለጥናቴ መነሻ የሆኑኝ

ከጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ የመጡ የቆዳ ስራ ባለሙያዎች በባህላዊ ቆዳ ቁሶች ስራ አሁንም ተሰማርተው እንደሚገኙ በስልክ መረጃ ሰብስቤያለሁ። የባህላዊ ቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎችን በስራው ላይ ተሰማርተው የማገኝበትን ትክክለኛ ጊዜ በስልክ በመገናኘት መረጃ ሰብስቤያለሁ። ከዚያም ለመስክ ስራ የሚያስፈልጉኝን ቁሶች እንደ ቴፕ ሪክርደር፤ ቪዲዮ ካሜራ፣ የፎቶ ግራፍ ማንሻ ካሜራ፤ ዲጂታል የቪዲዮ ካሜራ የመሳሰሉትን የዲጂታል ካሜራ እና የቴፕ ሪከርደር አጠቃቀም በባለሙያ ስልጠና ወስጀያለሁ።

የመጀመሪያ ዙር ታህሳስ 20 ቀን 2004 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ለምልከታ ከአዲስ አበባ 265 ኪ. ሜትር ከአርሲ ዞን ዋና ከተማ ከአሰላ 90 ኪሎ ሜትር በስተደቡብ ወደምትርቀው አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ጎቤሣ ከተማ ተጓዝኩ።

በመጀመሪያ ታህሳስ 23 ቀን 2004 ዓ.ም ወደ ሽርካ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በመሄድ ለወረዳው አስተዳደር ለአቶ ደምሴ አረዶ የተሰጠኝን ደብዳቤ በማሳየት በማንኛውም ጽ/ቤትና መረጃ አገኛለሁ የምለው ቦታ ላይ እንድሰራ ፍቃድ አገኘሁ። በቀጣይ ያደረኩት ለጥናቴ የሚያስፈልጉኝን መረጃ አቀባዮች እና ባለሙያዎቹን የማፈላለግ ስራ ነበር። ባለሙያዎቹ የሚሰሩበት ቦታ ድረስ በመሄድ በስራ ላይ እንዳሉ አረጋገጥኩ። ከዛም ለቀረፃ ቀጠሮ በመያዝ ወደ ቀጣይ ተግባር ተሸጋገርኩ፡ ቀጣዩ ስራ የሽርካ ወረዳ የቆዳ ባለሙያዎችን ማግኘት ስለነበር ይህንን ቦታ የሚጠቁመኝ ቁልፍ የመረጃ አቀባዬን በመያዝ ወደ ቤታቸው ሄድን በአጋጣሚ ሰዎቹን ባለማግኘታችን ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

በሁለተኛው ቀን ታህሳስ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ስለ ሽርካ ወረዳ አጠቃላይ መረጃ የሚሰጡኝ ሰዎች ቤት ለቤት በመሄድ መረጃ ለመብሰብ ቀጠሮ ያዝኩ። በተጨማሪ ባህላዊ የቆዳ ቁሶቹ ይገኛሉ የተባሉበት ቦታ ድረስ በመዘዋወር ቁሶቹ መኖራቸውን በማረጋገጥ በቀጠሮ ተለያየን። በሶስተኛው ቀን ታህሳስ 25 ከደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ ከመጡ የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ጋር በመገናኘት አመቺ የሆነውን ጊዜ በመምረጥ በቀጠሮ ተሰናበትን።

በአራተኛው ቀን ታህሳስ 26 ቀን 2004 ዓ.ም የስፌት ባለሙያዎችንና የብረት ብረት ሰራተኞች ቤት ድረስ በመሄድ ስለ ጉዳዩ አስረድቼ ለቀረፃ ቀጠሮ ሰጥቼ ተሰናበትኩ።

በአምስተኛ ቀን ታህሳስ 27 ቀን ለቀረፃው የሚያስፈልገኝን ባለሙያ በማፈላለግ በከተማው ውስጥ ለሠርግና ለልዩ ልዩ ዝግጅቶች የቪዲዮ ቀረፃ ስራ ከሚሰራ ሰው ጋር የቪዲዮ ከሜራውን በኪራይ ባለሙያውን ደግሞ በቀን አበል በመዋዋል ቀጠሮ ያዝኩ፡፡

በሁለተኛው ዙር ከ ከጥር 23 ቀን 2004 የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም በመጀመሪያ ከቪዲዮ ካሜራ ባለሙያው ጋር በመገናኘት ለቀረፃ ተዘጋጀን፡፡ በቅድሚያ የቀረፅነው የከተማዋን ዋናዋና ቦታዎች ሲሆን ከዚያም ወደ ቆዳ ቁሶች ስራ ባለሞያዎች መስሪያ ቦታ በመሄድ ለተከታታይ አምስት ቀናት እያንዳንዱ የቆዳ ቁስ የሚሰራበትን የአሰራር ሂደት በካሜራ ተቀርፆዋል፡፡ በመቀጠል መረጃ አቀባዮችን በየቤታቸው እና በመስሪያ ቦታቻው በመሄድ ቃለመጠይቅ በማድረግ፣ ከቆዳ የተሰሩትን ቁሶች በፎቶ ግራፍ እና በቪዲዮ ካሜራ በመቅረፅ፣ ዕለት ዕለት በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ወደ ፅሁፍ በመለወጥ የሁለተኛው ዙር ጉዞ ተጠናቆዋል፡፡

ሶስተኛው ዙር ከየካቲት 17 ቀን እስከ የካቲት 22 ቀን ድረስ ሲሆን በዚህን ወቅት በሁለተኛው ዙር ያላገኘኋቸውን ሰዎች መረጃ ለመቀበል የተጓዝኩት ጉዞ ሲሆን ከተለያዩ ቢሮዎች እና ከመረጃ አቀባዮች የተገኙ መረጃዎች የተጓደሉትን በሟሟላት ተጠናቋል፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ስር የንድፈ ሃሳብ መነሻዎች፣ የቁሳዊ ባህል ዘርፎች፣ የቁሳዊ ባህል ቁሶች፣ ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሂደቶች እና ቁሳዊ ባህልን የመመደበያና የመተንተኛ ሞደሎች ይቃኛሉ።

### 2.1. የንድፈ ሃሳብ መነሻዎች

#### 2.1.1. ቁሳዊ ባህል ምንድ ነው?

መንፈሳዊ፣ ቁሳዊ፣ ስነፅሑፋዊ እና ተመድረካዊ የሆኑ ነገሮችን የሚያጠናው ፎክሎር በስሩ ከሚያቅፋቸው ዘርፎች መካከል ቁሳዊ ባህል (material culture) አንዱ ነው።

ይህን የፎክሎር ክፍል የሚያጠናውን ጉዳይ በተመለከተ ፈቃደ አዘዘ (1991፣15) ከዶርሰን ያገኙትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው ገልፀውታል።

> *"ቁሳዊ ባህል" በአይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወ.ዘ.ተ. አሰራርን ሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሳሪያዎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል ማለት ነው። እቃውን እራሱን ማጥናት አንዱ ዋና ተግባር ሲሆን አሰራሩን ማጥናት ደግሞ ሌላው ነው ማለት ነው።*

ቁሳዊ ባህል በዕለት ተዕለት ሕይወታችን የምናየው ባህል አካላዊ ወይም ቴክኖሎጂካዊ ጉዳይ ነው። ይህም አካላዊ ቁስ በማህበረሰቡ ዘንድ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። "Material culture has in common that it is tangible- can be touched, seen eaten or lived in" (Sims and Stephens 2005, 13) በማለት ይገልፃሉ።

ቁሳዊ ባህል ተጨባጭነት ያለውና በአይን ሊታይ እና በእጅ ሊዳሰስ የሚችል ነገር እንደሆነ እንረዳለን። እነዚህ ቁሶች በእጅ የሚሰሩት አልያም ደግሞ በብዙሃኑ የሚመረቱና ዕለት ተዕለት የምንጠቀምባቸው ናቸው። ቁሳዊ ባህል ከቃላዊ ፎክሎር፣ ይልቅ አካላዊ፣ በአይን የሚታይ፣ በእጅ የሚዳሰስ ነው።

ባህላዊ ቁሶች የሰው ልጅ ለራሱ መገልገያ ሲል ከአካባቢው ባገኛቸው ቁሶች አማካይነት የራሱን የፈጠራ ስራ ተጠቅሞ የሚገለገልባቸው ናቸው። እነዚህ ቁሶች

ከመገልገያነታቸው ባሻገር የማህበረሰቡን ማንነት የመጠቆም ኃይል አላቸው። ባለሙያውም በሚሰራቸው ቁሶች ላይ የራሱን አሻራ ያሳርፍባቸዋል።

ቁሳዊ ባህል ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ከመስፋፋቱ አስቀድሞ የሰው ልጅ በባህላዊ መንገድ የመገልገያ ቁሶቹን ከተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች በማበጀት ሲጠቀምበት የነበረን የቁሶች አሰራር ሂደትን እንዲሁም ቁሶቹን ራሳቸውን የሚያጠናበት መንገድ እንደሆነ የቁሳዊ ባህል ትንታኔዎች ይጠቅሳሉ። እነዚህ ቁሶች የተጠኚውን ማህበረሰብ ማንነት ከመግለፅ ባለፈ ጥልቅ የፈጠራ ችሎታቸውን ይገልፃሉ።

> *Material culture is culture made material it is the inner wit at work in the world. Beginning necessarily with things, but not ending with them, the study of material culture uses objects to approach human thought and action. (Glassie, 1999,41)*

*Glassie* እንዳሉት ቁሳዊ ባህል፣ ባህሉ ራሱ ያፈራቸው የሰው ልጅ መገልገያ መሳሪያዎች ናቸው። ቁሶቹ ደግሞ የማህበረሰቡን ድብቅ የፈጠራ ችሎታ የሚያንፀባርቁ ናቸው።

ቁሳዊ ባህል አንድን ቁስ መቼ እንደተሰራ የሚጠቁሙና ራሳቸው ሰዎች ለዕለት ተዕለት ኑሮአቸው መገልገያነት የሰሩዋቸው እና የሚጠቀሙባቸው በተጨማሪ ራሳቸውን ከተለያየ ነገር የሚከላከሉባቸው መሳሪያዎችን የሚይዝ በትምህርት ዙሪያ እንዲያገለግል የተሰጠ ስያሜ እንደሆነ ምሁራን ይገልፃሉ። (Dorson, 1972, 2)

### 2.1.2. የቁሳዊ ባህል ዘርፎች

በ Dorson (1972) የተዘረዘሩት ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ (Folk crafts)፣ ሀገረሰባዊ ስዕል (Folk Arts)፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና (Folk Architecture) ሀገረሰባዊ ልብስ (Folk custome) እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር (Folk cookery) የሚሉት ይገኙበታል። እነዚህን ክፍሎች አንድ በአንድ ስናያቸው፡-

ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ (Folk Crafts) በቁሳዊ ባህል ጥናት ስር ከሚተኮርባቸው አንዱ ሲሆን ሰዎች ዘመናዊ ባልሆነ መንገድ ከአካባቢያቸው በሚገኙ ቁሶች አማካይነት ለራሳቸው መጠቀሚያ በእጅ የሚሰሩዋቸው ቁሶች ናቸው። (Dorson, 1972, 233) ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ የሚባለው ልዩ ልዩ የሸክላ ስራዎችን፣ በአንጥረኛ የሚሰሩ ለልዩ

ልዩ ተግባር የሚውሉ ዕቃዎችን፣ ስፌቶችንና በወንዶች የእጅ ስራነት የሚታወቁትን እንዲሁም ከተለያዩ የእንስሳት ቆዳዎች የሚሰሩ ቁሶችን ያካትታል፡፡

Roberts ስለ Folk Craft ሲገልፁ "Folk crafts are traditional craft" (Roberts ውስተ Dorson, 1972, 233) ይሉታል፡፡ ይህ የእጅ ስራ ዘዴ እና ዲዛይን ከአንድ ቤተሰብ ወደ ብዙ ትውልድ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ነው፡፡ ይህም አመጣጥ በመጀመሪያ ደረጃ ቤተሰቡ ይህን ሙያ ሲሰራ በመመልከት በቅብብሎሽ ከአያት ቅድመ አያት ወደ ልጅ እየተላለፈ የሚመጣው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ምንም አይነት የስጋ ዝምድና ሳይኖር በስልጠና ሙያውን የሚለምድበት መንገድ ነው፡፡

Roberts እንደሚሉት ቁሶቹ የተሰሩበት መንገድ አካባቢያዊ እውቀት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የማህበረሰቡን ባህል ቀልጭ አድርገው ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ (እንደላይኛው፣ 233)

ሀገረሰባዊ ስዕል (Folk art) የሚባለው የቁሳዊ ባህል ክፍል ልዩ ልዩ ሀገረሰባዊ ስዕሎችን፣ ቅርፃቅርፆችን ያካትታል፡፡ ሀገረሰባዊ ስዕሎችና ቅርፃቅርፆች በአይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ ናቸው፡፡ ሰው ውበታቸውን አይቶ እንዲያደንቃቸው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ እነዚህን ስዕሎች ለመስራት ከተለያዩ ነገሮች መሰራታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከቆዳ ለሚዘጋጁት ስዕሎች የፍየል ወይም የበግ ወይም የፈረስ ቆዳ ፍቆ ማዘጋጀትን ይጠይቃል፡፡ የቆዳ አዘገጃጀቱ ከሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ሲመደብ ስዕላቱ ከሀገረሰባዊ ስዕል ስር ይመደባሉ፡፡

ሀገረሰባዊ ምህንድስና (Folk Architecture) ልዩ ልዩ የቤት አሰራርን፣ ሀገረሰባዊ የመንገድ አቀያየስን፣ የአጥር አሰራርን፣ ባህላዊ የመስኖ ስራ የመሳሰሉትን የሚያጠና ነው፡፡ ሰዎች ተራራ ወጥተው ቁልቁለት ወርደው ወንዝንና ባህር ተሻግረው ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቶቻቸውን እንዳያደርጉ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ተፈጥሮአዊ ነገሮች ለማሸነፍ በልምድ ያካበቱትን ሀገረሰባዊ የምህንድስና እውቀታቸውን ተጠቅመዋል፡፡

ሀገረሰባዊ ልብስ (Folk Costume) ማንነትን ለመግለፅ በአንድ ማህበረሰብ አባላት በአለባበስ፣ በፀጉር አሰራር፣ በሌሎች የማጌጫ ዕቃዎች ማጌጥን ይመለከታል፡፡ የአንድ ማህበረሰባዊ ቡድን አባላት በአንድ በኩል የራሳቸውን ማህበረሰብ አባልነታቸውን በሌላ በኩል ደግሞ ከሌላ ማህበረሰብ ቡድን አባላት የተለዩ መሆናቸውን ለመግለፅ ይጠቀሙበታል፡፡ ሀገረሰባዊ ልብስ በቦታና በማህበራዊ ቡድን ይለያያል፡፡

ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር (Folk Cookery) የአንድን ማህበረሰብ የምግብ ዓይነትና አሰራር ያመለክታል፡፡ በተለያየ አካባቢ ያለ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ የምግብ አሰራርና የአመጋገብ ስርዓት አለው፡፡ አንድ ማህበረሰብ የሚመገበው ምግብና የምግብ አሰራር ከሌላው ይለያል፡፡ የራሳቸውን የሆነ የምግብ አዘገጃጀትና አሰራር ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከሌላው የሚለዩበት አመጋገባቸው መለያቸው የሚሆንበት አጋጣሚ በርካታ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ማህበረሰብ ከሌላው ጋር የሚጋራው የምግብ አሰራርና የአመጋገብ ስርዓት አለው፡፡

## 2.1.3. የቁሳዊ ባህል ቁሶች

የቁሳዊ ባህል ቁሶችን ለማጥናት ስንነሳ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወስ ይገባል፡፡

1. በቁሶቹ ላይ የተፃፈ ታሪክ
2. ቁሱ ምንድ ነው?
3. ቁሱ አሁን የሚገኘው የት ነው?
4. ቁሱ የተሰራበት ቀን መቼ ነው?
5. የቁሱ ተግባር (አገልግሎት) ምን ነበር?
6. ማን ሰራው?፣ ባለቤቱ ማነው? ወይም ቁሱን የሚጠቀመው ማን ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች በቂ ምላሽ መስጠት ይኖርብናል፡፡ (1 Dec. 2004 http://chnm.Gmu.edu) ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በዝርዝር ስንመለከታቸው:

በቁሶቹ ላይ የተፃፈ ታሪክ ለመፃፍ ስንነሳ ያለን ችሎታ የሚወሰነው በሚኖረው የመረጃ ተአማኒነት ነው፡፡ ለምሳሌ ከቀንድ የሚሰሩ ቁሶችን በመመልከት እዛ አካባቢ እንስሳው ይኖር እንደነበር ለመገመት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል በቁሱ ላይ የተፃፈው ፅሁፍ ቁሱ ለማን፣ የት እና መቼ እንዳገለገለ የሚጠቁም ነገር ይዞ የሚገኝበትም አጋጣሚ አለ፡፡ በቁሶች ጥናት ላይ ቁሱን ብቻውን ከማጥናት ከተፃፈ ገለፃ ጋር ማየት ለግንዛቤ ይረዳል፡፡

ቁሱ ምንድ ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ታሪካዊ ትንተና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በቁሶች ላይ ታሪካዊ ትንተና ስንሰጥ ደግሞ ጥንቃቄ የተሞላበት ገለፃ ያስፈልጋል፡፡ በአካባቢያችን ዙሪያ ቤታችን ወይም የመማሪያ ክፍላችንን ስንመለከት ቁሶች የትም አሉ፡፡ አብዛኞቹን የምናያቸውን ቁሶች ማወቅ የቻልነው ከኛ ጋር አብረውን ያሉ ስለሆነ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቁሱን ስንተነትን ተጨባጭ መረጃ የሚሆነን በቁሱ ላይ የተፃፈ የቁሱ ግለ ታሪክ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቁስ የሚነገር ታሪክ አለው፡፡ ታሪኩ ለሰዎች ጥቅም ሲባል ቅርፁን ይይዛል፡፡ የታሪክ ሰዎች ቁሶችን በሚተነትኑበት ጊዜ መሰረታዊ ከሆኑ "እውነታዎች" ከቃላዊ ገለፃ ምዝገባ ይጀምራል፡፡ ከተቻለ ደግሞ ፎቶ ግራፍ ይጠቀማሉ፡፡ ገለፃው የሚያካትተውም መለኪያውን፣ ቁሱን፣ የተለየ ገጽታውን እና ጥቅሙን ነው፡፡ ይህ አይነቱ መረጃ የሚያገለግለው ቁሱ ለአጠቃላይ ቴክኖሎጂ ኢኮኖሚ ወይም ማህበራዊ ግንኙነት በአንድ በተወሰነ ማህበረሰብ እና እንዴት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀየር ቻለ የሚለውን ለማወቅ ይረዳል፡፡ የቁሱ መስሪያ (ለምሳሌ፣ ሸክላ፣ ማሰሮ ለመስራት ይጠቀማል፡፡)

ቁሱን በምናጠናበት ጊዜ ከነዚህ መሰረታዊ ገለፃ መጀመር አለብን፡፡

1. ቁሱን በጥንቃቄ መመልከት፣ በጥልቀት ትኩረት መስጠት
2. በቁሱ ላይ መጠኑን፣ ቅርፁን እና የተለየ ባህሪውን ማስታወሻ መያዝ
3. ከተቻለ ቁሱን ከተለያዩ ማዕዘኖች ማየት
4. በምንገልፅበት ደረጃ ያለን ማስታወሻ (ከመፅሐፍ፣ ከዌብ ሳይት ወይም ከሙዚየም) የሚነግረን ነገር ምንድነው? ነገር ግን ገለፃዎቹ የኛን ጥያቄዎች ሊወስኑ አይገባም፡፡

ቁሱ አሁን የሚገኘው የት ነው? እንዴትስ እዚህ ሊገኝ ቻለ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የቁሱ ግለታሪክ የቁሱን ባለቤት በተለያየ መቼት እንዴት ይጠቀምበት እንደነበር መረጃ ማካተት ይኖርበታል፡፡ ቁሱ ሲመረት በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ ለአንድ ተግባር በቀጣዩ ጊዜ ትእምርታዊ እሴት ሊኖረው ይችላል ወይም የቁሱ ዋና ተግባር ምናልባት ከማህበረሰቡ ውጭ የመጣ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ማህበረሰቡ ለረጅም ጊዜ በቁሱ መጠቀም አቁሞ ይሆናል፡፡ አብዛኛው ቁሶች በብዙ የታሪክ ደረጃዎች ሲተላለፉ የተገኙበትን አካባቢ ለማግኘት አዳጋች ነው፡፡ እንዴት ቁሱ የተገኘበት አካባቢ ሊደረስ ቻለ? ስለ ቁሱ አካባቢና ማህበር ዓውድ ምን ሊነግረን ይችላል? ዓውድ ስለተሰራበት ቀን መረጃ አለው? የሚሉት ጥያቄዎች ለለውጡና ለግንኙነቱ ተጨባጭ መረጃ ለማግኘት ይረዳል፡፡

ቁሱ የተሰራበት ቀን መቼ ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ቁሶቹ የተሰሩበትን ቀን ማወቅ ያሻል፡፡ ነገር ግን በቁሱ ግለ ታሪክ ላይ ዋናው ቀን ምናልባት በጣም አስፈላጊ ቀን ላይሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ቀናት የማህበረሰቡን ከጊዜ ወደ ጊዜ መቀየር ትኩረት በማድረግ ይገልፃሉ፡፡ ጥቂት ቁሶች በራሳቸው ላይ ቀናት ተፅፎባቸው ይገኛል፡፡ የተሰሩበትንም ጊዜ ያገናኛሉ፡፡ ሌሎቹ ቁሶቹ ምናልባት ታሪካዊ በሆነ ምስል ይገልፃሉ፡፡ እንደ ሳንቲም በመሳሰሉት ጥቂት ቁሶች በባለቤታቸው በተመዘገበ መረጃ እንዴትና መቼ ቁሱ እንደተገኘ በመፈተሽ ያገኙታል፡፡ በአጋጣሚ አብዛኛው ቁሶች ያለመረጃ ይመጣሉ፡፡ እንደነዚህ አይነቶቹ ቁሶች በጣም አስቸጋሪ ናቸው፡፡ ግን እስካሁን ድረስ በላቦራቶሪ ምርመራ፣ በሞዴላቸውና በንፅፅሮሽ እየተመዘገቡ ይገኛሉ፡፡

የቁሱ ተግባር ምን ነበር? ከሌሎቹ የተለየ ነበር? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የቁሶች ተግባር ምን እንደሆነ መመርመር ያሻል፡፡ ቁሶች ደግሞ ብዙ ተግባር አላቸው፡፡ ጥቂቱ ከሌላው በጣም ግልፅ ነው፡፡ የቁሱ መጀመሪያው ተግባር ዋና ስራ ሁሉም ባይሆን ጥቅም የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ወንበር የተሰራው ለመቀመጫነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወንበር ትእምርታዊ እሴት አለው፡፡ ይህም እንደ ዙፋን ማገልገሉ ነው፡፡ ወንበሩን እንደቁስ ካየነው የራሱ ዲዛይን፣ ማህበራዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለምሳሌ፣ በቤት ውስጥ ለማስጌጥ ይጠቅማል፡፡

ከአዲስ ቁስ ጋር በተገናኘን ጊዜ ከልምዳችን በመነሳት የቁሱን መሰረታዊ ተግባር ትክክለኛ ግምት ለመስጠት እንሞክራለን፡፡ ይህ ልምድ ምናልባት ስህተት ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይ ቁሱ የመጣው በርቀት ከጠፋ ባህል ወይም ቦታ እና ጊዜ ከሆነ በራሳችን አካባቢውን፣ የጠፋበትን ቦታና መነሻ መፈለግ አለብን፡፡ በተጨማሪ የሳንቲምን ተግባር ስንመለከት ገንዘብ ነክ ዝውውር ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም ትእምርታዊ እሴትነት ያለው ይመስላል፡፡ ይህም ከብሔራዊ ማንነት ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡ ሳንቲሞች የፕሬዝዳንቶች ወይም የገዢዎች ምስሎች የሚታይባቸው አሉ፡፡ እነዚህ ቁሶች በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ሊነግሩት ይችላሉ፡፡ ሳንቲምን ለንግድ የማይጠቀሙ ባህሎች የማህበረሰቡን ደረጃ ሊገልፁ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የሳንቲሙን የላይኛውን ክፍል ቀዳዳ በመብሳት የአንገት ላይ ጌጥ በማድረግ የሚጠቀሙ አሉ፡፡

ቁሱን ማን ሰራው? የቁሱ ባለቤት ማነው? ወይም ቁሱን የሚጠቀመው ማን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ቁሱን ማነው የሰራው? ወይም ማነው የሚጠቀምበት

የሚለው ትርጓሜ አስቸጋሪ ነው። ለምሳሌ የተፃፈ ምንጭ በሌለበት አሁን ያሉ የእደ ጥበብ ውጤቶች ማን እንደሰራቸው በቀጥታ የማይታወቁና እንዲህ ናቸው ብለን ልንገልፃቸው የማንችለው ቁሶች አሉ።

ቁሶችን በምንመዘግብበት ሂደት ውስጥ የምንጀምረው ማን ሰራው? ማነው ቁሱን የሚጠቀምበት ከሚለው መረጃ አቀባዮች ከሰጡት መረጃ በመነሳት ነው። ለምሳሌ ቁሱ ይታወቃል? በእጅ የተሰራ ነው? አጥኚዎቹ የተሰራበትን ቀን፣ የቁሱን ዋና ባለቤት ስም? ቁሱን የሰራው ሰው ስም እና የቁሱን የአሰራር ዘይቤ ስም ሰጥተውታል የሚሉት ጥያቄዎች ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለባቸው። ነገር ግን የእኛ ጥያቄ ማዕከል የሚያደርገው የቤተሰቡ ታሪክ ሚና ላይ ይሆናል። (እንደላይኛው)

### 2.1.4. ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሂደቶች

ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን የተለያዩ የመተንተኛ ሂደቶች በተለያዩ ምሁራን ተሰጥተዋል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ Prown ናቸው። እንደ Prown (1982,7) አገላለፅ ቁስን ለመተንተን የሚከተሉትን ሶስት ነገሮች መመልከት ያስፈልጋል።

እነርሱም 1. ገለፃ (Description) 2. ትርጓሜ (Deduction) 3. ጥቆማ (Speculation) ናቸው። Prown እነዚህን ነገሮች ሲያብራሩ

1. ገለፃ (Description) ይህ ተግባር ቁሱን ስንተነትን በቦታው ላልነበሩ ሰዎች ምስል በመከሰት የማቅረብ ዘዴን የሚያሳይ ነው። በገለፃ ወቅት የቁሱን ቅርፅ፣ ከምን እንደተሰራ፣ርዝመቱን፣ክብደቱንና መልኩን ማሳየት ሲኖርብን በገለፃ ጊዜ በዐይናችን የምናየቸው ነገሮች ማካተት እንዳለብን ይነግረናል።

2. ትርጓሜ(Deduction)ከገለፃው በማስተካከል የምንጠቀምበት የመተንተኛ ሂደት ነው። በዚህ ክፍል በቁሱና በቁሱ ባለቤት ማህበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት የምናይበት ሲሆን፣ ለምናየው ነገርም ትርጓሜ የምንሰጥበት ነው።

3. ጥቆማ(Speculation)ከላይ የተጠቀሱትን የገለፃና የትርጉም ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ የምንተገብረው ስራ ሲሆን በዚህ ክፍል አጥኚው የራሱን ግንዛቤ ከቀደምት ትውሮች ጋር በማገናዘብ ትንታኔ የሚሰጥበት ክፍል ነው።

### 2.1.5. ቁሳዊ ባህልን የመመደቢያ እና የመተንተኛ ሞዴሎች

Prown (1982:2) ምደባ በቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው 1 ቁሶቹ የተሰሩበት ጥሬ ዕቃን በመመልከት 2 ቁሶቹ የተሰሩበትን ዘዴ በመመልከት 3. የቁሶቹን አገልግሎት ምክንያት በማድረግ መመደብ ይቻላል በማለት ይልፀው የተለያዩ መስፈርቶች እንዳሉ ሁሉ ሁሉም ግን ችግር የማያጣቸው በመሆናቸው ከነዚህ መካከል አገልግሎትን መሰረት ያደረገ ምደባ የተሻለ መሆኑንን ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ ከሚጠቀሱ ሊቃውንት መካከል አንዱ የሆነው Schlereth (1980, http//www.btnep.org) አንድን የቁሳዊ ባህል ጥናት ለመተንተን የሚያመቹ ዘጠኝ ሞዴሎችን አስቀምጠዋል። ሞደሎቹንም በትንታኔው ወቅት አንድና ከአንድ በላይ ወስዶ መጠቀም እንደሚቻልም ገልፀዋል።

ከዘጠኙ ሞዴሎች መካከል የመጀመሪያው ጥበባዊነት (Art Historical) የሚባለው ነው። ይህ ሞዴል ቁሱ ጥበባዊ ባህሪን የተላበሰ መሆኑን የሚገመግም ሲሆን ባህሪውም በገለፃ ፍንትው ብሎ እንዲታይ የሚያደርግ ነው።

ሁለተኛው ሞዴል ተምሳሌታዊነት (symbolic) ነው። ይህ ሞዴል ቁሱ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ሚና ምን እንደሚመስል የምንፈትሽበት ሲሆን ቁሶቹ ከዘወትራዊ አገልግሎታቸው ውጭ አንድን ነገር ወክለው መቆማቸውን የምንገመግምበት ነው። በሶስተኛነት የምናገኘው ሞዴል ባህላዊነት (cultural) የተባለውን ነው። ይህ ሞዴል ቁሶቹ የአንድን ጉሳ ወይም ብሔር ማመልከታቸውን እና የቁሱ ባህሪያዊ እድገት ከማህበረሰቡ ባህል ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል ሞዴል ነው።

በአራተኛነት የተጠቀሰው አካባቢያዊነት (Environmental) ነው። ይህ ሞዴል የአንድ አካባቢ የተፈጥሮ አቀማመጥ በቁሶቹ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችለን ሞዴል ነው።

በአምስተኛነት ደግሞ ፋይዳዊነት (functionalist) የተባለውን ሞዴል እናገኛለን። ይህ ሞዴል ቁሱ አገልግሎት ላይ እንዴት እንደዋለና ምን ጥቅም እንደሚሰጥ እና ጥቅም

ሲሰጡ ቀድሞ ለታቀደው ተግባር ነው ወይስ ለሌላ ተግባር የሚለውን የምንፈትሽበት ነው።

በስድስተኛነት የምናገኘው መዋቅራዊነት (structuralist) የሚባለውን ሲሆን ቁሱ እንዴት ተሰራ? ከምን ተሰራ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት የምንጠቀምበት ሞዴል ነው። በዚህም ውስጥ ቁሱ የተሰራበት መሳሪያ ምን ምን እንደሆነ ምላሽ ለማግኘት የሚረዳ ሞዴል ነው። በሰባተኛነት የተጠቀሰው ሞዴል ባህሪ ጠቋሚነት (Behaviorist) የሚለው ነው። ይህ ሞዴል የቁሶቹ በአካባቢው መኖር በማህበረሰቡ ላይ ያሳደረው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖን የምንፈትሽበት የሞዴል ዓይነት ነው።

በስምንተኛነት ማህበረሰባዊነት (community) የሚለውን ሞዴል እናገኛለን። ይህ ሞዴል በማህበረሰቡና በቁሶቹ መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ነቅሰን በማውጣት ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያለው አመለካከት አንድ መሆኑን አልያም መለያየት ምክንያትን ለማወቅ የሚረዳ ሞዴል ነው።

በመጨረሻ የምናገኘው ሰሻል ሂስቶሪካል (social Historical) የተባለውን ሞዴል ሲሆን ይህ ሞዴል የቁሶቹ ባለቤት ማን እንደሆኑ፣ በማን ተሰሩ እና በየትኛው ዘመን ከየትኛው ማህበረሰብ ተገኙ ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት የሚያስችል ሞዴል ነው። (እንደላይኛው)

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

### 2.2.1. ያልታተሙ ጥናቶች

ይህንን ጥናት ለማጥናት ባደረኩት አሰሳ ከባህላዊ ቆዳ ስራ ጋር የተያያዙ አራት ጥናታዊ ፅሁፎችን ተመልክቼያለሁ፡፡ ሁሉም ጥናቶች የተካሄዱት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ነበር፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ካላቸው ጥናቶች ውስጥ የመጀመሪያ በ1999 ዓ.ም በሄለን አላምረው “ባህላዊ ሸመናና የቆዳ ሥራ በደንበጫና አካባቢዋ” በሚል ርዕስ የቀረበው የማስተርስ ዲግሪ ሟሟያ ጥናት ነው፡፡ አጥኚዋ በመግቢያዋ ላይ እንደጠቀሰችው ይህን ጥናት ለማጥናት የፈለገችበትን ምክንያት ለዘርፉ ትኩረት ስላልተሰጠውና ለታሪክ እንደቅርስነት የሚያገለግል ስራ ለመስራት ከማሰብ የመነጨ እንደሆነ ገልፃለች፡፡ አጥኚዋ አላማ አድርጋ የተነሳችው በአካባቢው የሚገኙ የሸመናና የቆዳ ስራ ባለሙያዎች በሥራቸው የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎችና የአሰራር ሂደቶች ማሳየት ሲሆን እንዲሁም የባለሙያዎቹን ማህበራዊ ሕይወት እና ስለነሱ የሚነገሩ ስነቃሎችን ይዘት ማመልከት እንደሆነ ትገልፃለች፡፡ አጥኚዋ በጥናቷ የቆዳ ሥራ ባለሙያዎች በሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች የመገለል አዝማሚያ እንደሚታይባቸው ገልፃለች፡፡

ሄለን ንድፈ ሃሳቦችን በጥናቷ ካገኘቻቸው መረጃዎች ጋር አዛምዳ ባለመተንተኗ ጥናቷ ክፍተት ይታይበታል፡፡ አጥኚዋ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመችው ምልከታ እና ቃለመጠይቅ ሲሆን ቡድን ተኮር ውይይት አላደረገችም፡፡ በዚህም የመረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የተጠቀመችበት መንገድ ባለመኖሩ ጥናቷ ክፍተት ይታይበታል፡፡ ይሁንና እነዚህን ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መጠቀሟ ለጥናቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሁለተኛነት ከኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የኔዓለም አረዶ በ2000 ዓ.ም “የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት (በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ወረዳ)” በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነፅሑፍ ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ሟሟያ ያቀረበችው ጥናት ሲሆን አጥኚዋ ዓላማ አድርጋ የተነሳችው የሴቶች የባህል አልባሳትና ጌጣጌጥን የቀድሞና የአሁን ይዞታ መመርመርና ያሉበትን ደረጃ ማሳየት ላይ ሲሆን ትኩረት

ያደረገችው በሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ ነው። የኔን ጥናት ከየኔዓለም ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች ማዕከል የደረጉት አርሲ ዞንን በመሆኑና አጥኚዋ ከቆዳ የሰሩ አልባሳትንና ጌጣጌጦችን በማንሳቷ ነው። የኔ ጥናት ከየኔዓለም የሚለየው ሙሉ በሙሉ ትኩረት ያደረገው በባህላዊ የቆዳ ቁሶች ላይ በመሆኑ ነው።

በሦስተኛነት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የታምራት ኃይሉ "የብራና መጻሕፍት አዘገጃጀት በደቡብ ጐንደር እስቴ ወረዳ" በሚል ርዕስ በ2000 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ሟሟያ ያቀረበው ጥናት ነው። ታምራት አላማ አድርጐ የተነሳው በወረዳው በሚዘጋጁ የብራና መጻሕፍት አዘገጃጀትን በመመልከት ሂደቱንና የማዘጋጃ ቁሶችን መግለፅና ቀርጾ በቅርስነት ማቆየት ላይ ሲሆን ጥናቱን ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ከባህላዊ የቆዳ ስራ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው የታምራትን ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው እሱ በፍየል ሌጦ ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ደግሞ በቀንድ ከብቶች በሚሰሩ የቆዳ ቁሶች ላይ በማተኮሩ ነው። ሌላው ይህ ጥናት የባህላዊ ቆዳ ቁሶችን የአሰራር ሂደት እና ጠቀሜታ በስፋት ስለሚተነትን ይለያል።

በአራተኛነት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው አበበ መርዕድ "በጐባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና" በሚል ርዕስ በ2000 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጥናት ነው። አጥኚው ዋና ዓላማ አድርጐ የተነሳው በጐባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ መመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳውን መግለፅ ነው።

ይህን ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው አጥኚው ከቆዳ የተሰሩ ቁሶችን በማንሳቱ ሲሆን ከቆዳ የተሰሩ ቁሶች ብሎ ያነሳቸው ሁለት ነገሮች ውስጥ ፍፁም የሚያመሳስለን የአገልግል አሰራርንና አገልግሎት በማንሳቱ ነው። ይሁንና አጥኚው ትኩረት ያደረገው በአጠቃላይ የመመገቢያ ቁሶች ላይ በመሆኑ ከኔ ጥናት ይለያል። የኔም ጥናት በዚህ ጥናት ውስጥ ያልተካተቱትን የባህላዊ ቆዳ ቁሶች ክፍተተ የሚሞላ ይሆናል።

በአጠቃላይ አራቱ የማስተርስ ዲግሪ ሟሟያ ጥናቶች ከባህላዊ ቆዳ ስራ ጋር ተያያዥነ
ያላቸው ቢሆኑም ይህ ጥናት በተለይ ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶችን ወስዶ ንድፌ ሀሳቦች
በመጠቀም ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማዛመድ ለመተንተን በመሞከሩ ል
ያደርገዋል፡፡

## 2.2.2. የታተሙ ጥናቶች

Gallagher, (1974, 176) ያቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነ
ካላቸው ስራዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ አጥኚው የድንጋይ መሳሪያዎችን ጥቅም
ባህላዊ የቆዳ ስራ አሰራር ሂደትን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ጥናት አሥራ ሁለት ሰዎች
ከስድስት የተለያዩ አካባቢዎች የወሰዱ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የጉራጌ፣ የሲዳሞ እ
የአሩሲ ይገኙበታል፡፡ በዚህ ፅሁፍ የቆዳ ሰራተኞቹ በተለምዶ "ፋቂ" ተብለ
እንደሚታወቁ እና ለቆዳ ስራ የሚያገለግሉ ቆዳዎችን የሚያገኙት ከአካባቢያቸ
እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

አጥኚው ቆዳው ተወጥሮ እስኪፋቅ ድረስ ከእርጥበት ለመከላከል ሰሪዎቹ የብሳና ቅጠ
እንደሚጠቀሙ ያስረዳሉ አያይዘውም የቆዳ ስራ በቤት ውስጥ ቢዘጋጅ ጥሩ እንደ
ይመክራሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የቆዳ ሰራተኛው በቆዳው ላይ ያለውን ትርፍ ስጋ ለማስወ
"ጉንዳን" በመባል የሚታወቀውን የእንጨት መፋቂያ መሳሪያ እንደሚጠቀም፣ ቆዳ
በማልፋት ሂደትም የሴቶች ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡
አጥኚው ቆዳ ለልብስ እና ለመኝታ በምንጣፍነት ማገልገሉ በአሩሲ እና በሲዳሞ ሴ
ዘንድ የሚዘወተር መሆኑንም ገልፀዋል፡፡

የቆዳ አቅርቦትን በተመለከተም አንደኛው ፈላጊዎቹ አሰሪው ቤት ድረስ ይ
በመምጣት የሚያሰሩ ሲሆን ሁለተኛው ሰሪዎቹ ቆዳውን ከገበያ በመግዛት መልሶ ለገ
የሚያቀርቡ መሆኑን አመልክተዋል፡፡
በጥናቱ ባለሙያዎቹ ከማህበረሰቡ የተገለሉ መሆናቸውን እና ባለሙያዎቹ ለልጆቻቸ
እውቀቱንና መስሪያ ቁሶቹንም የሚያወርሱ መሆኑን ይዘረዝራሉ፡፡ አጥ

በመጨረሻም የሙያው ቅብብሎሽ አደጋ ላይ መውደቁን ገልፀው ስጋታቸውን በጥናቱ አስፍረዋል፡፡ (እንደላይኛው)

ከታተሙ ፅሁፎች መካከል Pankhurst, (1964, 230-233) ያጠኑት ጥናት ሲሆን አጥኚው ይህ ስራ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ገልፀው ከቆዳ የሚሰሩ ነገሮችን በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ የቆዳ ስራ በተለያዩ አካባቢዎች እንደሚሰራ እና በተለይ በሸዋ የሞረት ሕዝቦች በዚህ ስራ የተካኑ እንደሆኑ በተጨማሪ ጐንደርም በዚህ ስራ ተጠቃሽ እንደሆነ አስፍረዋል፡፡, Pankhurst, Merab እና Ruppell ን ጠቅሰው የቆዳ ስራ በአድዋ ደሪታል እና አንታሎ እንደሚሰራ አስፍረዋል፡፡ በመቀጠል የቆዳ ስራ አዘገጃጀትን በተመለከተ ቆዳው ተወጥሮ በፀሐይ እንዲደርቅ መደረጉ፣ ለመወጠሪያነት ዙሪያውን ትንንሽ ቀዳዳዎች እንደሚሰሩለት እና ከመሬት በላይ ትንሽ ከፍ ተደርጐ እንደሚወጠር ገልፀዋል፡፡ የደረቀውን ቆዳ ለማለስለስ ደግሞ ሰሪዎቹ የረጋ ወተትና ዱቄት እንደሚጠቀሙ ፅፈዋል፡፡ (እንደላይኛው 231)

Pankhurst, Mereb ን ጠቅሰው ጥሬ ቆዳው ከሦስት እስከ አምስት ቀናት በውሃ ውስጥ እንደሚዘፈዘፍ እና ቆዳው ላይ ያሉት ነገሮችን በእጅና በመሳሪያዎች በመጠቀም እንደሚወገድ ጠቅሰዋል፡፡ አጥኚው የቆዳ ቦርሳ አዘገጃጀትንም በተመለከተ በዚህ ፅሁፋቸው አንስተዋል፡፡ ቆዳው ለስድስት እና ለሰባት ቀናት በእንስራ ውስጥ በከብቶች ሽንት እና በተበላሸ ፍራፍሬ እንደሚዘፈዘፍና ይህም የሚደረገው የቆዳው ፀጉር በቀላሉ እንዲለቅ ለማድረግ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ (እንደላይኛው 232)

በፅሑፉ በባህላዊው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ቆዳ በስፋት ጥቅም ላይ ይውል እንደነበር ተጠቅሷል፡፡ ለምሳሌ ቆዳ በጦርነት ጊዜ በተለያየ መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉ በፅሑፉ ተብራርቷል፡፡

## 3. የሽርካ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ

### 3.1. መልክአምድራዊ ገጽታ

የሽርካ ወረዳ በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ 180 ወረዳዎች፣ ከአርሲ ዞን ከሚገኙ 22 ወረዳዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ወረዳ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት፣ በአርሲ ዞን ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 265 ኪሎ ሜትር፣ ከዞኑ ዋና ከተማ ከአሰላ በስተደቡብ ምዕራብ 90 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ወረዳው በደቡብ የሸበሌ ወንዝ፣ የአርሲና የባሌን ዞን የሚለያያቸው ሲሆን በደቡብ ምዕራብ የበቆጂ ከተማ፣ በምዕራብ የዲገሉና ጢጆ ወረዳ፣ በሰሜን የጠና ወረዳ፣ በምስራቅ ደግሞ የሮቤ ወረዳ ያዋስነዋል፡፡ የወረዳው ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 1,156 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን በውስጡ 34 ቀበሌዎችን እና አንድ የከተማ አስተዳደርን ይዞዋል፡፡

የዚህ ወረዳ ከፍታ ከባህር ወለል በላይ 360 እስከ 1350 ሜትር ይደርሳል፡፡ በወረዳው ከሚገኙ ዋና ዋና ወንዞች መካከል የጉመሎ ወንዝና የረጰሳ ወንዝ በረዥም ጉዟቸው ይጠቀሳሉ፡፡ የአካባቢው የመሬት ጥናት እንደሚያመለክተው 21.4% ሰብል ለማምረት አመቺ ሲሆን 3.6% የሚሆነው ለግጦሽ፣ 2.7% የሚሆነው በደን የተሸፈነ እና ቀሪው 69.6% ደግሞ ሰብል ለማምረት የማያመች ተራራማና ጥቅም ላይ የማይውል መሬት ነው፡፡ በደንና በቁጥቋጦ በተሸፈነው የደን ክልል ውስጥ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር አራዊት እንደ ቀይ ቀበሮ እና የደጋ አጋዘን ይገኙበታል፡፡

በወረዳው ከሚመረቱ ምርቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ በርበሬ ጥቁርና ነጭ አዝሙድ ይገኙበታል፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ የተለያዩ አዝርዕቶች በተለያዩ የአየር ፀባይ እንደሚያበቅሉ ይገለፃል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ ባቄላ፣ አተር የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ ከቅባት እህሎች መካከል ተልባ፣ ኑግ የመሳሰሉትን ያበቅላል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ዲሪባ ሙለታ፣ የካቲት 18 ቀን 2004 ዓ.ም)

### 3.2. የመሰረተ ልማት አውታሮች

የሽርካ ወረዳ 77 ኪሎ ሜትር የበጋ መንገድ 22% ደግሞ የክረምት ከበጋ የሚያገለግል መንገድ ያለው ሲሆን፡፡ ከአጠቃላይ የወረዳው ሕዝብ 51% የሚሆነው የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ነው፡፡ ወረዳው በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ የዲጂታል እና የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚ ሲሆን 24 ሰዓት የኤሌትሪክ መብራት አገልግሎት እንዲሁም የፖስታ

አገልግሎት ተጠቃሚ ነው፡፡ ለተለያዩ ወረዳዎች አገልግሎት የሚሰጠው የኤሌትሪክ ማሰራጫ ጣቢያም በዚሁ ወረዳ ዋና ከተማ ጉቤሣ ላይ ይገኛል፡፡ ወረዳው በቅርቡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍን በመክፈቱ የባንክ አገልግሎትም ተጠቃሚ ሆኗል፡፡

የወረዳው ዋና ከተማ ጉቤሣ በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ከተማ ከባህር ጠለል በላይ በ2353 ሜትር ላይ ይገኛል፡፡ ከተማው በውስጥ ለውስጥ መንገድ ከመደሮ እና ከጨቆ ከተሞች ጋር ይገናኛል፡፡

በሽርካ ወረዳ ዘመናዊ ትምህርት በ1948 ዓ.ም በጉቤሣ ከተማ እንደተጀመረ ከወረዳው የትምህርት መረጃና ስታትስቲክ ሥራ ሂደት ፈፃሚ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በወረዳው ያለው የት/ቤቶች ቁጥር ከ1-8፣56 ት/ቤቶች ሲኖሩ ከ9-10፡ 2 ት/ቤቶች እና አንድ የመሰናዶ ት/ቤት ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በወረዳው ከ1-12 የተማሪዎች ቁጥር 35.920 መድረሱን ከወረዳው ጽ/ቤት በተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ጌታሁን ከበደ፣ ጥር 25 ቀን 2004)

በሽርካ ወረዳ የጤና አገልግሎት በጤና ጣቢያ ደረጃ በ1977 ዓ.ም በስዊድን መንግስት እርዳታ ሥራ እንደጀመረና ከዛ በፊት ግን በክኒሊክ ደረጃ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን የጤና ባለሙያው ይገልፃሉ፡፡ በአሁኑ ሰዓት በወረዳው 33 ጤና ኬላዎች ሲኖሩ 3 ጤና ጣቢያና ሁለት ግንባታቸው በመካሄድ ላይ ያሉ ጤና ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ፍቃዱ ነጋሣ፣ የካቲት 18 ቀን 2004 ዓ.ም)

## 3.3. የወረዳው ሕዝብና ሃይማኖት

በ2007 እ.ኤ.አ. የማዕከላዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ ባወጣው መረጃ መሰረት የወረዳው ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት 163,823 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 81,812 ወንዶች 82,011 ሴቶች ናቸው፡፡ በወረዳው ውስጥ ካለው ሕዝብ መካከል ኦሮሞ 71.83% አማራ 26.83% ሌሎች 1.34% ሲሆኑ ኦሮሚኛ ቋንቋ የሥራ ቋንቋ በመሆን 65.98% ሲሸፍን 33.9% የአማርኛ ቋንቋ ይነገራል፡፡ ቀሪው 0.11% ደግሞ ሌሎች ቋንቋዎች ይነገሩበታል፡፡ ከወረዳው ሕዝብ 45.52% የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ሲሆን 54.19% ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ በወረዳው ሌሎች እምነቶችም ይገኛሉ፡፡

## 3.4 የሕዝቡ መተዳደሪያ

በወረዳው ውስጥ ከሚገኘው ለሥራ ከደረሰው ሕዝብ መካከል ጥቂቱ በመንግስት ሥራ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሲሆን ከፊሉ በንግድ ስራ ላይ የተሰማራ እና አብዛኛው 90% የሚሸነፍነው ደግሞ በግብርና ስራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡

ከወረዳው ግብርና ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛው ሕዝብ በግብርና ሥራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡ በተጨማሪ ጐን ለጐን የከብት እርባታና የንብ ማነብ ሥራንም ይሰራል፡፡ በወረዳው የእርሻ ስራ በዓመት ሁለት ጊዜ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ወንዞችን በመጠቀም የመስኖ ስራ ይከናወናል፡፡ (ቃለመጠይቅ አቶ ዲሪባ ሙለታ የካቲት 18 ቀን 2004 ዓ.ም)

በተለይ የአርሲ ኦሮሞዎች መተዳደሪያ ከብት እርባታ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የቀንድ ከብቶች፣ በሬዎች፣ ወይፈኖች፣ በግ፣ ፍየል እንዲሁም የጋማ ከብቶች፣ ፈረስ /ባዝራ፣ ድንጉላ/፣ አህያ፣ በቅሎ ወ.ዘ.ተ ይገኙበታል፡፡

የወረዳው ዋነኛ ኢኮኖሚ ከእርሻ ቀጥሎ የከብት እርባታ ነው፡፡ ይሁንና እርባታው የሚካሄደው በኋላ ቀር ዘዴ ስለሆነ አጥጋቢ ውጤት አይታይም፡፡ በደጋው ክፍል የሚገኘው ደግሞ እርሻን የሚያዘወትር ሲሆን የሚያመርተውም በአብዛኛው ገብስ የተባለውን አዝዕርት ነው፡፡ በቆላማው ክፍል የሚገኘው ማህበረሰብ በተለይም ወጣቶች ከብቶችን በመጠበቅና በመንከባከብ የሚያገለግሉ ሲሆን ማህበረሰቡም የሚተዳደረው አብዛኛው በከብት እርባታ ነው፡፡

ከአካባቢው ሰፊ የእንስሳት ሃብት ውስጥ 205,015 የቀንድ ከብቶች፣ 48,356 በጎች እና 43,924 ፍየሎች በወረዳው እንደሚገኙ ከወረዳው ግብርና ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ (ቃለመጠይቅ እንደላይኛው)

## 4. የመረጃ ትንተና በሽርካ ወረዳ የቆዳ ቁሶች ስራ

በዚህ ክፍል የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ምን እንደሚመስል በምዕራፍ ሁለት ስር ከቀረቡ ንድፈ ሀሳባዊ መነሻዎች ጋር እየተመሳከሩ ትንታኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

### 4.1. የቆዳ ቁሶች አይነትና አገልግሎት

በዚህ ርዕስ ስር ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች አይነትና አገልግሎት ለመኝታነት የሚያገለግሉ፣ የግብርና መገልገያ ቁሶች ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውሉ ቁሶች እና ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች በሚል ቀርበዋል፡፡ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡

#### 4.1.1. ለመኝታነት የሚያገለግሉ ቁሶች

##### 4.1.1.1. ነት

ነት፣ ከከብት ቆዳ የሚሰራ ሲሆን ለነት መስሪያነት የሚያገለግለው ቆዳ የሚገኘው ከልኳንዳ ቤቶች፣ ቤት ውስጥ ከታረደ ከብት፣ በየቤቱ እና ከገበያ ላይ በመግዛት ይሰበሰባል፡፡ ነት፣ የቆዳውን ፀጉር ሙልጭ አድርጐ በማንሳት በሁለቱም ፊት ንፁህ ቆዳ ያለው ለስላሳ ቆዳ ነው፡፡ ነት፣ እንደ ብራና ሁሉ በላዩ ላይ የተለያዩ ዲዛይኖችን በማሳረፍ ለጌጥነት የሚያገለግል ከቆዳ የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ነት፣ ለክብር መግለጫ የሚነጠፍ መሆኑን መረጃ አቀባዩ አቶ ስለሺ *"ነት የከብቱ ቆዳ ፀጉር ሙልጭ ብሎ ከተነሣ በኋላ የተለያዩ ዲዛይኖች ተቀርፀውበት ልክ እንደ አበባ ምንጣፍ በመደብ፣ በድንክ አልጋ ላይ የሚነጠፍ ቁስ ነው፡፡ ነት የሚነጠፈው በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ናቸው ለሚባሉ ሰዎች ነው፡፡"* በማለት ገልፀውልኛል፡፡ *(ቃለመጠይቅ ስለሺ ተስፋዬ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*



ስዕል 1 አቶ ከበደ ነት ይዘው ሲሄዱ

*የነት አሰራር ሂደት*

በመጀመሪያ የደረቀው ቆዳ በከብት ሽንት ውስጥ ከሶስት እስከ አምስት ቀን ድረስ ይዘፈዘፋል። ከዚያም ዙሪያውን ቀዳዳ (ቅፍንድ) ይበጅለትና በእንጨት ችካል ከመሬት ትንሽ ከፍ ተደርጐ ይወጠራል። በዚህ ሁኔታ ለአንድ ቀን ያህል ፀሐይ እንዲመታው ከተደረገ በኋላ ውሃ እየተርከፈከፈበት ከብቱ ሲገፈፍ በላዩ ላይ የቀረውን ስጋ (ደደብ) በቢላዋ ወይም በመጥረቢያ እንዲገፈፍ ይደረጋል። ከዚያም በቢላዋ (መጥረቢያ) በመጠቀም የውስጡ ክፍል ይፋቃል። በመቀጠል ቆዳው ተገለብጦ ይወጠርና ስለት ባለው መጥረቢያ ፀጉሩ ሙልጭ ብሎ እስኪለቅ ድረስ ይፋቃል። በዚህ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ከተረፈ ስጋው (ደደብ) እና ከቆዳው ፀጉር ነፃ የሆነው ቆዳ እንዲለሰልስ ተወቅጦ፣ በውሃ ተበጥብጦ፣ ፀሐይ ላይ እንዲቦካ የተደረገው የጉሎ ፍሬ በሁለቱም በኩል እየተገላበጠ ይቀባል። ቆዳው በደንብ መለስለሱ እንደተረጋገጠ በዙሪያው ላይ ቆዳውን ለመወጠር የተቀደዱት ቀዳዳዎች (ቅፍንዶች) ስለት ባለው ቢላዋ በጥንቃቄ ይወገዳሉ። እንደ አስፈላጊነቱ የተለያዩ ዲዛይኖችን ላዩ ላይ በመቅረፅ ውበት እንዲኖረው ማድረግ እንደሚቻል ባለሙያዎቹ ሲገልፁ፣ አሁን ግን ከገበያው ውድነት አኳያ ዝም ብለው ባዶውን ነት እንደሚታዘዙ ገልፀዋል። ነት በአሁኑ ጊዜ በአበባ ምንጣፍ እየተተካ ይገኛል።

የነትን አገልገሎት አንዱ መረጃ አቀበይ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡

> *በባህላዊ መንገድ የሚጋቡ ሙሽሮች ወንዱ ሙሽራ ሴቷን ሙሽራ ከቤቷ ይዟት ሊወጣ ሲል ዘመድ አዝማድ ተደርድሮ ይቀመጣል። ሙሽራውና ሙሽሪትም ከነሱ ትይዩ መሬት ላይ በተነጠፈ ነት ይቀመጡና ይመረቃሉ። በዚህን ጊዜ በብርጭቆ ወተት ይሰጣቸውና ይጠጣሉ። በመጨረሻም ነቱንም ብርጭቆውንም ይዘው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ። (ቃለመጠይቅ አፈወርቅ ጋረዴ፣ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ከዚህ የምንረዳው ነት የማህበረሰቡን ማህበራዊ ደረጃ እንደማሳየነት እንደሚጠቅም ነው። ለምሳሌ ያህል ነት የሚነጠፍላቸው ሰዎች "የተከበሩ" የሚባሉ ዓይነት ናቸው። በማህበረሰቡ ዘንድ ሙሽራም ከነዚህ ውስጥ የሚመደብ በመሆኑ የነት ጠቀሜታ ከክብር ጋር የተያያዘ መሆኑ ይታያል።

የዚህን ቁስ ጥበባዊነት ስንመለከት በማህበረሰቡ ዘንድ በቆዳው ላይ የተለያዩ ዲዛይኖችን የማስፈር ልማድ ይታያል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አቶ አፈወርቅን ጠይቂአቸው የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

> *በለሰለሰው ነት ላይ ከተለያዩ ቅጠላ ቅጠል እና አፈር በተቀመመ ቀለሞች የተለያዩ ስዕሎች ይሳልበታል የክርስትና እምነት ተከታይ መስቀል፣ የእስልምና እምነት ተከታይ የግማሽ ጨረቃ እና አንድ ኮከብ እንዲሁም የአንበሳ፣ የአበባ ስዕል የመሳሰሉትን ያስቀርፅበታል፡፡ /ቃለ መጠይቅ አቶ አፈወርቅ ጋረዴ ጥቅምት 10 ቀን 2005 ዓ.ም/*

የዚህን ቁስ ተምሳሌታዊነት ስንመለከት፣ ነት በተለምዶ ለመኝታና ለመቀመጫ እንዲያገለግል ተደርጐ የተሰራ ሲሆን በፍካሬያዊ ፍችው ግን የክብር መገለጫ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ በዚህም ቁስ አማካይነት አስተናግጁ ያለውን ክብር የሚገልፅበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ “ተራ” የሆነ ሰው በእንግድነት ወደ ማህበረሰቡ ቤት ሲመጣ ደላጐ የተባለ የቁርበት እላቂ ሲነጠፍለት፣ “ለተከበረው” እንግዳ ግን ነት ይነጠፍለታል፡፡ ይህም የሚያሳየው ቁሱ በግለሰቦች የማህበራዊ ደረጃ ላይ የልዩነት ማሳያ መሆኑን ነው፡፡

ነት በአሁኑ ጊዜ በአበባ ምንጣፍና በአንሶላ እየተተካ ነው፡፡ ይህም የፋብሪካ ውጤቶች በባህላዊ ቁሶቹ ላይ በማምጣት ላይ ያሉትን ተፅዕኖ ያመለክታል፡፡

የዚህን ቁስ መዋቅራዊነት ስንመለከት ቁሱ የተሰራው ከቆዳ ሲሆን አሰራሩም በነት የአሰራር ሂደት ውስጥ እንደጠቀሰው ነው፡፡

### 4.1.1.2. ጀባ



ስዕል 2 ጀባ

*ጀባ-* ከከብት ቆዳ የሚሰራ ሆኖ እንደ ነት ፀጉር አልባ ያልሆነ በአንድ ፊት ብቻ ፀጉሩ ሳይነካ የለሰለሰ ቆዳ ነው። እንደ መረጃ አቀባዩ አቶ ስለሺ ተስፋዬ አገላለፅ *"ጀባ መልክ ያለው የከብት ቆዳ ተመርጦ ከነፀጉሩ ለጌጥ እንዲሁም ለመኝታነት የሚያገለግል ቁስ ነው።" (ቃለመጠይቅ ስለሺ ተስፋዬ የካቲት 1ቀን2004 ዓ.ም)*

ይህ ቁስ በመኝታ ጊዜ ፀጉሩ ሙቀት በመፍጠር ስለሚያገለግል ተፈላጊ ነው። አቶ ዘገዬ ወልዴም ይህን ሲያብራሩ *"ጀባ ማለት ከነጠጉሩ ነው። ለመኝታ እንዳይቀዘቅዝ ጀባው ይሰራል።" (ቃለመጠይቅ ዘገዬ ወልዴ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)* ጀባ ለመስሪያነት የሚያገለግለው የከብቶች ቆዳ በአብዛኛው የተዥጎረጎረ መልክ ያላቸው ከብቶች ቆዳ ነው። በአንድ በኩል ለመኝታነት ሲያገለግል በሌላ በኩል ደግሞ ለጌጥነት ያገለግላል።

አንዳንድ ጊዜ መልክ ያለው ከብት ለቅርጫ በሚታረድበት ጊዜ የከብቱ ባለቤት ቆዳውን እኔ ልግዛው የበሬዬ ማስታወሻ ነው በሚል የሚወስድበት አጋጣሚ አለ። ይህም ከከብቱ ጋር የነበረውን ፍቅር መግለጫ ተደርጐም ይወሰዳል።

*የጀባ አሰራር ሂደት*

እንደ መረጃ አቀባይ አቶ ንብረት እንዳለው ገለባ በመጀመሪያ የደረቀው ቆዳ በውሃ ውስጥ ከአንድ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ይዘፈዘፋል፡፡ ከዚያም ዙሪያውን ቀዳዳ (ቅፍንድ) ይበጅለትና በእንጨት ችካል ከመሬት ትንሽ ከፍ ተደርጐ ይወጠራል፡፡ በዚህ ሁኔታ ለአንድ ቀን ያህል በፀሐይ ሙቀት እንዲደርቅ ከተደረገ በኋላ ውሃ እያርከፈከፉ በውስጥ በኩል ተረፈ ስጋውን (ደደብ) በቢላዋ ወይም በመጥረቢያ ቆዳው እንዳይቀደድ ጥንቃቄ በማድረግ መፋቅ ነው፡፡ ቆዳው በደንብ ተደርጐ ከተፋቀ በኋላ ተወቅጦና በውሃ ተበጥብጦ ፀሐይ ላይ እንዲቦካ በተደረገው ጉሎ አማካይነት እየቀቡ የቆዳውን ልስላሴ መጠበቅ ነው፡፡

በዚህ መልክ የተዘጋጀው ጀባ እንግዳ ሲመጣ ለመኝታነት ከማገልገሉም በላይ ባለቤቱ በመደበኛነት ለመኝታ ይጠቀምበታል፡፡ አሁን አሁን ይህ ቁስ በአንሶላ እየተተካ ይገኛል፡፡ *(ቃለመጠይቅ አቶ ንብረት እንዳለ ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም)*

4.1.1.3. የጠፍር አልጋ /ድንክ/



ስዕል 3 ድንክ




ስዕል 4 የጠፍር አልጋ

በጥንት ጊዜ እንደዛሬው ዘመናዊ አልጋዎች ባልተሰሩበት ወቅት የሰው ልጅ ከራሱ ሀገራዊ ጥበብ በመነሳት ከጠፍር አልጋዎችን /ድንኮችን/ በመስራት ለመኝታነት ሲጠቀምባቸው እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን በእንጦጦ ሙዚየም የሚገኘው የዳግማዊ ምንሊክ ከጠፍር የተሰራ የመኝታ አልጋ ነው፡፡

## የጠፍር አልጋ አሰራር ሂደት


በመጀመሪያ አራት እግሮች ያላቸው እንጨቶች ቅርፅ ወጥቶላቸው ቀዳዳ ተበጅቶላቸው ይሰራሉ፡፡ እነዚህም እግሮች ጫፋቸው ሹል በሆኑ አግዳሚዎች እንዲያያዙ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በነት አሰራር ሂደት ላይ እንደተመለከትነው ሂደቱ ሲጠናቀቅ በጥንቃቄ ቆዳው ልክ እንደመጫኛ ይተለተላል፡፡ ከዚያም እግሮቹን የሚያያይዘው አግዳሚ እንዳይወልቅ በማድረግ ከማዕዘን ጀምሮ በደንብ ከተያያዘ በኋላ ድርና ማግ እያደረጉ በተጋደመው እንጨት ላይ መወጠር ነው፡፡ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች እንደነገሩኝ ይህንን ሙያ አብዛኛው ሰው በመልመዱ የድንክ መወጠርን ስራ በየቤቱ ራሳቸው ባለቤቶቹ ሲሰሩት ይስተዋላል፡፡ (ቃለመጠይቅ ስለሺ ተስፋዬ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)

### 4.1.2. የግብርና መገልገያ ቁሶች




ስዕል 5 ባህላዊ የግብርና መሳሪያ

4.1.2.1. ምራን



ስዕል 6. ምራን

ከቆዳ በባህላዊ መንገድ ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ምራን ነው። ይህን በተመለከተ አቶ ጌቱ ተፈራ "ምራን ለእርሻ ስራ ከሚያገለግሉ ቁሶች መካከል አንዱ ነው። ምራን የሚዘጋጀው ከበሬው የግንባር ቆዳ ላይ ነው። ቆዳው ተጒንጒኖ በቀንበሩ መሃል ላይ ይደረግና ቀንበሩንና ሞፈሩን ያገናኛል።" ብለውኛል። (ቃለመጠይቅ አቶ ጌቱ ተፈራ የካቲት 2 ቀን 2004 ዓ.ም)

ምራን ቆዳው በቀጭኑ ይተለተልና በበሬው ቅልጥም በደንብ ከታሸ በኋላ ተጒንጒኖ ለግብርና አገልግሎት ከሚውሉ የቆዳ ቁሶች መካከል አንዱ ይሆናል። ቅልጥሙም የሚያገለግለው ቆዳው እንዳይበጣጠስ ስለሚረዳው እንደሆነ ከመረጃ አቀባዩ ለመረዳት ተችሏል። ይህ ቁስ በአሁኑ ጊዜ ከማዳበሪያ በተሰራ ገመድ እየተተካ ይገኛል።

4.1.2.2. መርገጥ

እንደምራን ሁሉ ከቆዳ በባህላዊ መንገድ ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ መርገጥ ነው። ስለመርገጥ አቶ ጌቱ ተፈራ እንዲህ ይላሉ፦

> *ለእርሻ ስራ ከሚያስፈልጉ ቁሶች መካከል አንዱ መርገጥ ነው። ከቆዳ ነው የሚሰራው። እንደ ጠፍር በረጅሙ ከተተለተለ በኋላ እርፉን፣ ድግሩንና ወገሉን በማገናኘት ሞፈሩ የእርሻ ተግባሩን እንዲፈፅም የምንጠቀምበት ነው። (ቃለመጠይቅ ጌቱ ተፈራ የካቲት 2 ቀን 2004 ዓ.ም)*

#### 4.1.2.3. ማርገቢያ-


ከበሬ ግንባር ቆዳ ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ቁስ በተለይ በውቂያ ላይ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህንንም ቁስ አቶ ጌቱ ተፈራ፡፡

> *"ማርገቢያ የሚባለው ከበሬ ቆዳ የሚሰራ ሲሆን የበሬው ቆዳ በልኩ ተቆርጦ መሀከሉ ላይ እጀታ ከገባለት በኋላ እንዲደርቅ በማድረግ በተለይ በጤፍ ምርት ወቅት እብቁን ከምርቱ ለመለየት የምንጠቀምበት መሣሪያ ነው፡፡" በማለት ይገልፁታል፡፡ (ቃለመጠይቅ ጌቱ ተፈራ የካቲት 2 ቀን 2004 ዓ.ም)*

የዚህን ቁስ አሰራር ስንመለከት በመጀመሪያ ከበሬው ግንባር ላይ ቆዳው ይገፈፍና በእርጥቡ ዙሪያውን ትንንሽ ቀዳዳ ተበጅቶለት ከመሬት ትንሽ ከፍ ተደርጐ ይወጠራል፡፡ ቆዳው እንዲደርቅ ፀሐይ ላይ ከቆየ በኋላ ከእንጨት እጀታ ተበጅቶለት ከቆዳው ጋር በጠፍር እንዲሰፋ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ያ ተወጥሮ የደረቀው ቆዳ ልክ እንደ ሰፌድ ሲያራግቡበት ምርቱን ከግርዱ ለመለየት ያገለግላል፡፡ በማርገቢያ የአሰራር ሂደት ቆዳው በደንብ መፋቅ የለበትም ምክንያቱም ከሳሳ በደንብ ማራገብ ስለማይችል ነው፡፡ ሌላው ማለሰለሻ ነገሮች አይቀቡም ያም የሆነበት ምክንያት ቆዳው እንደደረቀ ሳይተጣጠፍ ማገልገል እንዲችል ነው፡፡

#### 4.1.2.4. መጫኛ፡-

ከቆዳ ተተልትለው ከሚሰሩ የቆዳ ቁሶች መካከል አንዱ መጫኛ ነው፡፡ ለመጫኛ መስሪያ የሚሆነው ወፍራም የበሬ ቆዳ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መጫኛው አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ እንዳይበጠስ ስለሚረዳው ነው፡፡



ስዕል 7. መጫኛ



ስዕል 8. መረጃ አቀባዩ መጫኛ ይዘው

የመጫኛ የአሰራር ሂደት


በመጀመሪያ ቆዳው በውሃ ውስጥ ከተዘፈዘፈ በኋላ በችካል ተወጥሮ ፀጉሩ እና ተረፈ ስጋው ከላዩ ላይ ይነሳል፡፡ ከዚያም በቦካ ጉሎ ፀሐይ ላይ እንዳለ ይቀባና በደንብ ሲለሰልስ እንደገና በእግር በደንብ ተደርጦ ይለፋል ከዚያም በልክ እየተለካ ይቆረጣል፡፡ ከዚያም በጅማት እየተያያዘ ይሰፋል፡፡ አንድ የትልቅ በሬ ቆዳ ከአራት እስከ ስድስት መጫኛ እንደሚወጣው ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡ መጫኛው የበለጠ ጥንካሬ እንዲያገኝ ከበሬው ቅልጥም የሚገኘው መቅኒ ይቀቡታል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ሞራ ይቀቡታል ባለሙያው የመቅኒውንና የሞራውን ልዩነተ ሲያብራሩ መቅኒው የበለጠ እንዲጠናከር ሲያደርገው ሞራው ግን ለጊዜው ነው እንጂ ብዙም አይጠቅምም በማለት ይናገራሉ፡፡

የመጫኛ አገልግሎት፡- በገጠር አካባቢ የተለያዩ ነገሮችን በአህያ፣ በበቅሎ እንዲሁም በፈረስ ለመጫን ያገለግላል፡፡ አጫጫኑም የራሱ የሆነ ዘዴ ያለው ሲሆን የሚጫነውም በሁለት ሰዎች አማካይነት ነው፡፡ አንዱ ከወዲህ ሌላኛው ከወዲያ ሆነው በመሳብ ሲጭኑ የእንሰሳው ጭራ ስር የሚውል "ውዴላ" በመባል የሚታወቅ ትንሽ ቋጠሮም ይኖረዋል፡፡ ይህም ቦታ መጫኛው የከብቱን ጭራ እንዳይጐዳው በማለት በጨርቅ ይጠቅልሉታል፡፡ የአንድ መጫኛ ርዝመትም እስከ ሦስት ሜትር እንደሚደርስ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡ በዋጋ ደረጃም አንድ መጫኛ እስከ ሃምሳ ብር ያወጣል፡፡

የዚህን ቁስ ባህላዊነት ስንመለከት ቁሱ ዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎት ባልተሳፋፋባቸው ቦታዎች እቃን በጋማ ከብቶች ለማጓጓዝ ዕቃው እንዳይወድቅ ለማሰሪያ የምንጠቀምበት ሆኖ እናገኛዋለን፡፡ ይህም በባህላዊ መንገድ እቃን ማጓጓዣ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የዚህ ቁስ ተጠቃሚ ማህበረሰብ በገጠር አካባቢ የሚኖር እንደሆነ ቁሱ ይጠቁማል፡፡

የዚህን ቁስ ፋይዳ ስንመለከት ደግሞ የሚሰጠው ጥቅም በጋማ ከብቱ ላይ የሚጫነው ነገር እንዳይወድቅ አጥብቆ መያዣ ነው፡፡ ቁሱ ከጅምሩ ሲሰራ ለታሰበለት ነገር አሁንም ድረስ ሳይለወጥ ሲያገለግል ይታያል፡፡

#### 4.1.2.5. እጅ ቤዛ



ስዕል 9. እጅ ቤዛ

የእጅ ቤዛን አገልግሎት አቶ ፈለቀ ተስፋዬ *"እጅ ቤዛ እጅን በስራ ወቅት ከተለያዩ አደጋዎች ለመከላከል በእጅ ላይ የሚጠለቅ መከላከያ ነው። ለምሳሌ ነዶ ሲጋዝ፣ በከብት ጭነት ሲጫንና ለመሳሰሉት ስራ እንጠቀምበታለን።" በማለት ነግረውኛል። (ቃለመጠይቅ ፈለቀ ተስፋዬ የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም)*

የእጅ ቤዛ የአሰራር ሂደት፡- እጅ ቤዛ በመጀመሪያ በደንብ የተለፋ ወፍራም ቆዳ ይዘጋጅና ከግራ ጐኑ ላይ ወፍራሙ ቆዳ በክንድ ልክ ተቀርጦ የሚሰራ ነው። እጅ ቤዛ ሲዘጋጅ ሙቀት እንዳይፈጥር በጌጥ አልፎ አልፎ ቀዳዳ ይበሳለታል።

#### 4.1.2.6. ገምባሌ

ገምባሌ እንደ እጅ ቤዛ ሁሉ እግር ብር እንዳይወጋው ለመከላከል በደንብ ከተለፋ ወፍራም የበሬ ቆዳ የሚሰራ ነው።

የገምባሌ የአሰራር ሂደት፡- ገምባሌው በመጀመሪያ በደንብ የተለፋ ወፍራም ቆዳ አዘጋጅቶ ከግራ ጐኑ ላይ ወፍራሙ ቆዳ በእግር ባት ልክ ተለክቶ የሚቀረፅና የሚሰራ ነው። እንደ እጅቤዛ ሁሉ ገምባሌም ሙቀት እንዳይፈጥር በጌጥ ቀዳዳዎች ይበጅለታል። (ቃመጠይቅ ፈለቀ ተስፋዬ የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም)

#### 4.1.2.7. ዛብ

ከጠፍር ከሚሰሩ የቆዳ ቁሶች መካከል አንዱ ነው። ዛብ በቀጭኑ ከተተለተለ የከብት ቆዳ ከተዘጋጀ በኋላ በደንብ ተጉንጉኖ የሚሰራ ሲሆን አገልግሎቱም ከባድ የሆኑ ነገሮችን ለመጐተት ይሁን ለማንሳት ልክ እንደ ዘመኑ "ካቦ" የሚያገለግል ቁስ ነው። ይህ ቁስ በአሁን ጊዜ ከማዳበሪያ በሚገመዱ ገመዶች እየተተካ ይገኛል።

### 4.1.3. ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውሉ ቁሶች

ከስፌት የሚሰሩ ቁሶች ለረዥም ጊዜ ለማገልገል አይችሉም። ምክንያቱም የሚሰራበት ቁስ ሳር በመሆኑ ቶሎ የመበላሸት ነገር ይታይበታል። ይህንንም ዕድሜ ለማራዘም የስፌቱን የተለያየ ክፍል በቆዳ በመለጐም ቁሱን ረጅም ጊዜ እንዲያገለግል ማድረግ ይቻላል። በተጨማሪም ቁሱን ለማስጌጪያነት ይጠቅማል።


#### 4.1.3.1. አገልግል

የአገልግል ዓይነቶችን ከስንደዶ የሚሰሩና በቆዳ የተለበጡ በሚል በሁለት ክፍለን ልናያቸው እንችላለን። ከስንደዶ የሚሰራው የአገልግል አይነት የስፌት ባለሙያዋ እንደፈላጊው መጠን አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ትልቅ አድርጋ በተለያዩ ዲዛይን አለላን (ባለቀለም ስንደዶን) በመጠቀም የምታዘጋጀው የአገልግል ዓይነት ነው። ይህ አይነቱ አገልግል እርጥበት በሚያገኘው ጊዜ ስለሚበጣጠስ ዕድሜው አጭር ነው። በዚህ ጥናት በዋናነት የምንመለከተው ከስንደዶ ተሰርቶ ላዩን በቆዳ የሚለበጠውን የአገልግል አይነት ነው። ይህ አይነቱ አገልግል በእውቅ ስፌት ባለሙያ አልያም ከገበያ ላይ በመግዛት ለቆዳ ሰሪ ባለሙያዎች በመስጠት እንዲለበጥ የሚደረገው የአገልግል ዓይነት ነው።

እንደ መረጃ አቀባዩ አቶ ንብረት እንዳለው ገለፃ ለዚህ ስራ የሚሆነው ቆዳ የላም ቆዳ ነው። ምክንያቱም የላም ቆዳ ስስ በመሆኑ በቀላሉ ለፍቶ ሳያስቸግር አገልግል የመለጐም ስራውን ስለሚያቀላጥፍ እንደሆነ ይናገራሉ። የዚህ ጥናት አቅራቢም በታህሳስ ወር 2004 ዓ.ም መገባደጃ ላይ በሸርካ ወረዳ ጐቤሳ ከተማ በተፈጥሮ መቼቱ ላይ ተገኝቶ እንደተመለከተው ባለሙያዎቹ ሰፊውን የላም ቆዳ በአገልግሉ እየላኩ ሲቆርጡና አገልግል የመለጐሙን ሥራ ሲያከናውኑ ለመመልከት ችሏል።



ስዕል 10. የተለጎሙ አገልግሎች



ስዕል 11. አገልግል

## የአገልግል አሰራር ሂደት

በመጀመሪያ በስንደዶ የተሰራው አገልግል በባለሙያዋ ተሰርቶ ይመጣል፡፡ ከዚያም ቆዳው ለሦስት ቀን ያህል በውሃ ከተዘፈዘፈ በኋላ ዙሪያውን ለመወጠሪያ የሚያገለግል ቀዳዳ (ቅፍንድ) ይወጣለትና በችካል ይወጠራል፡፡ የተወጠረው ቆዳ በፀሐይ ሙቀት አማካይነት እንዲደርቅ ከተደረገ በኋላ በጣም እንዳይቀረፍድ ውሃ በትንንሹ እየተርከፈከፈ በቆዳው ላይ የቀረ ስጋ (ደደብ) በቢላዋ ወይም በመጥረቢያ በጥንቃቄ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ቆዳውን በመገልበጥ በፀጉሩ በኩል በስለታም መጥረቢያ ፀጉሩ እንዲላጭ ይደረጋል፡፡ ባለሙያዎቹ የቆዳውን ፀጉር ለማስለቀቅ የተለያዩ ዘዴዎችን እንደሚጠቀሙም ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ የከብት ሽንት በእንስራ በማጠራቀም ቆዳውን እዛ ውስጥ በመዘፍዘፍ ፀጉሩ በቀላሉ እንዲለቅ ማደረግ እንደሚቻል ይናገራሉ፡፡

በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ በሌሎች አካባቢዎች የሚጠቀሙበትን ኖራና አመድ ባይጠቀሙበትም ቆዳውን ለማስለቀቅ የከብት ሽንት እንደሚጠቀሙ በመስክ ጉብኝት ለመመልከት ተችሏል፡፡

በመቀጠል የቆዳው ፀጉር ሙልጭ ብሎ ከተነሳ በኋላ ቆዳው እንዲለሰልስ ጉሎ የተባለ ቅባትነት ያለው ፍሬ ተወቅጦና ተበጥብጦ እንዲቦካ ከተደረገ በኋላ በላዩ ላይ እንዲቀባ ይደረጋል፡፡ ይህም ዘዴ ቆዳው እንደተፈለገው እንዲተጣጠፍና እንዳይቀረፍድ ይረዳዋል፡፡ ቆዳው በዚህ መልኩ ከተዘጋጀ በኋላ ስለት ባለው ቢላዋ አገልግሉ እየተለካ (ከንፈሩ እንዳያጥር በጥንቃቄ እየተለካ) ይቆረጣል፡፡ በዚህ ጊዜ መክደኛውም ሆነ እናት አገልግሉ ለላይኛው ሽፋናቸው የሚሆን ቆዳ ይቆረጣል፡፡ የአገልግሉ የውስጠኛው ክፍል ግን በቆዳ አይለበጥም፡፡ የአገልግል መለጉም ዋና አላማው የአገልግሎት ዕድሜ ለማራዘም ሲባል ከውጭ የሚደርስበትን ጥቃት ለመከላከል ስለሆነ ትኩረት የሚደረገው በላይኛው ክፍል

ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ የውስጠኛው ክፍል ምግብ መያዣ እንደመሆኑ በቆዳ አይለበጥም፡፡ ዋና ምክንያቱም የምግቡን ይዘት ይቀይረዋል በሚል እንደሆነ መረጃ አቀባዩ ይገልፃሉ፡፡

በዚህ ወረዳ አገልግል የሚሰፉት ሴቶች ሲሆኑ አገልግል የሚለጉሙት ግን ወንዶቹ ናቸው፡፡ አጥኚው በታህሳስ ወር 2004 ዓ.ም መጨረሻ በጉመሳ ከተማ ላይ አቶ ንብረት እንዳለ ሲሰሩ እንደተመለከተው አገልግሉ ሲለጉም ቆዳው እንዳይሸበሸብ በሁለት ወስፌዎች ዳርና ዳር ተወጥሮ እንደሚያዝ ተመልክቷል፡፡ ከዚያም በአገልግሉ ላይ ለብሶ ዳርና ዳር የተወጠረው ቆዳ በቀጭን ከቆዳ በተተለተለ ጠፍር (ሲር) በሹል ወስፌ እየተበሳ እና በቀዳዳው እየተሾለከ ውበት ባለው መልኩ ይሰፋል፡፡ የመስፊያ ቁስን በተመለከተ አቶ ንብረት እንዳለ ሁለት አይነት የመስፊያ ቁስ እንደሚጠቀሙ ይገልፃሉ፡፡ አንደኛው ራሱ የቆዳው ትልታይ ቀጫጭን ጠፍር ሲሆን ሌላው ደግሞ ከፋብሪካ የተመረተ "ሲር" የተባለ ጠፍር መሰል ነገር ይጠቀማሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ባለቤቱ በጠፍር ወይም "በሲር" ይሰራልኝ ብሎ ሲያዛቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከባህላዊው ቴክኖሎጂ ጋር ተቀላቅሎ እየተሰራበት እንደሆነ ነው፡፡

ይህ ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ በመክደኛው እናት በኩል ጠንካራ ጠፍር ዙሪያውን ይሰፋበታል፡፡ ይህም አገልግሉን ለመክደን ጠፍሩን ለመጥለፍ እንዲያገለግል ስለማረዳው ነው፡፡ በእናት አገልግሉ ዙሪያ ደግሞ የተለያዩ ጥብጣቦች ይሰፋሉ፡፡ የነዚህ ጥብጣቦች አገልግሎት እናት አገልግሉንና ክዳኑን በማያያዝ አገልግሉ በደንብ እንዲገጥም ለማድረግ ነው፡፡ በጐንና በጐን ደግሞ ለማንገቻ የሚሆን ሰፋ ያለ ጠፍር ይሰፋበታል፡፡ ይህም በጉዞ ላይ ተንገቹ እንደልቡ አንግቶ እንዲቀሳቀስ እንዲያስችለው ነው፡፡


የዚህን ቁስ አገልግሎት ስንመለከት በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ላይ በግብርና ስራ የተሰማሩ ሰዎች ወደ እርሻ ቦታ ምግብ ለመውሰጃ ሲያገለግል፣ ከብት በመጠበቅ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችም ስንቃቸውን የሚይዙበት ነው፡፡ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ከቀያቸው ርቀው ሲሄዱ ስንቃቸውን የሚይዙት በዚሁ ነው፡፡ በቤት ውስጥም ዳቦ ቆሎ የመሳሰሉ ነገሮችን ለመያዣነት ያገለግላል፡፡ (ቃለመጠይቅ ንብረት እንዳለው) ጥር 25 2004 ዓ.ም


የዚህን ቁስ ጥበባዊነት ስንመለከት ቁሱ ሲሰራ በተለይ ቅርፅ (ክብ፣ ሞላላ፣ ሾጣጣ ወ.ዘ.ተ) ተደርጐ በመስራቱ ጥበብን የተላበሰ መሆኑ ማሳያ ይሆናል፡፡ የዚህን ቁስ

አገልግሎት ስንመለከት ማህበረሰቡ ትንንሾቹን አገልግሎች እረኞች ምሳቸውን (ቂጣ፣ ቆሎ ወ.ዘ.ተ) ይዘውበት እንዲሄዱ ሲያደርግ ለአባወራው ግን ተለቅ ያለው አገልግል ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል አገልግል ለክብር መገለጫነትም የሚውልበት ጊዜ አለ፡፡ ለምሳሌ የወለደች አራስ አልያም ለአክፋይ ሲኬድ የዶሮ ወጥ ተፈትፎቶ የሚሄድበት በመሆኑ ከተራው አገልግሎት ባሻገር ጥቅም ላይ ሲውል ይታያል፡፡

የዚህን ቁስ ባህላዊነት ስንመለከት፣ ቁሱ ዘመናዊ የምሳ መያዣ እቃዎች ባልተስፋፉበት ጊዜ ሲያገለግል የነበረ በመሆኑና አሁን ድረስ በገጠር አካባቢ በእርሻ ስራ ለተሰማሩ ሰዎች የምሳ መያዣ ሆኖ ሲያገለግል፣ ተሰብስቦ በአገልግሉ መብላት ደግሞ ማህበረሰባዊነቱን ያሳያል፡፡

#### 4.1.3.2. መሶብ





ስዕል 12 ባለሙያው መሶብ በመለጎም ላይ ስዕል 13 የተለጎመ መሶብ

መሶብ በባህላዊ መንገድ በስፌት ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አንዱ መሶብ ነው፡፡ መሶብ እንደ ስፌት አገልግል ሁሉ ከሳር ዘሮች ይሰራል፡፡ ከስፌት አገልግል የሚለየው ከፍ በማለቱና እግር ስለሚሰራለት እንደሆነ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡

የመሶብ አሰራር ሂደት፡- እንደማንኛውም የስፌት ቁሶች ሰበዝ፣ አክርማ፣ ስንደዶ የመሳሰሉትን ጥሬ እቃዎች በመጠቀም በወስፌ እየተገለገሉ የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ስለ መሶብ አሰራር በሸርካ ወረዳ ምርጥ ከተባለው ቀበሌ ገበሬ ማህበር መሶብ በመስፋትና ገበያ ላይ ወስዶ በመሸጥ የምትተዳደረው ወ/ሮ ፋኖሴ መብራቱ እንደሚከተለው ትገልፃለች፡፡

"ስፌቱን ስንጀምረው መቀመጫውን በዝርግ እንደሰፌድ በመስፋት ነው፡፡ ከዚያም እየሳደግነው እንሄዳለን፡፡ ክዳኑንም እንደዚሁ በዝርግ ተጀምሮ ዙሩ በጨመረ ቁጥር እያደገ ይሄዳል፡፡ በመጨረሻ ከእናት መሶቡ ጋር እንዲገጥም ይደረጋል፡፡ በስዕሉ ላይ የምንመለከተው መሶብ እስከ አምስት መቶ ብር እንደሚያወጣ ባለሙያዋ ትናገራለች፡፡ (ቃመጠይቅ፣ ፋኖሴ መብራቱ፣ ጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም) የቆዳ ስራውን በተመለከተ ከዚህ ስራ በኋላ መሶቡን ወስደው እንደሚለጉሙት ነው ከባለሙያዋ ማብራሪያ የምንረዳው፡፡

መሶብ በመለጎም ሂደት ውስጥ የመሶቡ ክዳንና የእናት መሶቡ የሚገናኙበት ቦታ ዙሪያውን ተለፍቶና ፀጉሩ ተመልጦ የተዘጋጀ ቆዳ በልክ እየተቆረጠ ከራሱ ከቆዳው በሚገኝ ጠፍር (ሲር) በወስፌ እየተበሳ ይለጎማል፡፡ በአንዳንድ ቦታ ክዳኑና እናት መሶቡ ላይ የቆዳ ዘለበት ነገር በመስፋት መሶቡ በቁልፍ እንዲቆለፍ የሚያደርጉበት ዘዴ እንዳለ ከመረጃ አቀባዮቹ መረዳት ይቻላል፡፡

*የመሶብ አገልግሎት* ለእንጀራ፣ ለዳቦና ለመሳሰሉት ምግቦች ማስቀመጫነት የሚያገለግል ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ ፋኖሴ መብራቱ የካቲት 8 ቀን 2004 ዓ.ም)

የዚህን ቁስ ጥበባዊነት ስንመለከት፣- መሶብ እናትና ልጅ በመባል የሚታወቁ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እናቱ ከልጁ ጋር ተጋጥመው የሚገኙበት መንገድ ጥበባዊ ፈጠራውን ያሳያል፡፡ በዚህ ስራ መሶቡን ለማስዋብ የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ቀለም ያላቸው የሳር አይነቶች (አለላ፣ ሰበዝ ወ.ዘ.ተ) እና ዲዛይኖች ልዩ ውበትን ያጎናፅፉታል፡፡ መሶቡን ከአደጋ ለመጠበቅና ውበትንና ለማጎናፀፍ የሚለበጡት ቆዳዎችም ለመሶቡ የሚያጎናፅፉት ውበት ጥበባዊነቱን ያሳያል፡፡ የዚህን ቁስ ባህሪ ጠቋሚነት ስንመለከት፣ ከምግብ ማስቀመጫነት ባለፈ የማህበረሰቡን ለመሶብ ያለውን አመለካከት ያሳየናል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ምንም ይሁን ምን መሶብ ቦዶውን አይቀመጥም፣ ለአዋይ ተብሎ ቁራሽ ይቀመጣል፡፡ አለበለዚያ በረከት ይርቃል የሚል እምነት በማህበረሰቡ ዘንድ ይታያል፡፡ ሌላው ወንዶች በምንም አይነት ጓዳ ገብተው መሶብ ከፍተው ምግብ አይወስዱም ይህም በሴቱና በወንዱ መካከል ያለውን በሥራ የፆታ ክፍፍልን ያሳየናል፡፡

የዚህን ቁስ ባህላዊነት ስንመለከት፣ ከአሰራሩ ጀምሮ ባህላዊነትን የተከተለ ቁስ ነው፡፡ ሐዘን በደረሰ ጊዜ ሐዘንተኛው ቤት በመሶብ እንጀራ ይዞ መሄድ የተለመደ ነው፡፡

በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድም ለማህበር ወይም ለሰንበቴ የሚሆን ዳቦ ወይም እንጀራ ተይዞ የሚኬደው በመሶብ ነው። እነዚህም ባህላዊነቱን ከሚያሳዩ መንገዶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

የዚህን ቁስ አካባቢያዊነት ስንመለከት፣ ቁሱ በደጋና በወይና ደጋ አካባቢ ለሚኖሩ ማህበረሰቦች አገልግሎት የሚውል ነው። ምክንያቱም ከመስሪያ ቁሶች ጀምሮ ያሉት የመሶብ ጥሬ እቃዎች የሚገኙት በደጋና በወይና ደጋ አካባቢዎች ነው። በቆላማው አካባቢ ምግብ በመሶብ ተደርጎ ቢቀመጥ ለብልሽት ስለሚዳረግ መሶብን የመጠቀም አዝማሚያ በብዛት አይስተዋልም። ይህም የሚያመለክተው የመሶብን አካባቢያዊ ጠቀሜታ ነው።

#### 4.1.3.3. ቁና/እንቅብ/



ስዕል 14. ቁና/እንቅብ/

ከስፌት የሚሰራ ቁስ ሲሆን መሃሉ ጉድጉድ ያለ ለእህል መስፈሪያነት የሚያገለግል ነው። በአብዛኛው ይህ ቁስ መቀመጫው ላይ እና ከንፈሩ ላይ ስለሚጎዳ የመለጐሙ ስራ የሚከናወነው በነዚህ የቁሱ አካል ላይ ነው። በመጀመሪያ በመቀመጫው ልክ ዝርግ

ቆዳ ይለካና ይቆረጣል ከዚያም በወስፌና በጠፍር በመጠቀም ይሰፋል። ከንፈሩም ልክ እንደ መሶብ ዙሪያውን በቀጭኑ በተቆረጠ ቆዳ እየተወጠረ ይሰፋል።

### 4.1.3.4. ወንፊት





ስዕል 15. ወንፊቶች

ወንፊት ከስንደዶ እና ከሰበዝ የሚሰራ የዕለት ተዕለት መገልገያ ቁስ ነው፡ መሀሉ በክብ ቅርፅ ከተሰራ በኂላ ዙሪያውን በስንደዶ እና በሰበዝ አማካይነት ከፍ ተደርጐ በዙር ይሰራል። መሃሉ ደግሞ ከስንደዶ በተገመደ ገመድ አማካኝነት ድርና ማግ ሆኖ የሚሰራ ነው። ይህን ቁስ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግልና ውበት እንዲኖረው ሲባል የወንፊቱ የላይኛው ክፍል ዙሪያውን በለሰለሰ ቆዳ ይለበጣል። እንዲሁም የወንፊቱ መቀመጫም በቆዳ ይለበጣል። ይህ ቁስ በቤት ውስጥ ዱቄትን ከቆሻሻ መለያ በመሆን ሲያገለግል በእርሻ ምርት ወቅት ምርቱን ከግርዱ ለመለየት ያገለግላል። በአሁኑ ወቅት ይህ ቁስ ከቆርቆሮና ከሽቦ በተሰራ ወንፊት እየተተካ ይገኛል። /ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ ፋኖስ መብራቴ ጥቅምት 10 ቀን 2005 ዓ.ም

በሌሎች አካባቢ እንደሚታየው የሚለጐሙ ቁሶችን የሚሰሩት ሴቶች ሲሆኑ በአርሲ ዞን ሸርካ ወረዳ ላይ ግን የመለጐሙን ስራ የሚያከናውኑት ወንዶቹ ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ሚስቶቻቸው ጉንደር ስለሚኖሩ እና እነሱም የቆዳ ስራውን ያለ ሴት ብቻቸውን በመስራታቸው ነው።

4.1.3.5. ቀረቦ




ስዕል 16. ቀረቦ


ቀረቦ ከእርጥብ ቁርበት የሚዘጋጅ ቁስ ነው። ቀረቦን ለማዘጋጀት በመጀመሪያ ለመስራት የተፈለገውን ሞዴል ቁስ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለምሳሌ እንስራን ብንወስድ እርጥቡ ቆዳ መጥቶ እንስራው ላይ ከተደረገ በኂላ ያ እርጥብ ቆዳ ሲደርቅ የእንስራውን ቅርፅ ይዞ ስለሚወጣ ቀረቦን በዚህ መልክ ማዘጋጀት ይቻላል ሲሉ መረጃ አቀባዩ ይገልፃሉ። (ቃለመጠይቅ አቶ እንግዳ ሰው ሳህሌ የካቲት 17 ቀን 2004 ዓ.ም) ጥንት ምንም አይነት የፋብሪካ ምርቶች ባልነበሩበት ጊዜ ባለሙያዎች በዚህ መልኩ እየሰሩ ለማር መያዣነት ጥቅም ላይ ሲያውሉ እንደነበር ከመረጃ አቀባዩ ለመረዳት ተችሏል።

## 4.1.4. ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች

በሽርካ ወረዳ ከቆዳ ከሚሰሩ ቁሶች መካከል አለንጋ፣ ጐመድ፣ ማሲኖዳ፣ ጋዲ፣ ሻንጣ፣ ጐፍላ፣ ደላጐ፣ ቀረቦ እና ድቤ ይገኙበታል። እነዚህን ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

4.1.4.1. አለንጋ





ስዕል 17. አለንጋዎች

ከባህላዊ የቆዳ ቁሶች መካከል አንዱ የሆነው አለንጋ ከተለያዩ እንስሳት ቆዳ ይሰራል፡፡ በዚህ ጥናት የምንመለከተው ግን ከከብት ቆዳ የሚሰራውን ይሆናል፡፡ ስለዚህ ቁስ አሰራር አቶ ተገኔ ተስፋዬ ሲገልፁ


“የዚህ አሰራር ውስጡ የፈሮ ሽቦ ሲሆን አናቱ ደግሞ የከብቶች ቆዳ ነው፡፡ (ቃለመጠይቅ ተገኔ ተስፋዬ የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም)

የአለንጋ የአሰራር ሂደት፡- በመጀመሪያ ለዚህ ቁስ ስራ የሚመረጠው ወፍራም የበሬ ቆዳ ነው፡፡ ከዚያም እንደመጫኛ በቀጭኑ ተተልትሎ በደንብ ከተለፋ በኋላ በቅርፅ እየተቀደደ በባለሙያ ብረቱ ላይ አልያም የተበጠሰ የጉማሬ አለንጋ እጀታ ላይ በማወራረስ አገልግሎት ላይ የሚያውሉበት ነው፡፡

አጥኚው በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም በሸርካ ወረዳ ጉቤሣ ከተማ ላይ በተፈጥሮ መቼቱ ላይ በተገኝበት ወቅት መረጃ አቀባዩን አለንጋ የሚታወቀው የጉማሬ እንደሆነና እንዴት በበሬ ቆዳ ሊሰራ እንደቻለ ለጠየቃቸው ጥያቄ ሲመልሱ የዚሁ የሸርካ ወረዳ ነዋሪ አቶ እንዳለ እሸቴ የተባሉ ባለሙያ እንደሚሰሩትና ይህም የሆነበት ምክንያት በወረዳው የጉማሬ ቆዳ ስለማይገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አቶ እንዳለ እሸቴ የተበጠሰ የጉማሬ አለንጋን የከብት ቆዳ በማስገባት እንደሚሰሩ መረጃ አቀባዩ አቶ ተገኔ ተስፋዬ ተናግረዋል፡፡

አለንጋ፣ በፈረስና በበቅሎ መጓጓዣዎች ሲጓዙ እንስሳዎቹ እንዲሄዱ ለመግረፊያ የሚያገለግል ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የስነ ምግባር ጉድለት ያላባቸውን ሰዎች ለመቅጣትም ይጠቀሙበታል፡፡

#### 4.1.4.2. ጉመድ




ስዕል 18 አቶ አሰፋ ጫላ ስለጉመድ ማብራሪያ ሲሰጡ

እንደ አቶ አሰፋ ጫላ አገላለፅ ጉመድ የሚሰራው ከከብት ጭራ ሲሆን በተጨማሪ ከፍየል እግርም እንደሚሰራ ገልፀዋል። በአብዛኛው ግን ከወፍራም የበሬ ጭራ እንደሚሰራ አስምረውበታል።

የጉመድ አሰራር ሂደት በመጀመሪያ የበሬው ጭራ ተቆርጦ ይወጣል። ከዚያም በጥንቃቄ የጭራው ስጋ ቆዳው ሳይሰነጠቅ እንዲወጣ ይደረጋል። በእርጥቡ በመጠን በመጠን እየተቆረጠ በዱላው ታችኛው፣ መሀከለኛው እና ጫፍ በተለያየ ቦታ ይገባል። ስለ ጉመድ ጠቀሜታ መረጃ አቀባዩ ሲገልፁ፦

“ዱላው እንዳይሰበር ጥንካሬ እንዲሰጠው ይጠቅማሉ። ደግሞም ለጌጥ ያገለግላሉ፡” በማለት ጠቀሜታውን ይዘረዝራሉ። በተለይ ፀብ በሚፈጠርበት ጊዜ ጉመድ ያለው ዱላ ለምክቶሽ አመቺና በቀላሉ ስለማይሰበር ጠቀሜታው የጉላ ነው። (አቶ አሰፋ ጫላ የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም)

#### 4.1.4.3. ማሲኖዳ

ስዕል 19. ማሲኖዳ

ማሲኖዳ ከቆዳ ከሚሰሩ ቁሶች አንዱ ነው ዘመናዊ የትራንስፖርት አቅርቦት በሌለበት
ቦታ ሰዎች የተለያዩ ቁሶችን ከቦታ ወደ ቦታ ለማጓጓዝ የተለያየ በህላዊ ዘዴዎችን
ይጠቀማሉ። ከነዚህም ውስጥ የጋማ ከብቶች ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ።
በጋማ ከብቶች ላይ እቃን ለማጓጓዝ ከሚጠቀሙበት መንገድ አንዱ ማሲኖዳ ነው።
ማሲኖዳ ነት እና ጀባ በሚሰራበት ጊዜ ያለውን ሂደት ያለፈ ቆዳ ግራና ቀኝ ትልልቅ
ኪሶች ተሰፍተውለት በፈረስ፣ በበቅሎ ላይ ከኋላ ግራና ቀኝ ተነጥፎ ለተለያዩ ነገሮች

መያዣነት የሚያገለግል ቁስ ነው። (ቃለመጠይቅ ወ/ሮ ብዙነሽ ተኮላ የካቲት 3 ቀን 2004 ዓ.ም)። ይህ ቁስ በአሁኑ ጊዜ ከማዳበሪያ በሚሰሩ ቁሶች እየተተካ ይገኛል።

#### 4.1.4.4. *ጋዲ*



*ስዕል 20. ጋዲ*

ጋዲ በቀጭኑ እየተቀረጠ አንዳንድ ጊዜም እየተገነጉና በገመድ መልክ በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጅ ከቆዳ የሚሰራ ቁስ ነው። ይሁንና ጫፉ ላይ በጣም አጠር ያለች እንጨት በተዘጋጀው ቀዳዳ ላይ ይገባና ይታሰራል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ቁሱ በጊዜያዊነት ላሚቷን ለማሰር ስለሚያገለግል በመጠምጠም አንቆ እንዳይዘው ለማድረግ ነው።

በጠፍር መልክ ከሚሰሩ የቆዳ ቁሶች መካከል አንዱ ነው። ይህ ቁስ መጫኛ በሚዘጋጅበት ሂደት ውስጥ አልፎ በቀጭኑ ከተተለተለ በኋላ በልክ ተቆርጦ /አንድ ሜትር ያህል/ የሚሰራ ሲሆን አገልግሎቱም ላም በምትታለብበት ጊዜ የኋላ ሁለት እግሯን ለማሰር ይረዳል። ይህም የሚሆነው አመለኛ የሆነች ላም ስለምትራገጥ እግሮቿ እንዳይፈራገጡ ለማድረግ የሚያገለግል ከቆዳ የሚሰራ ቁስ ነው። (ብዙነሽ ተኮላ የካቲት 3 ቀን 2004 ዓ.ም) ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ ቁስ በፋብሪካ በተሰሩ የፕላስቲክ ገመዶች እየተተካ ይገኛል።

#### 4.1.4.5. ሻንጣ



ስዕል 21. ከቆዳ የተሰራ ሻንጣ

በባህላዊ መንገድ ከሚሰሩ የቆዳ ቁሶች መካከል ሻንጣ ይገኝበታል፡፡ የቆዳ ሻንጣን በሁለት መንገድ ማዘጋጀት እንደሚቻል ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡ አንደኛው ፀጉሩ ሙልጭ ካለ ቆዳ የሚዘጋጅ ሲሆን ሁለተኛው መልክ ካለው ከብት ቆዳ ከነፀጉሩ የሚዘጋጅ ነው፡፡ አዘገጃጀቱም ልክ የመደበኛውን ሻንጣ አሰራር የተከተለ ሲሆን ከውስጥ በኩል ገበርም ይሰሩለታል፡፡ አጥኚው የቆዳ ቁሶችን በየቤቱ ሲያፈላልግ የተመለከተው ሻንጣ ዘመናዊ ዚፕ የተገጠመለት እና ውስጡ የሻማ ገበር የተሰፋለት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

#### 4.1.4.6. ጉፍላ፦



ስዕል 22. ጉፍላ

በቆዳ ከሚሰሩ የተለያዩ ቁሶች መካከል አንዱ ጉፍላ ነው፡፡ በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ የሚገኙ የቆዳ ባለሙያዎች የምትታለብ ላም ጥጃዋ ሲሞት ላሚቷ ወተት መስጠት

እንዳታቆም የሚያደርጉት ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ወረዳ ላም ስትታለብ ከፊቷ ጥጃዋ ቆሞ እሱን እየላሰች ካልሆነ እሺ ብላ አትታለብም፡፡ ይህም በመሆኑ ጥጃው ከሞተ ላሚቷ ወተት ስለማትሰጥ ጉፍላን መጠቀም ግድ ይላል፡፡

**የጉፍላ አሰራር ሂደት፡-** በመጀመሪያ የሞተውን ጥጃ ቆዳ ስልቻ እንደሚወጣ ቆዳው ሳይቀደድ ጃኬት ገልብጠን እንደምናወልቀው አይነት ቆዳው ድፍን እንደሆነ በዘዴ ይወጣል፡፡ ከዚያም መወጠሪያ እንጨት ውስጡ በማስገባት ቆዳው ቀጥ ብሎ ደርቆ እንዲቆም ይደረጋል፡፡ በመቀጠል ገለባ ወይም ጭድ በውስጡ በመጠቅጠቅ ሆዱ እንዲሞላና በሕይወት ያለ እንዲመስል ይደረጋል፡፡ ምንም እንኳ በዚህ መልኩ የተሰራው ጥጃ በፊቷ ቆሞ ብትታለብም ጨው ጥጃው ላይ መነስነስ ግድ ይላል፡፡ አቶ ፈለቀ ተስፋዬ በበኩላቸው ስለ ጉፍላ ሲናገሩ *"ጉፍላ የሞተ ጥጃን በህይወት እንዳለ አስመስሎ የመስራት ዘዴ ነው፡፡ ጥጃው ከሞተ በኋላ ልክ እንደስልቻ ከተገፈፈ በኋላ ውስጡን በጭድ ሞልቶ በማቆም ላሚቷን አታሎ የማለብ ዘዴ ነው፡፡" ይላሉ፡፡ (የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ.ም፡፡)*

ይህ ዘዴ በዘመናዊ መልክ Taxidermy በመባል ከሚታወቀው የአሰራር ጥበብ ጋር ይመሳሰላል፡፡

### 4.1.4.7. ደላጉ

ደላጉ፣ ቁርበት ወይም ነት ሲያልቅ ለተለያዩ ነገሮች የሚያገለግል ለምሳሌ፣ ለእህል ማስጫ፣ ብዙም የማይጨነቁለት እንግዳ ሲመጣ የሚነጠፍ ነገር ነው፡፡ በዚህም ማህበረሰቡ በቆዳ ቁሶች አማካይነት ለሰዎች ደረጃ መስጠቱን እንመለከታለን፡፡ ደጃዝማችና ባላምባራስ ሲመጡ ነት እንደሚነጠፍላቸውና ዝቅተኛ የተባሉት የማህበረሰቡ አባላት ደግሞ ደላጉ እንደሚነጠፍላቸው ያሳያል፡፡ *(ቃለመጠይቅ አቶ እንግዳ ሰው ሳህሌ፣ የካቲተ 17 ቀን 2004 ዓ.ም)*

### 4.1.4.8. ጠፍር

እንደ መጫኛ ተተልትሎ ለድንክ፣ ለአልጋ እና ለወንበር እንደርብራብ የሚያገለግል የቆዳ ቁስ ነው፡፡

**የጠፍር አሰራር ሂደት፡-** የጠፍር አሰራር ከመጫኛ የአሰራር ሂደት ጋር ተመሳሳይነት ሲኖረው የጠፍር ቆዳ ፀጉር ግን ሙሉ በሙሉ አይነሳም፡፡ መረጃ አቀባዮች እንደሚሉት

*ጥንት ሀብት ያላቸው ሰዎች የቤታቸውን ጣሪያ የሚያዋቅሩት በቀጫጭኑ በተተለተለ ጠፍር እንደነበረ አቶ ጌቱ ተፈራ "በድሮ ጊዜ ሀብት ያላቸው ሰዎች ቤቱን ካዋቀሩ በኋላ ማገሩንና ወራጁን እየማገሩበት ከጭምጭሙ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ የሚያያዙበት ነው። እንደገመድ የሚጠቀሙበት ነው።" በማለት ገልፀዋል። (ቃለመጠይቅ የካቲት 2 ቀን 2004 ዓ.ም)*

4.1.4.8 ድቤ



ስዕል 23. ድቤ

በሽርካ ወረዳ ላይ በባህላዊ መንገድ ከቆዳ ተሰርተው ከተገኙ ቁሶች መካከል አንዱ ድቤ ነው። ድቤ እንደ ጀባ ሁሉ ፀጉሩ ሳይመለጥ ክብ በሆነ ጉድጓዳ ሳህን ወይም ክብ ተደርጐ ከተጠረበ የኮርች እንጨት ላይ በመወጠር የሚሰራ ቁስ ነው። የድቤ አሰራር ሂደት በመጀመሪያ ከአፉ ሰፋ ያለ እና ከወደ መቀመጫው ጠበብ ያለ ሲሆን ከተጠረበ እንጨት እንደሚፈለገው መጠን ይዘጋጃል። ድቤን ለማዘጋጀት የደረቀው ቆዳ በውሃ ውስጥ ለሦስት ቀናት ያህል ከተዘፈዘፈ በኋላ በችካል ተወጥሮ ተረፈ ስጋው በቢላዋ ወይም በመጥረቢያ ሙልጭ ተደርጐ ይነሳል። ከዚያም በእርጥቡ በልክ ከተቆረጠ በኋላ ዙሪያውን ለመወጠሪያ የሚያገለግሉ ቀዳዳዎች (ቅፍንዶች) ይሰሩለታል። በመቀጠል ዙሪያውን በቀጫጭኑ በተተለተሉ ጠፍሮች አማካይነት በቀዳዳው እያስገቡ በመወጠር ዙሪያውን

ይታሰራል፡፡ በመጨረሻም ፀሐይ ላይ በማድረቅ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ (ቃለመጠይቅ አቶ ከበደ በዳኔ ጥር 27 ቀን 2004 ዓ.ም) በአብዛኛው ይህ ቁስ ቃልቻ ቤት እንደ ከበሮ ሆኖ ያገለግላል፡፡

በተለይ ባሌ ዞን የሚገኘው የሼክ ሁሴን በዓል ላይ ለመታደም የሚጓዙ መንገደኞች በሁለት ቀጫጭን ዱላዎች አማካይነት እየመቱ ምስጋና የሚያቀርቡበት የምት መሳሪያ ነው፡፡ ይህ ቁስ ከባህላዊ መሳሪያዎች አንዱ ሲሆን በባህላዊ እምነት ላይ የመንዙማ ዜማ ማጀቢያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 4.2. በሸርካ ወረዳ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች መስሪያ መሳሪያዎች

በወረዳው የቆዳ ቁሶችን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች መጥረቢያ፣ ወስፌ፣ ቢላዋ፣ ችካል /ካስማ/ ሲሆኑ እነሱም ለመፋቅ፣ ለመብሳት፣ ለመቆራረጥና ለመወጠር ሰሪዎቹ የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ እነዚህን መሳሪያዎች ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

መጥረቢያ



ስዕል 24. መጥረቢያ

እጀታው (ዛቢያ) ከእንጨት የሚሰራ ሲሆን መፋቂያው ከብረት የሚሰራ ጠፍጣፋ የሆነና ለእንጨት (ዛቢያ) ማስገቢያ የሚሆን ቀዳዳ የተበጀለት መሳሪያ ነው፡፡ እንጨቱ (ዛቢያው) በብረቱ ቀዳዳ ልክ ከተስተካከለ በኋላ በቀዳዳው እንዲገባ ይደረጋል፡፡ ጫፉ በሞረድ ይሳልና ቆዳውን ለመፋቅ ያገለግላል፡፡ መጥረቢያ ከቆዳ ስራ ባሻገር አነስ ያሉ ግንዶችን ለመፍለጥና ለመቁረጥ ያገለግላል፡፡

ወስፌ (ወሳፍቻ)



ስዕል 25 ወስፌዎች

ወስፌ በቆዳ የሚለጐሙ ስፌቶችን ለመስፊያ ያገለግላል፡፡ እጀታው ከእንጨት የተሰራ ሲሆን ለስፌት የሚያገለግለው ክፍል ከብረት የተሰራ ሹል ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አገልግል በሚለጐምበት ጊዜ ቆዳው እንዳይሸበሸብ በሁለት ወስፌዎች ተወጥሮ በሶስተኛው ወስፌ በአቶ ንረበት እንዳለ አማካይነት ሲሰፋ አጥኚው በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም በጉቤሣ ከተማ በተፈጥሮ መቼቱ ላይ በተገኘበት ወቅት ለማየት ችሏል፡፡

ቢላዋ





ስዕል 26. ቢላዎች (ካራዎች)

ቢላዋ፣ እጀታው ከእንጨት ወይም ከቀንድ የሚሰራ ሲሆን መቁረጫው ደግሞ ከብረት የሚሰራ ቁስ ነው፡፡ ይህ መሳሪያ ቆዳው ላይ የቀረ ተረፈ ስጋ (ደደብ) ከማስለቀቁም በላይ ለመወጠሪያ የሚያገለግሉት ቀዳዳዎች (ቅፍንድ) ለመብሻነት ያገለግላል፡፡

ችካል (ካስማ)



ስዕል 27. የእንጨት ችካሎች

ለባህላዊ ቆዳ ስራ የሚያገለግለው ችካል ከእንጨት የሚሰራ ሲሆን ወደ መሬት ዘልቆ መግባት እንዲችል ከጫፍ ላይ ሾል ተደርጐ የሚዘጋጅ መሳሪያ ነው። ይህ ቁስ ቆዳውን በተለያየ አቅጣጫ ወጥሮ ለመያዝ የሚያገለግል ነው። አንድን የበሬ ወይም የላም ቆዳን ለመወጠር ከሰላሳ እስከ ሰላሳ አምስት ችካሎች እንደሚያስፈልጉ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ።

## 4.3. ለማለስለስ እና ፀጉር ለማስለቀቅ የሚያገለግሉ ጥሬ እቃዎች

የቆዳ ባለሙያዎች ቆዳውን ለማለስለስና በቆዳው ላይ ያለውን ፀጉር ለማስለቀቅ የሚጠቀሙባቸው ጥሬ እቃዎች ከተክል ዘር ጉሎ የተባለውን ተክል ነው። ከተክሉ በተጨማሪ የከብት ሽንት ይጠቀማሉ።

ጉሎ



ስዕል 28. የጉሎ ፍሬ



ስዕል 29. የጉሎ ተክል

ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ ቅባትነት ያለው ፍሬ የሚያፈራ ተክል ነው፡፡ ፍሬው ከግንዱ ላይ ተለቅሞ እንዲደርቅ ከተደረገ በኋላ ተወቅጦ በውሃ ይበጠበጣል፡፡ የተበጠበጠውን ጉሎ እንዲባካ በሸክላ ዕቃ ተደርጐ ፀሐይ ላይ ይቀመጣል፡፡ በዚህ አይነት የተዘጋጀው ጉሎ ቆዳው ከተፋቀ በኋላ ለማለስለሻነት ያገለግላል፡፡ ቆርፍዶ የነበረውን ቆዳ እንደልብ እንዲተጣጠፍ ይረዳዋል፡፡ ባለሙያው አቶ ከበደ በዳኔ ስለ ጉሎ ሲገልፁ፡-

"ጉሎ" ቁርበት መቀቢያ ነው፡፡ ያለሰልሳል ወቅጠን አድቀን በውሃ በጥብጠን እንዲቦካ ፀሐይ ይሞቃል፡፡ ቅባትነት ስላለው ቆዳውን ያለሰልሰዋል፡፡ (ቃለመጠይቅ አቶ ከበደ በዳኔ ጥር 27 ቀን 2004 ዓ.ም)

ሌላው መረጃ አቀባይ ሲገለፁ፡-

> *ቆዳው ተፍቆ ካለቀ በኋላ ፀሐይ ላይ ተወጥሮ እንዲደርቅ ከተደረገ በኋላ በእርሾ በቦካ የጉሎ ቅባት መቀባት ነው፡፡ ከተቀባ በኋላ ፀሐይ ላይ ማንቃቃት ነው፡፡ የጉሎ ጥቅም ቅባትነት ስላለው እንዲለሰልስ ያደርገዋል፡፡ (ቃለመጠይቅ ስለሺ ተስፋዬ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

በአሁኑ ጊዜ የጉሎ ፍሬ ዋጋ እያሻቀበ በመምጣቱ ባለሙያዎቹ እየተቸገሩ መኖሩን መረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡

የከብት ሽንት

በወረዳው የቆዳ ስራ የከብቱን ፀጉር ለማስለቀቅ የሚያገለግለው የከብት ሽንት ነው፡፡ የከብት ሽንት የአሲድነት ባህሪ ስላለው በቆዳ ስራ ጊዜ የቆዳው ፀጉር እንዲለቅ የሚዘፈዘፈው በዚህ በተጠራቀመ የከብት ሽንት ነው፡፡ በከብት ሽንት የተዘፈዘፈው ቆዳ ጥሬውን ከሚፋቀው ቆዳ ፀጉሩ ቶሎ የመልቀቅ ባህሪ እንዳለው መረጃ አቀባዩ አቶ ንብረት እንዳለ ይናገራሉ፡፡

## 4.4. ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ለመዳ በሸርካ ወረዳ

Roberts ውስተ Dorson (1972, 233) Crafts techniques and designs were passed down with in one family for many generation or were transmitted by the apprentice system" በማለት ይገልፀዋል፡፡

የአርሲ ሕዝብ ከዚህ በፊት ኢኮኖሚው በከብት እርባታ ላይ የተመሰረተ ሲሆን አሁንም ከእርሻ ጐን ለጐን ከብት እርባታን እያካሄደ ይገኛል። ከእነዚህም የሚገኙ የቆዳ ውጤቶችን ለተለያዩ አገልግሎቶች ይጠቀምባቸዋል። ባህላዊ እውቀቱንም ተጠቅሞ ከቆዳ ልብስ ይሰራል። እንዲሁም የተለያዩ ቁሶችን ያመርታል። በዚህ ሂደት ይህንን እውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ እያሸጋገረው እዚህ ደርሷል።

የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በሸርካ ወረዳ ቀድሞ ይሰሩ የነበሩትና አሁን ደግሞ ከጐንደር አካባቢ የመጡት የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ሙያውን በሦስት መንገድ እንደለመዱት ይናገራሉ። አንደኛው ከቤተሰብ በዘር ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ሲሆን ሁለተኛው ማስልጠኛ ገብተው በመሰልጠን የተገኘ ነው። ሦስተኛው ደግሞ ማስልጠኛ ገብተው ከሰለጠኑ ሰዎች ወይም ሙያውን ከሚሰሩ ሰዎች በመመልከት ሙያውን የለመዱ መሆናቸውን ይናገራሉ። *"እኔም የተማርኩት ከቀድሞዎቹ የቆዳ ስራ ባለሙያዎች ነው። እነበላቸው ከነሱ ተማሩ እኔም ከነበላቸው ተማርኩ አሁንም እየሰራሁ እገኛለሁ።" በማለት አቶ በላይነህ ማሞ ሙያው ውስጥ እንዴት እንደገቡ ገልፀውልኛል (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)* በተጨማሪ አቶ በላይነህ የቆዳ ስራ ሙያን ከቤተሰብ የወረሰ ሰው እንዳለ ሲገልፁ "የለም ተከታትሎ የስራ የለም አንድ ነበር እሱም አልሰራም አለ። ትቶንም አሰላ ሄደ።"

የቀድሞዎቹ የቆዳ ስራ ባለሙያዎች ሙያውን ለልጆቻቸው አለማስረከባቸውን መረጃ አቶ ስለሺ ተስፋዬ *"በሸርካ ወረዳ ላይ የቆዳ ስራን ይሰሩ የነበሩ ባለሙያዎች ተረካቢ በማጣታቸው ስራው እየተዳከመ በመጣበት ወቅት ከጐንደር መተው አሁን እያስፋፉት ይገኛሉ።" (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

የባህላዊ ቆዳ ስራው እየተዳከመ በመጣበት ወቅት ከደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ የመጡ ሰዎች እንደአስፋፉት ይናገራሉ። ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አቶ ንብረት እንዳለ እንደሚናገሩት በጐንደር እስቴ ወረዳ የጐልማሶች ማስልጠኛ ጣቢያ በባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ እንደሚያስለጥንና አሳቸውም እዛ ማስልጠኛ ገብተው ሙያውን እንደቀሰሙ ይናገራሉ። አሁን ከሳቸው ጋር የሚሰሩት አንዳንድ ባለሙያዎችም ሙያውን ከአቶ ንብረት እንዳለ ለምደው እየሰሩ መሆናቸውን በቃለ መጠይቁ ወቅት ተናግረዋል።

## 4.5. የባህላዊ ቆዳ ስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ

በዚህ ርዕስ ስር የሸርካ ወረዳ የቆዳ ቁሶች ባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታቸው ምን እንደሚመስል ይዘረዘርበታል፡፡

### 4.5.1. የባህላዊ ቆዳ ስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት

ቀደም ባለው ጊዜ በሀገራችን የእደ ጥበበ ባለሙያዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጣቸው ግምት ዝቅተኛ ነበር፡፡ Silver man (1999,1) ስለ ኢትዮጵያ የእጅ ባለሙያዎች ሲያብራሩ በአብዛኛው በቡድን በአንድ አካባቢ ራሳቸውን ለይተው እንደሚኖሩና በሌላው ማህበረሰብ የተገለሉ መሆናቸውን፣ ለዚህ ምክንያቱ ሰዎቹ የተለዩ ፍጡራን ናቸው በሚል አስተሳሰብ እንደሆነ ነው፡፡ ባለሙያዎቹ የሚሰሯቸውን ቁሶች እየተገለገሉበት፣ ባለሙያዎቹን እንደሚንቁና እንደሚያገሉ በዚህ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች ይናገራሉ፡፡ እንደ ሌሎቹ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ሁሉ የቆዳ ስራ ባለሙያዎችም “ፋቂ” እና “ጥንብ በላ” የሚል መጠሪያ ተሰጥቷቸው ሲንቋሸሹ ይታዩ ነበር፡፡ ለቆዳ ባለሙያው “ፋቂ” እንደሚሉት ለብረት ሰራተኛውም “ቀጥቃጭ” ወ.ዘ.ተ በማለት ክብራቸውን ዝቅ ሲያደርጉት ይታያል፡፡ (Gallagher, 1974, 177)

የቆዳ ስራ ባለሙያዎችን “ፋቂ” በሚለው ስም መጠራት የጀመሩት ጥንት መሆኑንን የሚያስረዳ አንድ የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ አለ፡፡ “በኢዮጵም ስምኦን ከአንድ ቁርበት ፋቂ ጋር አያሌ ቀን ኖሩ፡፡” ሐ/ሥ 9፣43 ይላል፡፡

በሸርካ ወረዳም ባለፉት ጊዜያት የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ዝቅ ተደርገው የሚታዩና ማግለልም እንደነበረ ከመረጃ አቀባዩ አቶ ደርቤ ይፍሩ ገለፃ መረዳት ይቻላል፡፡ “ድሮ የቆዳ ቁሶች ማግለል ነበረ እነዛ ሰዎች በሚሰሩበት ጊዜ እንደዚህ አይነት ነገር ነበር፡፡ የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎቹ ስራው ከመጥፎ ሽታ ጋር የተያያዘ መሆኑና “ቡዳ” ናቸው የሚል አመለካከት ስለነበረ እኔ ልጅን ለቆዳ “ፋቂ” አልሰጥም በማለት እነሱ እርስ በርሳቸው ይጋቡ ነበር እንጂ ከሌላው ጋር በጋብቻ አይገናኙም ነበር፡፡ (አቶ ደርቤ ይፍሩ፣ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)፡፡ ጉዳዩ አቶ ስለሺ ከዚህ ቀደም ማህበረሰቡ ስለባለሙያዎቹ የነበረውን አመለካከት *“ከዚህ በፊት በነበረው ሁኔታ በቆዳ ሰራተኞች እና በብረት ሰራተኞች ላይ የማግለል ሁኔታ ነበር፡፡ እንደ ብረት ሰራተኞቹ ባይሆንም የቆዳ*

*ሰራተኞቹ ላይ ይታይ ነበር።" በማለት ይገልፃሉ። (ቃለመጠይቅ፣ ስለሺ ተስፋዬ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

*ሌላው መረጃ አቀባይ አቶ አፈወርቅ ጋሪዴ ደግሞ "አንድ የቆዳ ስራ ባለሙያ ሚስት ለማግባት ከራሱ ከባለሙያው ወገን ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ከሌላው ማህበረሰብ ውስጥ ሚስት የሚያጭለት አልነበረም። አሁን ግን ያነገር ቀርቷል።" ብለዋል። (ቃለመጠይቅ የካቲት 8 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ሌላ አካባቢ ይሄዳሉ፡ በዚህን ጊዜ ከሚሄዱበት አካባቢ ሕረተሰብ ጋር በባህል፣ በቋንቋ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ይተሳሰራሉ። ሰዎቹ በሚንቀሳቀሱበት ጊዝ የራሳቸው የሆነውን አካባቢያዊ እውቀት በመጠቀም በሄዱበት አካባቢ ይሰራሉ። ይሁንና እነሱ ይዘውት የመጡት አካባቢያዊ እውቀት ለማህበረሰቡ አዲስ አይሆነም፣ ተመሳሳይ ነው። ይህም የሚያሳየው በእንቅስቃሴው ወቅት Folk እንጂ Lore እንደማይንቀሳቀስ ያሳያል። ይህም በዚህ ጥናት ከጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ የመጡት ባለሙያዎች ከሽርካ ወረዳ ካሉት ባለሙያዎች ጋር በአስራር ጥበብ ተመሳሳይ ሆኖ መገኘት ነው። ይህም የሚያሳየው ሰዎቹ መጡ እንጂ ጥበቡ እዚህም እንዳለ የሚያሳይ ነው። የባለሙያዎቹን አመጣጥ ስንመለከት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ እግር ጥሏቸው የመጡት አንድ የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያ የወረዳውን የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ገበያ አጥንተው መስራት በመጀመራቸው ብሎም ተከታዮቻቸው በቆዳ ባለሙያው እግር ተከትለው በመምጣታቸው ምክንያት አሁን አሁን የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ሙሉ በሙሉ በእነዚህ ሰዎች ስር ወድቋል ማለት ይቻላል።

*ባለሙያዎቹ ቤት ለቤት በመሄድ ቆዳውን የሚሰበስቡ በመሆናቸው ጥንት እቤት ድረስ ያውም በምልጃ ያሰራ የነበረው ደንበኛ አሁን እፎይ ብሎ ባዘዘው ሰዓት እና በሚፈልገው መልኩ ስለሚሰራለት ያለፈውን ጊዜ በቁጭት ሲያነሳ ይታያል።"ከዚህ በፊት ሽርካ ወረዳ ላይ በቆዳ ስራ የተሰማሩ ሰዎች አንድን ቁስ ለመስራት ከሦስት ወር*

*በላይ ቀጠሮ ይሰጡ ነበር። የተሰጣቸውንም ቆዳ አይጥ እያስበሉ ግማሹም በለውጥ እየሄደ፣ የለም እየተባለ (ሳቅ) እየተጣላን ሁሉ የቀረ ነበር።" (ቃለመጠይቅ ስለሺ ተስፋዬ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

በማህበራዊ ኑሮ በኩልም እነዚህ ባለሙያዎች እንደ ጥንቶቹ የማይገለሉና በሙያቸው ተከብረው እየኖሩ እንዳለ ከመረጃ አቀባዮቹ መረዳት ይቻላል።

> *በጥናት ከደቡብ ጐንደር መጥተው እዚህ አገር ባህላዊ የቆዳ ስራ ገበያ እንዳለ አዩ። ተመልሰው አገራቸው ሄደው ብዙ ሰዎች ይዘው መጥተው አሁን ይኸው ብዙ አገልግሎት እየሰጡ ነው። ሕዝቡም በጣም ተቀብሏቸዋል። ጥሩ ነው ማግለሉ የለም። (ቃለመጠይቅ ስለሺ ተስፋዬ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ባለሙያዎቹ ከማህበረሰቡ ጋር ተከባብረውና ተዋህደው እንደሚኖሩና የስራ ተነሳሽነታቸው ለአካባቢው ማህበረሰብ አርአያነት እንዳለው መምህር ኃይልዬ ማንደፍሮ *"ከጐንደር የመጡ ባለሙያዎች በማህበራዊ ህይወታቸው ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር ተስማምተው በሰላም ነው የሚኖሩት የአካባቢውም ህዝብ በደንብ ተቀብሏቸዋል።" ሲሉ ያለውን ሁኔታ ይገልፃሉ። (ቃለመጠይቅ መምህር ኃይልዬ ማንደፍሮ የካቲት 4 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ባለሙያዎቹ የሚኖሩት የወንዙን ዳር ዳር ይዘው ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት አንድም የቆዳ ስራ ከመጥፎ ሽታ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጐረቤት ላለማስቀየም፣ አንድም ቆዳውን በውሃ ለመዘፍዘፍ አመቺ በመሆኑ ነው። ይሁንና ቤት አከራዮቹ ቤታቸውን ለተለያየ ጉዳይ ስለሚፈልጉት እና ለባለሙያዎቹ ካላቸው የተዛባ አመለካከት የተነሳ ባለሙያዎቹ በየጊዜው ቤት ለመቀየር መገደዳቸውን ከባለሙያዎቹ እና ከመረጃ አቀባዮቹ ለመረዳት ተችሏል።

ባለሙያዎቹ በአለባበሳቸው ከነዋሪው ለየት ያሉ ስለሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ "ቁምጣ ለባሾች" በመባል ይታወቃሉ። እነሱ የሚለብሱት ከላይ እጃ ጉርድ ጃኬት እና ከታች ከጉልበት በላይ የምትውል ጠባቃ ቁምጣና በእግራቸው የሚሄዱ ሲሆን በከተማም ውስጥ ሆነ በገጠር ቆዳ ለመሰብሰብ ወይም የተሰራን ቆዳ ለማድረስ ሲሄዱ በሰልፍ ዱላ ይዘው እንደሆነ ከመረጃ አቀባዮች ለመረዳት ተችሏል። ከዚህም የተነሳ አንዳችም ሌባ ወደነሱ እንደማይጠጋ ነዋሪዎቹ ይናገራሉ።

ቁምጣ የሚለብሱበት አንዱ ምክንያት ለስራ ስለሚያመቻቸው እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ። አብዛኞቹ የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች በደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ ላይ ትዳር የመሰረቱና ልጆች የወለዱ መሆናቸውን በቃለ መጠይቁ ወቅት ለመረዳት ተችሏል። እነዚህ ባለሙያዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚጠያየቁበት ወቅትም የፆም ወቅት በተለይም የሁዳዴ ፆም መሆኑን አጥኚው በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም ጐቤሳ ከተማ ተፈጥሯዊ መቼቱ ላይ በተገኘበት ወቅት ለማረጋገጥ ችሏል። ይህንንም ወቅት የመረጡበት ምክንያት ወቅቱ የሚታረድ ከብት በብዛት ስለማይኖር መሆኑን ይገልፃሉ። በዚህን ጊዜ በአጋጣሚ የታረደ ከብት ካለ ቀብድ ሰጥተው ስለሚሄዱ ከጐንደር ሲመለሱ ቆዳው በአግባቡ ተቀምጦ እንደሚጠብቃቸው ከመረጃ አቀባዮቹ ለመረዳት ተችሏል።

የቆዳ ስራ ባለሙያዎቹ ቤተሰቦቻቸው ከነሱ ርቀው ስለሚኖሩ በቤታቸው ውስጥ ምግብ የሚያበስል ባለመኖሩ ምግባቸውን የሚያገኙት አንድም ከሆቴል፣ አንድም የቆዳ ስራውን ከሰሩላቸው ደንበኛ ቤት በመጋበዝ ነው። በሆቴል ቤት ሲመገቡ በአንድ ላይ ሳይሆን እያንዳንዱ በትሪ ለየብቻው እንደሆነ አንድ የሆቴል ባለቤት የሆኑት ወጣት ዳንኤል ዘውዴ ይናገራሉ።

"አንድ እንጀራ ለሁለት አይበሉም አንዳንድ በተናጠል ነው ለሁሉም የሚሰጠው ያ ምንድነው ጉልበተኛው ራሱ እንዲበላ አይፈልጉም።" (ቃለመጠይቅ ወጣት ዳንኤል ዘውዴ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም) የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎቹ የስራ ክፍፍልን በተመለከተ ገሚሱ እቤት ቆዳ ሲዘፈዝፍ፣ ሲወጥር፣ ሲያለፋና ሲፍቅ ሲውል፣ ገሚሱ ደግሞ ወደ መስክ በመሰማራት የሚሰሩ ቁሶችን፣ ቆዳዎችን፣ መሰብሰብ እና ተሰርተው ለባለቤቶቹ የሚመለሱትን በመመለስ በየቤቱ እና በየገበያው በመሄድ የድርሻቸውን ይወጣሉ። በቀጣይ መስክ ላይ የነበረው ቤት ሲውል ቤት የነበረው ደግሞ በተራው ወደ መስክ በመውጣት ስራቸውን ያከናውናሉ።

ባለሙያዎቹ ከማሕበረሰቡ ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች (በሠርግ፣ በለቅሶ፣ በተዝካር፣ በንግስ በአላት ወ.ዘ.ተ. በመገናኘት አብረው ያሳልፋሉ። በመዝናኛ ቦታዎች ያለውን ሁኔታ አቶ ደርቤ ይፍሩ የተባሉ መረጃ አቀባይ እንዲህ ይገልፁታል።

> *ከጐንደር የመጡ ባለሙያዎችን እንደአየኋቸው ከስራ ሰአት ውጭ እና በባእላት ላይ ሲዝናኑ ደስ ይላሉ። ከህብረተሰቡም ጋር ተዋህደው እና ተግባብተው እየኖሩ እንዳለ በሰርጉ፣ በተስካሩ እና በልደቱ እየተጠሩ ሲሳተፉ ነው የማየው። (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ባለሙያዎቹ መካከል ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ነባሮቹ ለአዲሶቹ ያላቸው አመለካከት ጥሩ አይደለም፡፡ የቆዳ ስራ በማን እንደተጀመረ ለተጠየቁት ጥያቄ "የለም እነሱ ተሰደው ነው ከሀገራቸው የመጡት እኛ ግን የቆየንበት ነው" በማለት ሲመልሱ ስለ ባለሙያዎቹ ካላቸው በጐ ያልሆነ አመለካከት የተነሳ በምሬት እንዲህ ብለዋል፡፡

"እነሱማ አሉ ወንዙን ኩሉ ይዘውታል፡፡ እንደውም እኛ ሰርተን እንዳንበላ ገበያው ሁሉ ያዙት፡፡" (ቃለመጠይቅ አቶ በላይነህ ማሞ ጥር 27 ቀን 2004 ዓ.ም)

## 4.5.2. የባህላዊ ቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ኢኮኖሚያዊ ገጽታ

በአርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ላይ የሚገኙ የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ ወረፋ ይበዛ ነበር፡፡ ባለሙያዎቹ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩበት ሙያ ይኸው የቆዳ ስራ ነበር፡፡ ይህንንም ባለሙያው አቶ በላይነህ ማሞ ሲገልፁ፡፡ በፊትም ሆነ ዛሬ ስራዬ የቆዳ ስራ ነው፡፡ እቁብም ብጠጣ ቦታም ብገዛ በዚሁ ስራ ነው፡፡ (ቃለመጠይቅ በላይነህ ማሞ ጥር 27 ቀን 2004 ዓ.ም) የቀድሞዎቹ የቆዳ ባለሙያዎች አሁን ያሉበት ሁኔታ አጅግ አሳዛኝ ነው፡፡ ቀድሞ ቤት ድረስ ጥሬ ቆዳውም ሆነ ቁሶቹ እየመጡላቸው በምልጃ እንዳልሰሩ አሁን ከጐንደር እስቴ ወረዳ በመጡ ባለሙያዎች ገበያውን በመነጠቃቸው ሙያውን በመተው ወደ ሌላ ስራ ለመሰማራት እንደተገደዱ ይናገራሉ፡፡ አቶ በላይነህ ማሞ ስለዚህ ሁኔታ ሲገልፁ፡-

"ቆዳው እዚሁ እቤት ነው የሚመጣው አሁን ግን እነሱ እየዞሩ ከየቤቱ ስለሚሰበስቡ በሙሉ ደጁ ሁሉ የነሱ ነው፡፡ እኛ አሁን ምንም ቆዳ የለንም የምንሰራው እንኳ የለንም፡፡" (ቃለመጠይቅ በላይነህ ማሞ ጥር 27 ቀን 2004 ዓ.ም)

ከጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ የመጡ የቆዳ ስራ ባለሙያዎችን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ወጣት ዳንኤል ዘውዴ ጐንደር እስቴ ወረዳ ሄደው ከመጡ ሰዎች እንደሰማው "*ኑሮአቸው በከፍተኛ ሁኔታ እየተለወጠ መምጣቱን ነው፡፡ ሽርካ ወረዳ ላይ ሰርተው፣ ጐንደር ላይ የተለያየ ግንባታ እያካሄዱ እንዳለ ነው፡፡" (ቃለመጠይቅ፣ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

እነዚህ ባለሙያዎች ከአለባበሳቸው ጀምሮ ሲመለከቷቸው ምስኪን መስለው ይታያሉ በማለት ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ናቸው መባሉን አቶ ደርቤ ይፍሩ እንዲህ ሲሉ አጫውተውኛል፡፡

*ከጐንደር የመጡ ባለሙያዎችን ስንመለከታቸው ምስኪን ይመስላሉ። ነገር ግን በአንዳንድ ስራ አጋጣሚ ጐንደር ሄደው የመጡ ሰዎች ሲነግሩን በቀያቸው ደህና ኑሮ እንደሚኖሩ ነው። እዚህ እኛጋ ሰርተው ወደ ጐንደር ለቤተሰቦቻቸው እንደሚልኩ ነው የምንሰማው። (ቃለመጠይቅ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ከመረጃ አቀባዮቹ ገለፃ እንደምንረዳው ቀድሞ በወረዳው ላይ ባህላዊ የቆዳ ስራን ይሰሩ የነበሩ ሰዎች ከደቡብ ጐንደር በመጡ ባለሙያዎች የገበያ ውድድር ከጫወታ ውጭ እየሆኑ መምጣታቸውን እንገነዘባለን። ባለሙያዎቹ በአካባቢው ነዋሪ ዘንድ አለባበሳቸውን በመመልከት ብቻ ምንም የሌላቸው ምስኪን አድርጐ እንደሚቆጥራቸው ከመረጃ አቀባዮቹ ለመረዳት ይቻላል። ነገር ግን ባለሙያዎቹ በደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ ላይ ጥሩ የሆነ ኑሮ ቤተሰቦቻቸውን እንደሚያኖሩና የተከበሩ እንደሆነ በሥራ አጋጣሚ ጐንደርን ያዩ የወረዳው ነዋሪዎች እማኝነታቸውን ሰጥተዋል።

# 5. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳቦች

በዚህ ክፍል እስካሁን በቀረቡ ክፍሎች የተዳሰሱ ጉዳዮችና ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳት ለባህሉ እድገት የሚጠቅሙና ቢደረጉ የሚሉ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በወረዳው ምን እንደሚመስል ማሳየት እና መሰነድ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ቁሶቹ ሲሰሩ ያለውን የአሰራር ሂደት፣ ከቆዳ የሚሰሩት ቁሶች የሚሰሩባቸውን ጥሬ ዕቃዎችና የመገልገያ መሳሪያዎች ጭምር መግለፅ ነው፡፡ በሌላ በኩል የባለሙያዎቹን ማህበራዊ ህይወት በመቃኘት ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸውን ማሳየት፣በተጨማሪ የባለሙያዎቹን የአሰራር ጥበብ መመርመር፣ በወረዳው የቆዳ ቁሶች ስራ አጀማመር እና ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ ለማህበረሰቡ አመለካከት ማሳየት ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህን ዋናና ንፁሳን አላማዎች ከግብ ለማድረስ በመስክ ቆይታ ምልከታና ቃለመጠይቅን በዋነኛ መረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሞዋል፡፡ በእነዚህ ሁለት ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በክለሳ ድርሳን ውስጥ ከቀረቡት ንድፈ ሃሳቦች አኳያ ተተንትነው ከሚከተለው የማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ተደርሷል፡፡

ጥናቱ መረጃ አቀባዮችን ዋቢ አድርጎ በሸርካ ወረዳ የቆዳ ቁሶች ስራ ከዘጠና ዓመት ዕድሜ በላይ ያስቆጠረ እና ሲወርድ ሲወራረድ እዚህ የደረሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና ጥሬ እቃዎች አቅርቦት ከአካባቢው የሚገኙ እንደሆነና በአሁኑ ጊዜ የቆዳ ማለስለሻ የጐሎ ፍሬ በመወደዱ ምክንያት ባለሙያዎቹ ችግር እንደ አጋጠማቸው በጥናቱ ታይቷል፡፡ የባህላዊ የቆዳ አሰራርን ለመዳ በተመለከተ ሙያውን የሚለምዱት የተወሰኑት ማስልጠኛ ገብተው በመማር ሲሆን ሌሎቹ ከሰለጠኑት በመልመድ ቀሪዎቹ ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው ሙያውን በመውረስ እንደሆነ በጥናቱ ታይቶዋል፡፡ የባህላዊ እውቀት ቅብብሎሹ የሚታየው ከቤተሰቦቻቸው ሙያውን በወረሱት ላይ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

የባህላዊ ቆዳ ስራ ባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወትን በተመለከተ ቀደም ሲል በሸርካ ወረዳ ይሰሩ የነበሩ ባለሙያዎች ከመስሪያ ቁሶች መወደድ የተነሳ ሙያውን እየላቀቁ ወደ ሌላ ስራ እየተሰማሩ እንደሆነና ከደቡብ ጐንደር ዞን እስቴ ወረዳ የመጡ ባለሙያዎች ግን ችግሩን ተቋቁመው እየሰሩ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል

በፎክሎር ጥናት Folk እንጂ Lore አይንቀሳቀስም የሚለውን የምሁራን አስተሳሰብ በጥናቱ በተግባር ተረጋግጦዋል። ይህም ሲባል ከደቡብ ጐንደር እስቴ ወረዳ የመጡ ባለሙያዎች ጐንደር ላይ የሚሰሩት ባህላዊ የቆዳ ስራ አርሲ ሽርካ ወረዳ ላይ ከሚሰራው የባህላዊ ቆዳ ስራ የተለየ እንደልሆነና የባለሙያዎች መቀያየር እንጂ ጥበቡ ያው ራሱ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል።

በዚህ ጥናት ዕለት ከዕለት የምርቱ ዓይነት እየቀነሰ መምጣት እና ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው ለባለሙያዎቹ በቂ የመስሪያ ስፍራ አለመኖር፣ የቆዳ ቁሶች መስሪያ ጥሬ እቃዎች መወደደ እና የፋብሪካ ቁሶች በርካሽ ዋጋ መቅረባቸው ነው። ማህበረሰቡም ከቆዳ ቁሶች ይልቅ ለፋብሪካ ውጤቶች ትኩረት መስጠቱ በጥናቱ ታይቶዋል። ጥናቱ በወረዳው የሚሰሩት ቁሶች የተጠቃሚ ሰዎችን ማህበራዊ ደረጃ በመጠቆም ላቅ ያለ ሚና መጫወታቸውን ያሳያል። ለምሳሌ በተለያዩ ዲዛይን ያማረ ነትን ሀብት ያላቸው ሰዎች ሲጠቀሙ ሌሎቹ ጀባን ይጠቀማሉ። አልያም ያልተሳለበትን ነት ይጠቀማሉ።

በዚህ ጥናት የባህላዊ የቆዳ ስራ ቆዳውን ከመሰብሰብ ጀምሮ እስከ ቁሶቹ ምርት ድረስ ያለው ሂደት እጅግ አድካሚና ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ አናሳ መሆን፣ ይህም ከድካሙ ጋር ተመጣጣኝ እንዳልሆነ በጥናቱ ታይቶዋል።

በተተኳሪ ወረዳው ላይ የሚኙት ባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት ሲታይ ደግሞ ቀደም ባሉት ላይ ማግለል እንደነበረ እና አሁን ግን የማግለሉ ሁኔታ እንደሌለ ጥናቱ ያሳያል።

## 5.2. የይሁንታ ሃሳቦች

ሽርካ ወረዳ ከጥንት ሲወርድ ሲወራረድ ማህበረሰቡ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በባህላዊ ግንኙነቶች አማካይነት የፈጠረው ቁሳዊ ባህል ያለው ነው። ከነዚህ ቁሳዊ ባህሎች መካከል ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ አንዱ ነው። እነዚህ የቆዳ ቁሶች የማህበረሰቡን እምነትና ማንነት የሚጠቁሙ ነገሮች ናቸው። ይሁንና እነዚህን ቁሳዊ ሀብቶች ወደፊት ለማስቀጠል የተለያዩ ችግሮች ገጥመዋል። አንደኛው በፋብሪካ ምርት ውጤቶች መስፋፋት የተነሳ በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ የቆዳ ቁሶችንና ያለመጠቀም አዝማሚያ ነው። ሁለተኛው ከሙያው ጋር በተያያዘ ስራው የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ከፍሎ ሙያውን ለማስቀጠል የሚፈልግ ትውልድ መጥፋት ሲሆን ሦስተኛው ለባህላዊ ቆዳ

ቁሶች ስራ የሚውል በቂ ቦታ አለመኖር ነው፡፡ ስለሆነም ይህ አሻራ ደብዛው ከመጥፋቱ በፊት ይመለከተኛል የሚሉ ባለድርሻ አካሎች ሊረባረቡ ይገባል፡፡

በዚህ ጥናት ይህንን ቅርስ ጠብቆ ለማቆየት ይረዳል ብዬ ያሰብኩትን ሃሳብ ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡ እንደዚህ ያሉ የማህበረሰብ ጉዳዮችን ችግር ለመፍታት የተለያዩ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ርብርብ ይጠይቃል፡፡ የሸርካ ወረዳ ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ባለሙያዎችም ሙያቸው ተከብሮ ኑሯቸው እንዲሻሻልና ቅርሶቹን ከትውልድ ወደ ትውልድ ጠብቆ ለማስተላለፍ፡-

- የሸርካ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ለማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በማዘጋጀት ስለባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ከፍተኛ የሆነ ስራ ቢሰራ
- የሸርካ ወረዳ ጤና ቢሮ ከማህበረሰቡ የሚነሳውን ሮሮ ለማስቀረት ከባህላዊ የቆዳ ቁሶች ጋር ተያይዞ በጤና ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ቢሰራ፣
- የጐቤሣ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለባህላዊ የቆዳ ቁሶች ባለሙያዎች ለስራው አመቺ የሆነ ቦታ በማዘጋጀት ስራውን በአግባቡ እንዲሰሩ ቢያደርግ
- የሸርካ ወረዳ አነስተኛና ጥቃቅን ማደራጃ ጽ/ቤት ወጣቶች በሙያው ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የተለያዩ ስልጠናዎች በማዘጋጀት ወጣቶቹ ተደራጅተው የባህላዊ ቆዳ ቁሶችን ስራ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ቢያመቻች
- የሸርካ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ለሙዚየም የሚሆን ቤት በማዘጋጀት ቁሶቹ ከያሉበት ተሰባስበው ለቱሪዝም አገልግሎት የሚውሉበትን መንገድ ቢቀይስና ሙዚየሙ ለቱሪስት ክፍት እንዲሆን ቢያደርግ

ከላይ እንደተዘረዘረው ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተረባርበው ከሰሩ የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በወረዳው ከፍተኛ የሆነ መሻሻል ያመጣል የሚል እምነት አለኝ፡፡

# ዋቢ ፅሁፎች

ሄለን አላምረው፡፡ "ባህላዊ ሽመናና ቆዳ ሥራ በደምበጫ እና አካባቢዋ፡፡" ያልታተመ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡ 1999 ዓ.ም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይ እና የሐዲስ ኪዳን መፅሐፍት፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መፅሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም፡፡

ታምራት ኃይሉ፡፡ "የብራና መጽሐፍት አዘገጃጀት በደቡብ ጐንደር እስቴ ወረዳ፡፡" ያልታተመ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡

አስራት ወልዴ፡፡ የቆዳ ስራ መምሪያ፣ አዲስ አበባ፣ የትምህርት ተራድኦ ማተሚያ ቤት፣ 1952 ዓ.ም፡፡

አበበ መርዕድ፡፡ "በጉባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና፡፡" ያልታተመ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡

የኔዓለም አረዶ፡፡ "የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት፡፡" ያልታተመ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ ባህርዳር፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ 1998 ዓ.ም፡፡

ዳንኤል ዘውዴ፡፡ የትምህርት ጥናትና ምርምር አተገባበር፣ አዲስ አበባ፡፡ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1994 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የሥነ ቃል መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢንተርናሽናል ጀርመን የጐልማሶች ትምህርት ተቋም፣ 1991 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ ሥላሴ ተፈራ፡፡ የብራና መፅሐፍ ግኝትና አጠባበቅ በኢትዮጵያ ብራና ጽሑፎች ድርጅት ለሲምፖዚየም የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ፣ 1979 ዓ.ም ያልታተመ፡፡

Central Statistical Authority. "The 1994 population and housing census of Ethiopia." Statistical Report, Addis Ababa, 1998.

Dorson, M. Richard (ed.) Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago press, 1972.

Dundes, Alan. Who are the Folk? PP 1-19 in: Alan Dundes. Interpreting Folk lore. Bloomington: Indiana University Press. 1980.

Fekade Azeze. Teaching Material Selected and compiled; Reader for Elti 621. Department of Ethiopian languages and Literature MA in Ethiopian Literature and Folklore, 2003.

Gallagher, J. "The preparation of Hides with sone Tools in South Central Ethiopia." Journal of Ethiopian Studies. V-12, No1, (1974): 176-177.

Georges, Robert A. and Michael Owen Jones. Folkloristic: An Introduction. Indiana University Press Bloomington and Indianapolis: 1995.

Hennry Glassie. Material Culture Bloomington and Indianapolis: Indiana University Press, 1999.

Jacques Dubois. "Traditional crafts" Roots and Flowerings of Ethiopian's Traditional Crafts. Nov. 2008:5

Marta C.Sims and Martine Stephens. Living Folklore. An introduction to the study of people and their traditions. Utah state University Press, 2005.

"Material Culture Objects". 1 Dec. 2004. <http://chnm. Gmu.edu /world history sources/ unpacking/objects ql.htm/>.

Mathisen, Stein R. Folk lore and cultural Identity. Anttonen and Kuidelland (ed). 1993.

Richard, Pankhurst, "The old-time handicrafts of Ethiopia" Ethiopian Observer. Vol.VIII No 3. (1964): 230-233

Prown, J. David 'Mind in Matter: an Introduction to Material Culture Theory and Method' on line, Available at: http://www.Jstor org/about/ terms/html.1982.

Roberts, E Warren. "folk Crafts" in Folklore and Folk life: An Introduction. Dorson, Richard's ed; Chicago and London: The University of Chicago Press. 1972.

Schlereth Thomas. Artifacts and the American Past. Online. Available at: www.http://Btnep.org.1980.

Silver man. Ray Mond A. (ed). Ethiopian Traditions of Creativity. East Lasting: Michigan State University Museum, 1999.

## አባሪ አንድ

## ለወረዳው ነዋሪዎችና ለሀገር ሽማግሌዎች የቀረበ ቃለ መጠይቅ

### ግላዊ መረጃ

1. ሙሉ ስም
2. ፆታ
3. ዕድሜ
4. የትምህርት ደረጃ
5. የቤተሰብ ሁኔታ
6. የመኖሪያ አድራሻ
7. ሃይማኖት
8. ስራ

### አካባቢያዊና ባህላዊ መረጃ

1. የወረዳውና የከተማው አስያየም እንዴት ነው? ማን ሰየመው? መቼ ተሰየመ?
2. ማህበረሰቡ ቆዳን ለምን ለምን አገልግሎት ይጠቀማል?
3. በባህላዊ ቆዳ ስራ ምን ምን ቁሶች ይሰራሉ?
4. ከጐንደር እስቴ ወረዳ የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች እንዴት ወደ ወረዳው ሊመጡ ቻሉ?
5. የባለሙያዎቹ ማህበራዊ ሕይወት እና ኢኮኖሚ ሁኔታ ምን ይመስላል?
6. የባህላዊ የቆዳ ቁሶችን ይጠቀማሉ? ለምን አገልግሎት?
7. ባህላዊ ቁሶቹ ከእምነት ጋር የተያያዘ ነገር አላቸው?
8. ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? ጋብቻን በተመለከተስ?
9. ባለሙያዎቹ በአካባቢው ላይ ያደረሱት ጉዳት አለ? ካለ ምንድ ነው?
10. የወረዳውን አጠቃላይ ገጽታ ቢገልፁልኝ?

## አባሪ ሁለት

## ለቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

### ግላዊ መረጃ

1. ሙሉ ስም
2. ፆታ
3. ዕድሜ
4. የትምህርት ደረጃ
5. የቤተሰብ ሁኔታ
6. የመኖሪያ አድራሻ
7. ሃይማኖት
8. ስራ

### ከቆዳ ቁሶች ስራ ጋር የተያያዙ ቃለ መጠይቆች

1. ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በሽርካ ወረዳ እንዴት ተጀመረ? መቼ ተጀመረ? በማን ተጀመረ?
2. ባህላዊ የቆዳ ስራን እንዴት ለመዱት?
3. ባህላዊ የቆዳ ቁሶች መስሪያ ጥሬ ዕቃዎች ምንድናቸው? የሚሰበሰቡት ከየት ነው? እንዴት ነው?
4. ለማህበረሰቡ ያለዎት አመለካከት ምን ይመስላል?
5. ከጉንደር እስቴ ወረዳ ስለመጡ የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች ቢገልፁልኝ?
6. የባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ ባለሙያዎች አሁን በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?
7. ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ስራ በፊትና አሁን ያለውን አንድነትና ልዩነት እያነፃፀሩ ቢገልፁልኝ?
8. ከብረታ ብረት ሰራተኞች ጋር ያላችሁ የሥራ ግንኙነት ምንድ ነው?
9. የአንዱ ቁስ ዋጋ ምን ያህል ነው?
10. በባህላዊ የቆዳ ስራ ላይ ያጋጠመዎት ችግር አለ? ካለ ምንድ ነው?

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

## የሀገር ሽማግሌዎች እና የወረዳ ነዋሪዎች


| ተ/ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | የት/ት ደረጃ | የቤተሰብ አድራሻ | የመኖሪያ አድራሻ | ሃይማኖት | ስራ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | ርዕስ ጉዳይ | መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ | መረጃ የተሰጠበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ስለሺ ተስፋዬ | ወ | 60 | 6ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ሽቀጣሽቀጥ ነጋዴ | 1/6/04 | የሽርካ ወረዳ አመሰራረትና የባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት | በቪዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ጠላ ቤት | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 2 | አቶ ደርቤ ይፍሩ | ወ | 46 | 9ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | እህል ነጋዴ | 1/6/04 | የባለሙያች ማህበራዊ ህይወት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ጠላ ቤት | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 3 | መ/ር ጌቱ ተፈራ | ወ | 43 | ዲግሪ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | መምህር | 2/6/04 | የማርገቢያ ምራን፣ መርገጥ እና ቤት ማዋቀሪያ ጠፍር አሰራር | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | መኖሪያ ቤት | |
| 4 | መ/ር ኃይልዬ ማንደፍሮ | ወ | 48 | ዲፕሎማ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | መምህር | 4/6/04 | ስለ ባለሙያዎች መረጃ እና ስለ ከተማው አመሰራረት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ሲርባ ወንዝ | ቁልፍ መረጃ አቀባይ |
| 5 | አቶ ጌታሁን ከበደ | ወ | 45 | ዲግሪ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | የስታትክቲክ ባለሙያ | 6/6/04 | ስለትምህርት ቤቶች አጀማመርና አሁን ያሉበት ሁኔታ | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ሽርካ ወረዳ ት/ቤቶች ጽ/ቤት | |
| 6 | አቶ አፈወርቅ ጋረደ | ወ | 59 | 8ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ጠጅ ጫጭ | 8/6/04 | ስለወረዳው አመሰራረትና ስለባለሙያዎ ች ማህበራዊ | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ክብት ተራ | |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | ህይወት | | |
| 7 | አቶ ዘገዬ ወልዴ | ወ | 65 | 4ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ድለላ | 1/6/04 | ስለሽርካ ወረዳ አመሰራረትና የባለሙያዎች ህይወት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፐሪኮርደር | ጠላ ቤት |
| 8 | ወጣት ዳንኤል ዘውዴ | ወ | 34 | 12ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ሆቴል ንግድ | 1/6/04 | ስለ ባለሙያዎች ማህበራዊ ህይወት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፐ ሪኮርደር | ጠላ ቤት |
| 9 | አቶ አሰፋ ገበቶ | ወ | 55 | 12ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ነጋዴ | 10/6/04 | ስለ ከተማዋ አመሰራረት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፐሪኮርደር | ሱቅ |
| 10 | አቶ ደመቀ በላይ | ወ | 65 | 6ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | የጥበቃ ሰራተኛ | 10/6/04 | ስለ ሽርካወረዳ አመሰራረት ስለ ባለሞያዎች ሕይወት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፐ ሪኮርደር | ት/ቤት |

# የመረጃ አቀባዬች ዝርዝር መግለጫ

| ተ/ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | የት/ት ደረጃ | የቤተሰብ አድራሻ | የመኖሪያ አድራሻ | ሃይማኖት | ስራ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | ርዕስ ጉዳይ | መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ | መረጃ የተሰጠበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ተገኔ ተስፋዬ | ወ | 26 | 6ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ግብርና | 12/6/2004 | ስለ አለንጋ አሰራር | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ጉቤሣ መኖሪያ ቤት | |
| 2 | አቶ ፈለቀ ተስፋዬ | ወ | 30 | 7ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ግብርና | 12/6/04 | ስለ ጉፍላ፣ ገንባሌ፣ እጅ ቤዛ አሰራር | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | መኖሪያ ቤት | |
| 3 | አቶ አሰፋ ጫላ | ወ | 28 | 5ኛ | ያገባ | ሌሙና ጢጆ | ኦርቶዶክስ | ግብርና | 12/6/04 | ስለ ጉመድ አሰራር | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | መኖሪያ ቤት | |
| 4 | አቶ እግዳሰው ሳህሌ | ወ | 57 | 8ኛ | ያገባ | ያያ ኡርጉባ | ኦርቶዶክስ | የገንዘብ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት መዝገብ ቤት | 17/6/04 | ስለ ሸርካ ወረዳ አስያየም እና ስለ ቆዳ ባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ለቅሶ ቤት | |
| 5 | አቶ ፍቃዱ ነጋሳ | ወ | 45 | ዲግሪ | ያገባ | ያያ ኡርጉባ | ኦርቶዶክስ | የጤና ባለሙያ | 18/6/04 | ስለ ጤና ጣቢያ አመሰራረት እና ሳኒቴሽን | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ጉቤሣ ጤና ጣቢያ ቢሮ | |
| 6 | ወ/ሮ ብዙነሽ ተኮላ | ሴ | 46 | ያለተማረ ተ | ያገባች | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ጠላ ሻጭ | 3/6/04 | ስለ ማሲኖዳ አሰራር እና ስለ ቀረቦ አሰራር | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | መኖሪያ ቤት | |
| 7 | ወ/ሮ ፋኖሴ መብራቴ | ሴ | 31 | 8ኛ | ያገባች | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | የስፌት ባለሙያ | 8/6/04 | ስለ መሶብ ስፌት አሰራር | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕሪኮርደር | መሶብ ተራ | |
| 8 | ወ/ሮ አበበች በልሁ | ሴ | 80 | ያልተማረ ች | ያገባች | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | የስፌት ባለሙያ | 27/5/04 | ስለ ጀባ አሰራር እና የባለሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | መኖሪያ ቤት | |
| 9 | አቶ አብደላ አብራሂም | ወ | 35 | ዲፕሎማ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | የመምህራን ማህበር ተወካይ | 6/6/04 | ስለ ሸርካ ወረዳ መምህራን | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕሪኮርደር | በሸርካ ወረዳ መምህራን ማህበር ጽ/ቤት | |
| 10 | አቶ አሸናፊ ሸኖ | ወ | 35 | 12ኛ | ያገባ | ጉቤሣ 01 | ኦርቶዶክስ | ጠበቃ | 4/6/04 | ስለ ሸርካ ወረዳ አመሰራረትና ስለ ባሙያዎች ማህበራዊ ሕይወት | በሺዲዮ፣ ካሜራ እና በቴፕ ሪኮርደር | ቢሮ | |

# ባህላዊ የቆዳ ቁሶች ሥራ



ተወጥሮ የደረቀ ቆዳ



ዳዩ ጎብረት እንዳያ ከረውን ሲለለብት



የተወጠሩ ቆዳዎች




የቆዳው ተረፈ ጋርን ሲነሳ



ቆዳ ሲፋቅ


ቆዳ ሲወጠር


ቆዳ ሲወጠር


አቶ ጌቶ ፀሐይን ሲወስዱት


የቆዳው ውጥር ሲፈቱ


አቶ ካሳ ደሴ ቆዳ ተሸክመው

# ቃለ መጠይቅ



አቶ ስለሺ ተስፋዬ



አቶ ዘገዬ ወልዴ



አቶ ደርቤ ይፍሩ




ወጣት ደንኤል ዘውዴ




አቶ ከበደ በዳኔ



ሐጂ አብዲ ከዲር




አቶ በረከት አውግቸው



ወ/ሮ ብዙነሽ ተኮላ



አቶ ጌታሁን ከበደ



መምህር አብደላ ኢብራሂም




ወ/ሮ በለጡ ከበደ



አቶ በላይነህ ማሞ



አቶ ወጋየሁ ፀጋዬ



አቶ አሸናፊ ሸኖ



አቶ አሰፋ ገበቶ



ወ/ሮ ፋኖሴ መብራቱ




ሐጂ ከማል ቃሶ



አቶ አፈወርቅ ጋሪዬ



አቶ ተገኜ ተስፋዬ



አቶ አሰፋ ጫላ

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ የእኔ ወጥ ስራ ነው። ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴንም በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ጥቅምት 2005 ዓ.ም